**ይዘት፡ ...........................................................ገፅ**


የብስራት መፅሄት መልእክት ..............................................................46

ድርጅታዊ መግለጫ..............................................................................47

ጠለቀች ሲኋት የፈለቀች ፀሐይ............................................................50

ከታጋይ ይብራህ በርሄ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ......................................56

የኢህአዴግ በጥልቀት የመታደስ ሂደት ከየት ወዴት? ምንስ ይመስላል?........................................................................................67

የኢህአዴግ ስርዓት በስልጣን እንዲቀጥል ያስቻለው ምክንያት ምንድነው?..................73

የትግራይ ህዝብ ሊሄደው የሚፈልገው መንገድና ተግዳር ፈጠሪዎቹ፡......................79

የህዝባችን የማንነት ጥይቄ፡ ህገ-መንግስታዊ መልስ ሲያገኝ እንጂ በበትር አይቀለበስም፡..........................................................................82

ህዝብ ነው ሃያሉ/ ግጥም/ ..................................................................86



ቴሊፎን.............................00291-153947

ፋክስ...............................00291-153946

ፖስታ ሳፁን ቁጥር...............1653

ዌብ-ሳይት............ www.demhitonline.com

ኢ-መይል............. tpdm1993@yahoo.com

## የብስራት መፅሄት መልእክት

ይህ ወር በአገራችን ታሪክ አበይት ታሪካዊ ፍፃሜዎችን ያቀፈ ታሪካዊ ወር ነው። ሌሎች የታሪክ ፍፃሜዎችን ትተን፡ መተንፈሻ አጥቶ የነበረው ህዝባችን የኢህአዴግን የአፈና ሰንሰለት በጣጥሶ ጭቆናን ለመታገል የትህዴን ትግል የማዕዘን ድንጋይ ያስቀመጠበት የካቲት 19/1993 ዓ/ም ታሪካዊ ቀን ናት፡ በዚህ አጋጣሚ ደግሞ ይህች ልሳነ ሐቅ የሆነችው መፅሄታችሁ ብስራት መፅሄት፡ ከሁሉ በፊት እንኳን ወደ እዚህች ታሪካዊት ወር፣ ታሪካዊቷ ቀን የካቲት 19 የተጋድሎአችን ምስረታ በአል በሰላም አደረሣችሁ አደረሰን ትላለች።

ብስራት መፅሄት በየግዜው ህዝባዊ ሃላፊነት የማይሰማቸው መንበረ ስልጣን ተቆጣጥረው የሚገኙ ኢህአዴጋዉያን፡ በህዝብና በሃገር ላይ ሲፈፀም የቆየና ያለ ታሪክ ይቅር የማይለው ግፍና በደል በ24 እትሞቿ እያጋለጠቻቸዉ መጥታለች። እንደዉጤቱ ደግሞ ለህዝባችን በተለይ ደግሞ የለውጥ ሃይል ለሆነ የሃገራችን ወጣት ትዉልድ የስርአቱን ተግባራት ኮንኖ የለውጥ መስኮቶችን ከፍቶ፡ ወደ ትግል እንዲጎርፍ በማድረግ የላቀ ሚና ተጫውታለች።

አሁንም ብስራት መፅሄት ከ2ኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችን በኋላ ለመጀመርያ ጊዜ እያከበርነው ላለን 16ኛው አመት የትጥቅ ትግላችን የምስረታ በዓል የካቲት 19 ምክንያት በማድረግ፡ በተጨባጭ ፖቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የህዝባችንንና የሃገራችንን ሁኔታ አስመልክታ፡ እንዲሁም የኢህአዴ "ጥልቅ ተሃድሶ" ምን እንደሚመስል የሚዳስሱ ፅሁፎችን ይዛላችሁ ቀርባለች። ብስራት መፅሄት ከዚህ ውጪ ከትህዴን ምክትል ሊቀመንበር ታጋይ ይብራህ በርሀ ጋር አጭር ቃለ-መጠይቅ አካሂዳለች።

ክቡራን የብስራት መፅሄት አንባቢዎች ዋና አላማችን በኢትዮጵያ ህዝቦች አንድነትና ውህደት የምታምን አንዲትና ጥምርት ኢትዮጵያን መመስረት ነው። ለዚህ አላማ እምነው ገሃድ ለማድረግ ደግሞ የህይወት መስዋእት እየከፈሉ ያሉ ቆራጥ ለህይወታቸው የማይሰሱ የትህዴን ታጋዮች ከሁሉ በላይ ክብር ይገባቸዋልና እንኳን ወደ እዚህች ክብርት ቀን አደረሣችሁ ትላለች።

በአጠቃላይ ደግሞ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ፡ በተለይ ደግሞ የለዉጥ ሃይል ለሆነዉ ወጣት ትዉልድ፡ ይህች እየፈለግናት ያለነው የተዋሃደች ኢትዮጵያ ልትመጣ የምትችለው በትጥቅ ትግል ብቻ መሆኑን አምኖ ከብቦት ካለው አጥር ጥሶ በመዉጣት ወደ ታጋዮች ማዕድ እንዲሰለፍና ለማይቀረው ለውጥ የድርሻውን ይወጣ ዘንድ የብስራት መፅሄት መልእክት ነው።

በመጨረሻ ፍፁም የሚባል ስራ የለምና በዚህች ለ10ኛ አመት ለ25 ጊዜ ለህትመት የበቃችው ብስራት መፅሄታችን የሚታያችሁን ስህተት ወይም ሂስ ሆነ አስተያየት ካላችሁ ከላይ በሰፈረው አድራሻችን መሠረት ልትልኩን ትችላላችሁ። ደግመን እንኳን ወደ እዚህች ክብርት እለት አደረሳችሁ ለማለት ትወዳለች። መልካም ንባብ፦

ድምቀት የተጋድሏችን የምሥረታ እለት ለሆነችው 19 የካቲት!!
ድል ለጭቁኖች!!

## የካቲት 19 የድርጅታችን ትህዴን 16ኛ ዓመት የምሥረታ በዓል ምክንያት በማድረግ የተሠጠ ድርጅታዊ መግለጫ!!

የተከበርክ በውስጥና በውጭ የምትገኝ የኢትዮጵያ ህዝብ፡ የተከበርክ ጀግናው የት.ህ.ዴ.ን ተጋይ፡ የተከበራችው በውስጥና በውጭ የምትገኙ የድርጅታችን ስቢል ኣባላት፡ ድርጅታችን የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ት.ህ.ዴ.ን/ ጭቁንነት ባንገፈገፋቸው፣ የአምባገነኖችን የባርነት ቀንበር ባልተቀበሉ፣ የህዝባቸው ብሶት በሚሰማቸው የህዝብ ልጆች ልክ በዚህ ሰሞን በየካቲት 19 ቀን 1993 ዓ.ም የነፃነት መባ ለመሆን በረሃ ወጥተው ሲመሰርቱት ወቅታዊና ፍትሃዊ ስለነበር ብዙ ተከታዮችን አግኝቶ ዓበይት ፖለቲካዊና ወታደራዊ ስራዎችን እየፈፀመ ነው እዚህ ደረጃ ደርሶ ያለው።

ድርጅታችን ከነሐሴ 28 ቀን እስከ ጳጉሜ 4 ቀን 2008 ዓ.ም ባካሄደው ስኬታማ 2ኛው ድርጅታዊ ጉባኤ የነበሩንን ውስጣዊ ደካማ ጎኖችና ጠንካራ ጎኖች ለይተን፣ የጠላታችንን ሁኔታ ደግሞ በጥልቀት በመገምገም ለቀጣይ ሊያሰራን የሚችል እስትራቴጂ ነድፈን በአስተማማኝ ደረጃ ሆነን የትግል ጉዟችንን ወደ መጨረሻው ድል ለማድረስ በፍጥነት በመገስገስ ላይ እንገኛለን።

ት.ህ.ዴ.ን እንደ ድርጅት እስካሁን የሰራቸው ስራዎች የትኞቹ ናቸው? ሊሰራቸው ከሚገባው ያልተደረሱ ወይም ያልተጨበጡ ድሎችስ የትኞች ናቸው? ለቀጣይስ በምን ዓይነት እስትራቴጂ ከተጓዝን ነው ወደ ሙሉ ድል ደርሰን ህዝባችን ካለው ጨፍላቂ ስርዓት አርነት አውጥተን የተመቻቸ ህይወት ለመምራት እንዲችል የሚል በጥልቀት ገምግመን በ2ኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችን የነደፍናቸውን የትግል እቅዶች ከግባቸው ለማድረስ ቀን ከሌት በኃያል ጥረት ላይ እንገኛለን።

ብዙ ወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግን የሚታገሉ ድርጅቶች በሰላማዊ ፖለቲካዊ ትግል ከስልጣኑ ይወገዳል ብለው ወስነው ሰላማዊ ትግል ያካሂዱ በነበሩበት ወቅት፡ ት.ህ.ዴ.ን የወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ስርዓት በትጥቅ ትግል እንጂ በሰላማዊ መንገድ ከስልጣኑ ሊወርድ አይችልም የሚል አቋም ይዞ አማራጭ የሌለው መፍትሄ የትጥቅ ትግል እንደሆነ ሲወስን ደግሞ ልክ አሁን እየታዘብነው እንዳለነው ስርዓቱ አምባገነናዊነቱን እያስፋፋ እንደሆነ አስቀድሞ ስለ አወቀው ነበር።

ይህ አሁን በስርዓቱ በህዝባችን ላይ እየተፈፀመ ያለው አሰቃቂ በደል ደግሞ ለድርጅታችን ት.ህ.ዴ.ን ከ16 ዓመታት በፊት ግልጽ ስለነበር፡ የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ይህን አረመኔያዊ ስርዓት ለማስወገድ የመጨረሻ መፍትሄው የትጥቅ ትግል ነው ብሎ አስምሮበት ያለፈ ጉዳይ ነው። የወቅቱ ውሳኔያችን ትክክለኛና የማያሻማ እንደነበረ ደግሞ በዚህ በአገራችን አጋጥሞ ባለው ወቅታዊ ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ አረጋግጠናል።

የተከበርከው የኢትዮጵያ ህዝብ፦ የወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ስርዓት በንፁሃን ወገኖቻችን ላይ እያወረደው ያለው አፈናና ረገጣ፣ ግድያና እስራት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ በመምጣት ዛሬ የመጨረሻ ጫፍ ላይ ደርሶ ልትታገሰውና ልትቋቋመው በማትችለው ጫፍ ደርሶ ይገኛል። የዚህ ውጤት ደግሞ በተለይ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ በስርዓቱ ላይ እያደረግኸው ያለኸው አመፅና ንቅናቄ በጣም የሚያኮራ ነው። እንደውጤቱም ስርዓቱን አናግቶ ከውድቀቱ ጫፍ ላይ ደርሶ ይገኛል።

የወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ስርዓት በስልጣን ኮረቻ ላይ ተኮፍሶ ህዝባችንን እየበዘበዘ ለመቀጠል የዘላለም ምኞቱ ስለሆነ ስልጣኑን እንዳያጣ ሲል ብዙ እንቅፋቶችን እየፈጠረ ነው የሚገኘው። የዚህ ማሳያ ደግሞ ህዝባዊ አመፆችን ለማስቆም ብሎ ያወጀው የአስቸኳይ ጊዜ

አዋጅ ህዝብ እንደ ህዝብ፣ ሃገር እንደ ሃገር አጥር የሆኑ መምሪያዎችን አውጥቶ ቆርፍዶ በመያዝ አራጊ ፈጣሪ ሆኖ ቸፈረሴ ለማለት ያሰበው ወጥመድ ወደ ራሱ እንዳይገለበጥ ላይ ታች ሲል ይታያል። ይሁን እንጂ ይህ ሲካሄድ የቆየው ህዝባዊ ተቃውሞ ከጥቂት የቴክኒክ እጥረቶቹ በስተቀር ትክክለኛ የለውጥ መንገድ ነው የነበረው። ለህዝብና ለአገር አደጋ ሆኖ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚታወጅበት ምክንያት አልነበረውም። አደጋ ሊሆን የሚችለው ለፀረ ህዝቡ ስርዓት ብቻ ነው። ይህ አዋጅ ደግሞ አገራችንን እንደ አገር የህግ ሽፋን ተጠቅሞ ህጋዊ እስርቤት ለማድረግ ያለመ ነው። በዚህ የተነሳ ደግሞ ህዝብና በስልጣን ላይ ያለው ገዥው ስርዓት ሙሉ በሙሉ ሊነጣጠሉ ችለዋል።

ይህ ስርዓት ህዝብ አንድ ሆኖ በላዩ ላይ ተነስቶ እንዳለ ሙሉ መረጃ ስለያዘ ይህንን ህዝብ አንድነቱን እንዳልነበረ ለማድረግ ከፋፍለህ ግዛ የሚል እኩይ እስትራቴጂ በተግባር በማዋል በግልፅና በድብቅ ህዝባችንን በታትኖ ሃይሉን ለማዳከም ሳይሰለች እየሰራ ነው። በሆዳቸው ባደሩት ካድሬዎቹ ተጠቅሞ እስከ ቀበሌ እየወረዱ አንድ ብሄር በሌላው ብሄር ላይ ጥቃት እንዲያውጅ መነሳሳት ሲያደርጉ ቆይተዋል። አሁንም እያደረጉ ይገኛሉ።

እንደውጤቱ ደግሞ በአንዳንድ ወገኖች በትግራይ ህዝብ ላይ እየወረደ ያለው ብሄርን መሠረት ያደረገ ጥቃት፡ በትግራይ ተወላጆች ላይ ከባድ የአካልና የህሊና ቁስል ፈጥሯል። ብዙ ዜጎች ህይወታቸውን እንዲያጡ፣ ለአመታት ከርተት ብለው ያፈሩት ንብረታቸው እንዲቃጠል፣ ይኖሩበት ከነበሩት አካባቢዎች በሃይል ተባረው ንብረታቸውንና ቤታቸውን ትተው እንዲወጡና ባዶ ሜዳ ላይ ተወርውረው ለፀሐይና ለንፋስ ለተለያዩ ህመሞች ሊጋለጡ ችለዋል።

ስለዚህ የዚህ መነሻና ተጠያቂው ወያኔ ቢሆንም እንኳ የተለያየ ሽፋን ተጠቅሞ በትግራይ ህዝብ ላይ የሚፈፀመው ጥቃት ተቀባይነት ስለሌለው፡ የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ አጥብቆ ይቃወመዋል፡ ይኮንነዋል። የት.ህ.ዴ.ን ድርጅት ለህዝብ ብሎ ከባድ መስዋዕት እየከፈለ ያለ ህዝባዊ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን በጭቁኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ተቃራኒ የታጠቁ ሃይሎችን በህዝብ ላይ መጥፎ እርምጃ የሚወስዱ ሰወችን ደግሞ ከስርዓቱ ለይቶ እንደማያያቸው ያስጠነቅቃል። ስለዚህ ሁላችን ኢትዮጵያውያን ከጠባብነትና ከትምክህት ወጥተን የትግላችን ኢላማ በስልጣን ላይ ባለው ስርዓት ላይ ብቻ ማነጣጠር እንዳለበት ት.ህ.ዴ.ን ጥሪውን ያቀርባል።

**የተከበርህ ሕዝባችን፦** በዚህ ባለፈው አመት 2008 ዓ.ም ጀምረህ እስካሁን በከባድ ድርቅና የስርዓቱ ብልሹ አስተዳደር በሁለት አለንጋ እየተገረፍክ እያሳለፍከው ያለኸው ህይወት ለድርጅታችን ት.ህ.ዴ.ን የሚያሳዝን ፍፃሜ ነው። እነዚህ እንደ ጅብ ቁስላቸውን እየበሉ የሚሄዱ መሪዎች ነን ባዮች ግን፡ በድርቅ ስም ከውጭ ሃገሮች ለሚያመጡት ረድኤት አንተን በጉሮሮህ ይዘው የራሳቸውን ሞልተው እየጎረሱ በግላዊ ጥቅማቸው እያዋሉት መምጣታቸው እንዳይበቃ ድርቅ የሚቋቋም ኢኮኖሚ ገንብተናል፡ ድርቅ እንጂ ረሃብ የለም እያሉ ያልበላኸውን በላህ ሲሉህ እየሰማን ነው። ዛሬ በአብዛኛው የአገራችን አካባቢዎች የንፁህ መጠጥ ውሃ ካለመኖሩ ጋር ተያይዞ ድርቅና የውኃ ጥም ተጋግዘው እየገረፉህና ለተለያዩ ውሃ ወለድ በሽታዎች ተጋልጠህ እየተሰቃየህ ቢሆንም ስርዓቱ ግን ይህንንም ሊደብቀው ነው እየፈተነ ያለው።

ስለዚህ ወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ባለፉት 25 ዓመታት በስልጣን ላይ ቢቆይም በአገር እድገትና በሕብረተሰቡ አኗኗር ላይ የሆነ ይሁን ተጨባጭ ለውጥ ሊያመጣ አልቻለም። በተቃራኒው ግን የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እያፈነ፣ ዴሞክራሲ ብሎ

የሚጠይቀውን ደግሞ በአደባባይ በግልፅ እየረሸነ፣ አስሮ እያሰቃየ፣ ለህዝባችን በጉቦና በአድሎ ቤቱን እየዘረፈ ወደ አስከፊ ድህነት ሊያስገባው ችሏል።

ስለዚህ ያለንበት ወቅት ከአለፈው ጊዜ በላይ የትግል ጊዜ ስለሆነ ጭቁንነታችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ በመሄድ ወደ ከፋ ደረጃ ስለደረሰ የትጥቅ ትግል አማራጭ የሌለው የመጨረሻ አማራጭ መሆኑ የተረጋገጠበት ጊዜ ስለሆነ፡ ትግላችን ወቅታዊና ፍትሃዊ ነው ብለን አጠናክረን የምንቀጥልበት መሆናችንን ለማረጋገጥ እንወዳለን።

**የተከበርህ የኢትዮጵያ ህዝብ፦** ይህ የአንድነትህና የእድገትህ ፀር በመሆን የተነሳውን ስርዓት ሙሉ በሙሉ ከስልጣኑ ተገርስሶ መውረድ ስለሚገባው ካለፈው ጊዜ በላይ አደረጃጀትና ትግል ይጠይቅሃል። እየተመኘኸው ያለኸው የዴሞክራሲ ለውጥ በአጭር ጊዜ ለማረጋገጥ፡ መጭዋን ኢትዮጵያ ከሚያለመልሙ ድርጅቶች ጋር ልትጣመርና ድርሻህን ልታበረክት የምትችልበት ጊዜ አሁን ነው። አገራችን ኢትዮጵያ በአደገኛ ቀይ መስመር ረግጣ እንዳለች ተረድተህ አገርህን ከመበታተን እንድታድናት ጊዜ የማይሰጥ አስቸኳይ የቤት ሥራ እንዳለብህ አምነህ ተነስ።

**የተከበራችሁ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅቶች፦** አሁን ያለው የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ስርዓት የፈጠረው በህዝባችን እየታየ ያለው መከፋፈልና ጥላቻ ወደ ነበረበት ሊመለስ ከሆነ፡ በዋናነት ደግሞ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ስርዓት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከስልጣኑ ሊወገድ ከሆነ እኛ የግድ በህብረት ልንሰራና ልባዊ መተጋገዝና ቅርርብ ልናደርግ ይገባል። የእኛ አንደነትና ውህደት ለኢትዮጵያ ህዝቦች ፍቅርና የጋራ እድገት ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ከዚህ ውጭ የሚደረግ ጉዞ ግን ስርዓቱን ካልሆነ በስተቀር ለማንም ሊጠቅም እንደማይችል ደግመን ልናሰምርበት እንወዳለን።

ይህ ወቅት አንድነትን የሚጠይቅ ወቅት ስለሆነ ድርጅታችን ት.ህ.ዴ.ን ለጋራ ጥቅምና ዘላቂ ሰላም አስመልክቶ የመሰረተው ትግል ከግቡ ለማድረስ ከሁሉም በኢትዮጵያ አንድነት በሚያምኑ ታጋይ ድርጅቶች አብሮ ለመስራት ዝግጁ መሆኑን ያረጋግጣል።

ድርጅታችን ት.ህ.ዴ.ን ይዞት ያለው ትግል ደግሞ ወቅታዊና ፍትሃዊ ስለሆነ ገና ስንመሰርተው እዚህ ደረጃ ላይ ይደርሣል ብቻ ሳይሆን፡ ለዚህ ፀረ ህዝብ ስርዓት ደምስሶ ሠላምና ዴሞክራሲ እንደሚያረጋግጥ ቅንጣት ታህል ጥርጣሬ የለንም። ስለዚህ ይህን ፍትሃዊ የህዝብ ትግል ከግቡ ለማድረስ ከማንኛውም ጊዜ በላይ ጠንክረን እንታገላለን።

ለማጠቃለል ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ በውስጥና በውጭ ለምትገኙ የትግላችን ደጋፊዎች፣ ስለጭቁኖች ክቡር መስዋዕት እየከፈላችሁ ያላችሁ ጀግኖች የት.ህ.ዴ.ን ታጋዮች፡ እንኳን ለየካቲት 19 የድርጅታችን ት.ህ.ዴ.ን 16ኛ ዓመት የምሥረታ በዓል በሠላም አደረሳችሁ እያልን፡ እጋምሰነው ያለነው 2009 ዓ.ም የድል ዘመን ይሆንልን ዘንድ ት.ህ.ዴ.ን መልካም ምኞቱን ይገልጻል።

ዘላለማዊ ክብርና ሞገስ ለጀግኖች ሰማዕታቶቻችን!!
ድል ለጭቁኖች!!
የካቲት 19 ቀን 2009 ዓ.ም

# ጠለቀች ሲኋት፤ የፈለቀች ፀሐይ!!

"ደጋ የልቡን ያኸልማል" ሲባል ሰምታችኋል? የሠው ልጆች ስንባል በተፈጥሯችን ስግብግቦች እየሆን ነው መሰል፡ እየመረረን እንኳን እውነት መናገር አንወድም። የሐቀኝነት ማተብን ይዘን መሬት ላይ ያለውን ተጨባጭ እውነታ ከምንመሰክር ይልቅ፡ ጥቁሩን ነጭ ነው እያሉ የሚከራከሩት ጥቂቶች አይደሉም። ፖለቲካ ነው የሚል ሽፋን እየተጠቀምን አንደኛውን ወገን ከፍ አድርገን ሌለኛውን ወገን በቃላቶቻችን መሬት ላይ ተንሸራቶ እንደወደቀ አድርገን የምንገልፀው ስንቶቻችን ነን? ምናልባት ግን ፖለቲካም ቢሆን እኮ እውነት ይዞ ነው የሚያሸንፍ እንጂ የሌለውን ሰብኮ አይደለም ማሳመን ያለበት።



የተደበቁ እውነታዎችን ገልጦ፣ የተቀበሩ ጉዳዮችን ቆፍሮ፣ ትኩረት ያልተደረገባቸውን ማዕዘናት ተመልክቶ፣ በአጠቃላይ ለህዝቡ የተደበቁትን ከእይታው የራቁትን እያያቸው ሳለም ሊያስተውላቸው ያልቻለ ሐቆችና ጭብጦች ከህዝብ የተለየ መነፅር /መካኒዝም/ ተጠቅመህ ህዝብ እንደሚያያቸውና መፍትሔዎችን እንዲፈልግላቸው ማድረግ ነው ፖለቲካ መባል ያለበት እንጂ፡ በፖለቲካ ስም ያልተፈፀመ ነገር ይዞ መቅረብ የስልጣኔ ወይም የፖለቲካ ብስለት መገለጫ አይደለም።

ይህች ፀሐይ በቃ ጨልማለች ዳግም አትወጣም እያለ የሚሰብክ ግለሰብ ይሁን ቡድን ቢገጥማችሁ ልታምኑት ትችላላችሁ? መልሳችሁ በፍፁም እንደሚሆን እርግጥ ነው። ምክንያቱም ፀሃይ እንቅስቃሴዋን የማታቋርጥ ኃያል ዘወትር የምትመላለስ ብርሃን ናትና። ምናልባት ለቀጣይ እንዴት ትሆናለች የሚል ትንቢት ማስቀመጥም ድፍረት ስለሆነ፤ ሁላችንን ለፈጠረው ፈጣሪ ብቻ የሚመለከት ኃላፊነት ነው። እኛ ግን ፅሑፋችን ስለ ፀሃይ አይደለም። ፅሑፋችን ስለ ጠለቀች ሲኋት የፈለቀች ፀሐይ ነው።

የትግራይ ህዝብ ት.ህ.ዴ.ን የሚል ድርጅት መስርቶ የትጥቅ ትግል ጀመረ የሚል ዜና በሰማ ጊዜ ምን ዓይነት ደስታ እንደተሰማው ራሱ ያውቀዋል። ምክንያቱም ለዓመታት በጉጉት ሲጠብቀው የነበረ ፍፃሜ ስለነበር። ት.ህ.ዴ.ን የሚባል ድርጅት ፈረሠ የሚል ዜና በሰማ ጊዜ ደግሞ ምን አይነት ሃዘን ሊሰማው እንደሚችል መግለጫ ቃላት የለውም።

ለማንኛውም ወደ እዚህ ፅሁፍ ቁምነገር እንግባ። የትግራይ ህዝብ ህ.ወ.ሓ.ት የተባለ የሽፍቶች ቡድን ስልጣን ከተቆጣጠረበት ጀምሮ የዴሞክራሲና የፍትህ እጦት፣ የሰላምና የእኩልነት እጦት፣ በአጠቃላይ የቡድኑ ክህደትና ውለታ ቢስነት የወለደው የደም እንባ ከማልቀስ ተለይቶ አያውቅም። በዚህ የተነሳም የህ.ወ.ሓ.ት መተኪያ ሌላ የህዝብን ጥያቄ የሚመልስ ዴሞክራሲንና የህግ የበላይነትን ሊያረጋግጥ የሚችል ዴሞክራሲያዊና ህዝባዊ ድርጅት እንዲመጣለት በመፀለይ የፀሃይን ፍልቀት ሲመኝ ረጂም አመታት አስቆጥሯል።

እነዚህ አገራቸው ከገቡ በኋላ ቀለማቸውን የቀየሩ ገንዘብና አብለጭላጭ ንብረት ባዩ ጊዜ በጥቅም የባለጉ ህወሓታውያን ደግሞ "በጠገበ ሆድ ረሃብተኛ የለም" ሆኖባቸው ነው መሰል የትግራይ ህዝብ በሙሉ፡ ልክ እነሱ ጠግበው እንደሚያድሩት ጠግቦ የሚኖር

እየመሰላቸው፤ የትግራይ ህዝብ ጥያቄው ስለተመለሰ ከህ.ወ.ሓ.ት ውጭ ሌላ ድርጅት አያስፈልገውም ወደ ሚል መደምደሚያ ነው የደረሱት።



የትግራይ ህዝብ ግን ትዕግስተኛ ስለሆነ እንጂ ህ.ወ.ሓ.ት የሚባል ድርጅት የቤተ መንግስትን በር ከረገጠ ጀምሮ አንድ ብሎ በትግራይ ህዝብ ላይ ክህደት እንደጀመረ አልሳተውም። ይሁን እንጂ "አድቅቆ የመተሩት አያንቅም፡ አብሮ የመከሩት አይከፋም" ስለሆነ ሁለት አማራጮች ይዞ ለአስር ዓመታት ከስርዓቱ ጋር ቆይቷል። በአንድ በኩል ስርዓቱን እየመከርህና እየነቀፍህ ከጉድለቶቹ እንዲታረምና ከህዝቡ ጋር እንዲወግን ማድረግ። ይህ ካልሆነ ደግሞ ከ16 ዓመት በፊት የወሰደው እርምጃ እንዲወሰድ። በዚህ በአካሄደው ፈታኝ ትዕግስት የመጀመሪያ ሓሳቡ ባለመሳካቱ ሁለተኛውን እርምጃ ለመውሰድ ተገዶ ት.ህ.ዴ.ን የሚል ድርጅት ለመመስረት ተገዶዋል።

ይህ ት.ህ.ዴ.ንን የመመሥረት እርምጃ ከተወሰደ በኋላ ግን የትግራይ መሬትንና ህዝቧን የራሱ ግዛት ብቻ አድርጎ የሚያስብ የነበረው ህ.ወ.ሃ.ት ካራ እንዳየች ዶሮ ሲንገፋገፍ ታይቷል። እንደውጤቱም በፅሁፉ መግቢያ ላይ እንደተገለፀው ት.ህ.ዴ.ን የሚለውን ትግል ላለመቀበል ፖለቲካ በሚል ቁማር ተጠቅሞ የተለያዩ ስሞችን ከመስጠት አልፎ የትግሉን ህላዌ እስከመካድ ደርሷል።

ከዚህ ኣልፎም ፍፁም ጠባቦች ናቸው ተብሎ ሌሎች ህዝቦች እንዳይከተሉት የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ት.ህ.ዴ.ን/ የሚለውን ስም የትግራይ ሓርነት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ት.ሓ.ዴ.ን/ ወደ ሚል ቀይሮ ዝርዝር ማስረጃ የሌለው ፖለቲካዊ ሽቀጥ ለማካሄድም ሞክሯል።

ቀጥሎም ይህ ሁሉ ነጎድጓዳማ ወታደራዊ ጥቃት በላዩ ላይ በዘነበበት ጊዜ የትግራይን ህዝብ የትግል ስም ላለመጥቀስና እውቅና ላለመስጠት ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2003 ዓ.ም በተከታታይ በሠራዊቱ ላይ የወረደውን ቅጣት ዋጥ አድርጎት ተኝቷል። በህዝብ ዘንድ ደግሞ "ይህች ዝምታ እንከን አላት" የሚል ሃሳብ ሊነሳ ችሏል።



ህ.ወ.ሃ.ት ግን የትግራይን ህዝብ ትግል ውስጥ ለውስጥ ለማፍረስና ለማዳከም በጆሌዎቹ በኩል ከልደታችን ጀምሮ እስካሁን ማለቂያ የሌላቸው እንቅፋቶች ለመፍጠር ሞክሯል። ሆኖም ግን ሙከራው ባሳደገው ህዝብ ላይ ስለነበር ስኬታማ ሙከራ ሊሆንለት አልቻለም። እንዲያውም በግልባጩ ብዙ ነገሮች ከስሯል።

ትግል ሲባል ግን ብዙ ውጣ ውረዶችን የሚጠይቅ፣ ታጋይ ሲሰዋ ሌላ ታጋይ ሲተካ፣ ትግል በተሞክሮ መገንባት የትግል ባህርይ ስለሆነ፤ ት.ህ.ዴ.ንም ሁሉንም እነዚህን ፈተናዎች

አስተናግዷቸዋል። ለምሳሌ ጎላ ያለች የድርጅታችን የትግል እንከን ሙከራ የምንላት በ2007 ዓ.ም መጨረሻ አንዳንድ አሞታቸው የፈሰሰ፣ የታጠቁትን ትጥቅ የፈቱ የትግል አፈግፋጊዎች ከት.ህ.ዴ.ን የትግል ማዕድ ከድተው ከአዞ ምህረት ጠይቀው ነበር።

ይህ ክስተት ደግሞ ሁለት ታላላቅ ፖለቲካዊ ፍፃሜዎች አስተናግዷል። በአንድ በኩል የትግራይን ህዝብ የትግል ህላዌ እውቅና ላለመስጠት ህ.ወ.ሃ.ት ክዶት የነበረው ጉድፎች ስለተጠረጉ የትግራይ ህዝብ ትግል ያበቃ መስሎት፣ ለዚህ ክዶት የነበረውን ትግል ተቀብሎ ፈርሰው አገራቸው ገቡ በማለት ሚዲያዎችን ሲያጨናንቅ እና፣ ፀሐይ ጨለመች እያለ የቅል ከበሮ ሲደልቅ ታይቷል። "የሉም ይባል አልነበረም ወይ ዛሬ ታዲያ ከየት መጡ" የሚል የህዝብና የአንዳንድ ፖለቲከኞች ጥያቄ ግን መልስ አላገኘለትም። የወሰደው አማራጭ ቢኖር ስለ ት.ህ.ዴ.ን የጀመረውን የማጥቆር ንግግር ማቆም ብቻ ነበር።



በሌላ በኩል ደግሞ ውጤት የሌለው ደመና ሲጠረግ ያች ፀሃይ ደመቀች። በት.ህ.ዴ.ን በረት የዴሞክራሲ ማዕድ ሰፋ። መመካከር መጣ፣ ከተሞክሮ እንደተረጋገጠው ደግሞ ት.ህ.ዴ.ን ፈተና ባጋጠመው ቁጥር ኃይሎ የሚወጣ ድርጅት እንደሆነ ዳግም አረጋግጧል።

ጠላት ደክመዋል፣ ይጨልምባቸዋል፣ መሬት ከድታቸዋለች እያለ ሲዘምር እኛ ደግሞ ግዜ ሰጥተን በጥልቀት መክረንና ተነጋግረን ወደ አንድ ስኬታማ መድረክ ደረስን። ከነሐሴ 28 ቀን እስከ ጳጉሜ 04 ቀን 2008 ዓ.ም ጠላቶቻችን ያልጠበቁት ስኬታማ የፀዳና ፍፁም ዴሞክራሲያዊ የሆነ ሁለተኛ ድርጅታዊ ጉባኤያችንን በማካሄድ በድል አጠናቀናል። ጨለመች እያሏት የነበሩት ድርጅታችን ደግሞ በልጆቿ ጽናት ኮለል ብላ ደመቀች። "ጠለቀች እያሏት የፈለቀች ፀሐይ" ያልነው በዚህ ነው።

ስለኛ ትንፍሽ ብለው የማያውቁት የጠላት ሚዲያዎች አንዳንድ ከዳተኞች በሸሹበት ግዜ 24 ሰዓት በትግላችን አስመልክተው አበቃላት እያሉ ዘመሩ። የአለምን ማህበረሰብ ለማደናገር ታጥቀው አጭበረበሩ። የሚገርመው ግን መስመራችንን አቃንተን ጉድፋችንን ጠርገን ስኬታማ የሆነ የጉባኤ መድረክ ባካሄድንበት ጊዜ፣ ስለ ድላችን መናገር ይቅርና ሆዳችንን አመመን ብለው እንኳን ትንፍሽ አላሉም።

ምክንያቱም በዚህ ፅሁፍ መግቢያ እንደነካነው "ድሃ የልቡን ያኸልማል" ስለሆነ ፍላጎታቸው ውድቀታችን ስለነበር፣ ስለ ህልማቸው እንጂ ስለእውነት ለመናገር ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት የላቸውም። ይህ ግን ስርዓቱ የስልጣን እድሜውን ለማስረዘም የሚጠቀምበት ፖለቲካዊ ቀልድ ስለሆነ ብዙ አያስገርምም።

ክብርና ሞገስ ቀድመው ስለዚህ ህዝባዊ ትግል ህይወታቸውን የሰጡ የዚህ ትግል ጀማሪዎች ይሁንና የት.ህ.ዴ.ን ድርጅት በማንኛውም ዓይነት እንቅፋት ሊነቃነቅም ይሁን ወደ ኋላ ሊመለስ በማይችል ፅኑ መሰረት ነው የመሰረቱት። እነሆ ደግሞ ጨለመች ሲሏት እየፈለቀች፣ ደከመ ሲሉት ጡንቻው እየበረታ የታጋይ ድርጅቶች መሪ ለመሆን በቅቷል።



ይህ ከነሐሴ 28 ቀን እስከ ጳጉሜ 4 ቀን 2008 ዓ.ም ያካሄድነው ሁለተኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችን ፅኑ መሰረታችንን ለማያውቁ ወገኖች መበታተኛ እነደሚሆን ነበር አመላክተውት የነበረው። ጉባኤያችን ግን መሳያችን ሆኖ ምቹ መንገድ በመጥረግ መጭ ድላችን በቅርብ ወደ ምናይበት ፅኑ መድረክ አሸጋግሮናል። በወቅቱ የአማራጭ ኮሚቴው ፕሬዚደንት ሆኖ ጉባኤውን በብርታትና በንቃት የመራው ወደ ት.ህ.ዴ.ን ከመሰለፉ በፊት በህ.ወ.ሃ.ት አስተዳዳሪና አስመራጭ ኮሚቴ የነበረ ታጋይ ዓለም ካህሣይ ሁኔታውን እንደዚህ ሲል ገልፆት ነበር፦

"እኔ የህ.ወ.ሃ.ት አባል ሆኘ አስተዳዳሪ በነበርኩበት ወቅት፣ ብዙ ምርጫዎች አይቻለሁ። አስመራጭ ሁኜም ሰርቻለሁ፣ በህ.ወ.ሃ.ት ምርጫ ወደድህም ጠላህም አድርግ አታድርግ ነው። የተባልከውን ነው የምታደርገው። እንደዚህ ያለ ት.ህ.ዴ.ን ድርጅት አካሄዶት እንዳለው ፍፁም ዴሞክራሲ የሆነ ነፃነትና ግልፅነት የሞላበት ምርጫ ግን አይቸም አላውቅም። ይህ ለእኔ በህይወቴ አዲስ ፍፃሜ ነው" ሲል ገልፆት ነበር።

ይህ ሊያስደንቀንና ሊያስደስተን የሚችል ነጥብ ት.ህ.ዴ.ን ድርጅት ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ማካሄዱ አይደለም፣ ት.ህ.ዴ.ን ድርጅት የሚያካሂዳቸው መድረኮች ከጊዜ ወደ ጊዜ ዴሞክራሲያዊነታቸው እየገነነና እየጎለበተ የሚሄድ መሆኑ፣ ከትናት ዛሬ ከዛሬ ደግሞ ነገ የዴሞክራሲን ቡቃያ የሚኮተኩት ድርጅት መሆኑ ነው። ነገ ደግሞ ይህ ድርጅት ከህዝቡ ጋር ሆኖ ሌላ ታምር ሊሰራ እንደሚችል ነው ተስፋ የሚያሰንቅህ።

"በሌሎች ዓይን ያለውን ጉድፍ ከመጥረግህ በፊት መጀመሪያ በዓይንህ ያለውን ጉድፍ ጥረግ" የሚል በጣም የሚመስጥ ጥቅስ አለ። የሆነ ታጋይ ደግሞ የህዝብን መብት ከማረጋገጡና ዴሞክራሲያዊ አሰራር አነግሳለሁ ብሎ መስዋእት ከመክፈሉ በፊት የሚያካሂደው ትግል ፍትሃዊነት ማረጋገጥና ዴሞክራሲያዊ ድርጅት መገንባት መቻል አለበት። የት.ህ.ዴ.ን ታጋይ ደግሞ ይህንን አባባል በተግባር ፈፅሞታል።

2ኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችንን ከምናጠናቅቅ ወዲያው 170 ቀናትን አስቆጥረናል። በእነዚህ በተመዘገቡት ቀናት ምን አፈራን ሊባል ይችል ይሆናል። በጣም ትልቁ ሂደታችን አደረጃጀታችንን ማደላደል፣ አዳዲስ ክፍሎቻችን መሠረት እንዲይዙና፣ ነባሮቹ ደግሞ እንዲጠናከሩ ማድረግ፣ የድርጅታችንን መረጃና መሃንዲስ ወታደራዊ ሳይንስ እንዲታጠቁ ማድረግ፣ ግንባሮቻችን የሚሰሩበትን ቦታዎች በግልፅ እንዲያውቁ ማድረግና በመሳሰሉት ከባድ ሥራዎች ነው ተጠምደን የቆየነው።



ትግል የሚጠይቃቸውን ጥንቃቄዎች የማያውቁ ጥቂቶች እስካሁን ዘገያችሁ ሊሉን ይችላሉ። እኛ ግን ለሁሉም በጥበብ ቃኝተን የድል ዜናዎችን ልናበስርበት በምንችልበት ጫፍ ምሽጋችንን አንጥፈን አፈሙዛችንን አቅንተን ጠፍተዋል ላሉን ጠላቶች በሙቀታችን ልናቃጥላቸው ምላሳቸውን ልናጥፋቸው እጅ በቃታ ደርሰናል። ይህ ደግሞ ሞታችንን ለሚመኙት የፀሃያችንን መጥለቅ ለሚጠባበቁ ጠላቶቻችን በግልባጩ ሁለት ሞት ነው።

ህዝባችን በታሪክ አሸናፊነት እንጂ ድክመትንና መበታተንን የሚያስተምረን ሃረግ ይሁን አንቀፅ የለውም። የትግራይ ህዝብ የጀመረው ትግል ሁሉም የአገራችን ህዝቦች ተጨምረውበት ምንጊዜም አሸናፊ ነው። የዛሬ ትውልድስ የማን ልጅ ሆነና ነው ታሪክ ያደፈርሳል ብላችሁ ልታስቡ የቻላችሁ። ስለዚህ ይህ በከባድ የትግል መሰናክሎች እየተፈተነ እየተሳለ የ16 ዓመታት ርቀት ተጉዞ ያለው የት.ህ.ዴ.ን ትግል አሸናፊ ትግል እንደሆነ ከ2ኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችን በላይ ማረጋገጫ የለም።

የተከበራችሁ የብስራት መፅሄት አንባቢዎች ይህ አንስተነው ያለነውን ፅሁፍ በ2ኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችን በቀረበው የአቋም መግለጫና ውሣኔዎች አንስተን እናጠናቀው፦

## በት.ህ.ዴ.ን ድርጅት 2ኛው መደበኛ ጉባኤ መጠናቀቅ ምክንያት የተሠጠ ድርጅታዊ መግለጫ!!

ክቡራትና ክቡራን ተሳታፊ የትህዴን ታጋዮች፡ ድርጅታችን ባለፉት ዓመታት የትግል ጉዟችን ከባድና ፈታኝ መሰናክሎች እያጋጠሙት የመጡ ሆኖ ይህ በትግል ሂደት ሊያጋጥመው የሚችል መሰናክሎች ደግሞ የተለመደና ሊቀጥል የሚችል መሆኑን አምነን በታጋያችን ፅናትና ራስ ተነሳሽነት ከትግላችን መስመር ሳንወጣ እየመከትነው መጥተናል።

ይህ ባለፈው አመት መጨረሻ ያጋጠመን በጣት የሚቆጠሩ ከሃዲዎች የተሴረ ድርጅታችንን የማፍረስ አደጋ ከባድ የነበረ ቢሆንም እንኳ፡ ሁልጊዜ ህዝባዊ መስመር አሸናፊ ስለሆነ እነሆ ያጋጠመንን ሁኔታ በፅናት ተሻግረን ለዚህ በሞቀ መንፈስ እየተጠናቀቀ ያለውን 2ኛው ታሪካዊ ድርጅታዊ ጉባኤያችን ለማካሄድ በቅተናል። በዚህ አጋጣሚ በጉጉት እየጠበቀን ያለውን ጭቁን ህዝባችን፣ ለጀግኖች የት.ህ.ዴ.ን ታጋዮች፣ ለድርጅታችን ደጋፊ ማህበር አባላት፣ ለትግላችን ወዳጆችና ለደጋፊዎቻችን እንኳን ደስ አላችሁ እንኳን ደስ ያለን ስንል ከፍ ያለ ደስታና ኩራት ይሰማናል።



በዚህ ባካሄድነው ስኬታማ 2ኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችን የነበረንን አሉታዊና አወንታዊ ጎኖች በጥልቀት በመፈተሽና በመገምገም፡ አወንታዊ ጎኖቻችንን በማጠናከር ድክመቶቻችንን ደግሞ ለይተን ወደ አወንታዊ ጥቅሞቻችን በመቀየር፡ ለዚህ ለ25 ዓመታት በህዝባችን ትክሻ ላይ ቸ ፈረሴ እያለ ያለውን ጨቋኝ ስርዓት ለማስወገድ በሚካሄደው ትግል ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ታጋይ ወንድሞቻችን ጋር በመተባበር መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት ተዘጋጅተን እንዳለን እየገለፅን እነዚህ ከዚህ በታች ቀጥለው ያሉትን ውሳኔዎችና ደንቦች በዚህ ስኬታማና ታሪካዊ 2ኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችን እናስተላልፋለን።

## ውሣኔዎችና ደንቦች

1) የወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግን ስርዓት ሙሉ በሙሉ በመደምሰስ የብሔር ብሔረሰቦችን እኩልነትና አንድነት የተከበረባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት የጀመርነውን የትጥቅ ትግል አጠናክረን የምንቀጥልበት መሆናችንን ደግመን እናረጋግጣለን።
2) ወያኔ እየተከተለው የመጣው አውዳሚና ፀረ ሰላም ፖሊሲ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየባሰ በዚህ ልክ ደግሞ በህዝባችን ላይ እያወረደው ያለው በደልና ስቃይ እየበረታ በመሄድ ላይ በመሆኑ የትጥቅ ትግላችንን በማበረታታትና ወታደራዊ ስራዎቻችንን በማጠናከር ከህዝባችን ጎን የምንቆም መሆናችንን እናረጋግጣለን።
3) ስርዓቱ እየፈጠረ ያለውን በኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች መካከል ቂምና ጥላቻን በመጫር የማይድን ቁስል፡ በመላው ህዝቦች ትግል ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማስወገድ የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ የኢትዮጵያ ህዝቦች የትግል መሪ ሆኖ የሚቀጥል መሆኑን ያረጋግጣል።
4) ይህ በአሁኑ ወቅት በአገራችን ተከስቶ ያለው ድርቅና ቸነፈር በስርዓቱ የተዛባ የፖሊሲ አቅጣጫ የተፈጠረ መሆኑን በማመን ይህ ሁኔታ እንዳይቀጥል ለዚህ ፀረ ህዝብ ስርዓት ለመቀየር የድርሻችንን የምናበረክት መሆናችንን እናረጋግጣለን።

5) ህዝባችን በወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ካድሬዎችና አመራሮች የመናገር፣ የመፃፍና የመቃወም መብቶችን ታፍኖ የእስራትና የሞት ሰለባ ሆኖ ስላለ የህዝባችንን ተጨቋኝነት ለማጋለጥ አስፈላጊ የቅስቀሳ ስራችንን አጠናክረን የምንቀጥልበት መሆናችንን እናረጋግጣለን።
6) በዚህ በቅርቡ ወቅት በጋምቤላ ክልል ስርዓቱ ለህዝቡ የማይጨነቅና የማይጠብቅ መሆኑን ያረጋገጠ በውጭ ሃይሎች በዜጎቻችን ላይ የተፈፀመውን ኢ-ሰብዓዊ ጭፍጨፋና እገታ በጥብቅ እናወግዛለን።
7) በዚህ አመት በኦሮምያ ክልል የተጀመረውና አሁንም በተለያየ መልኩ በክልሎች በትግራይ፣ አዲስ አበባ፣ አማራና ሌሎችም ክልሎች እየቀጠለ የሚገኝ ህዝባዊ ተቃውሞ፣ በስርዓቱ የተፈፀሙ በሺዎች የሚቆጠሩ የዜጎቻችንን ህይወት የተቀጠፈበትን ተግባርና ሺዎችን ደግሞ በእስራት እንዲሰቃዩ ያደረገውን ተግባር በጥብቅ እንኮንናለን።
8) በወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ እቅፍ ሆኖ በሰላማዊ ፖለቲካዊ ትግል ለውጥ አመጣለሁ፣ የኢትዮጵያን ህዝብ ችግር እፈታለሁ ብሎ ማሰብ እራስንና ህዝብን ወደ ከፋ ችግር ውስጥ ከመክተት አልፎ ሌላ የሚያመጣው መፍትሄ እንደሌለ በማመን ሁሉም የአገር ጉዳይ ይመለከተኛል የሚል በጎናችን በመሰለፍ አማራጭ በሌለው የትጥቅ ትግላችን እንዲቀላቀል ጥሪያችንን እናቀርባለን።
9) ድርጅታችን ለዚህ በአሁኑ ወቅት በአገራችን ተፈጥሮ ላለው ቅልውላው ዋና ተጠያቂው በወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የሚመራው ፀረ ህዝብ ስርዓት መሆኑን እየገለፅን በማንኛውም አካልና በማንኛውም መልክ የትግራይን ህዝብ በአገራችን ካለው ስርዓት ጋር አያይዞ የሚኮንንና በትግራይ ህዝብ ላይ ያነጣጠረ ቅስቀሳና እንቅስቃሴ አጥብቀን በመቃወም ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነቱን አጠናክሮ በጨቋኙና ከፋፋዩ ስርዓት ላይ እንዲነሳ ጥሪያችንን እናቀርባለን።
10) የኢትዮጵያ ህዝብ የታገለላቸውን አላማዎች በመክዳት በግል ጥቅሙ የተዘፈቀውን ስርዓት ለማስወገድ እያካሄድነው ባለነው የትጥቅ ትግል በአገር ውስጥና በውጭ

የሚኖር ህዝባችን አቅሙ የፈቀደውን ሁለንተናዊ አገዝ እንዲያበረክት ጥሪያችንን እናቀርባለን።

11) ህዝባችን የትግራይ ህዝብ ይህ በስልጣን ላይ ያለው ከሃዲ ወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ስርዓት ነገ በመላው የኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚደመሰስ መሆኑን አምኖ ከሌሎች ጭቁን የኢትዮጵያ ህዝቦች ወገኖቹ ጋር ትግሉን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ እናቀርባለን።

12) ሁላችሁም የወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የፀጥታ መዋቅሮችና ካድሬዎች በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ያለው ስርዓት ኗሪ አለመሆኑን አምናችሁ የስርዓቱ ተላላኪ በመሆን በህዝባችሁ ላይ እያካሄዳችሁት ያላችሁትን ኢ-ሰብዓዊ ጭፍጨፋ አቁማችሁ ከህዝባችሁ ጎን እንድትቆሙና የዚህን ፀረ ህዝብ ስርዓት እድሜ በማሳጠር የድርሻችሁን እንድትወጡ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

13) ት.ህ.ዴ.ን ከሁሉም የወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግን ስርዓት ከሚታገሉ በኢትዮጵያ አንድነት ከሚያምኑ ዴሞክራሲያውያን ድርጅቶች ጋር አብሮ ለመስራት ዝግጁ መሆኑን ደግሞ ያረጋግጣል።
14) በወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሪዎች ያልተመለሱ የትግራይ ህዝብና የመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጥያቄዎችን ለመመለስና የሰማዕታቶችን አደራ ከግቡ ለማድረስ በዚህ በ2ኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችን ቃላችንን እናድሳለን።
15) ሁሉንም የ2ኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችን እቅዶች ለማሳካት የት.ህ.ዴ.ን አመራሮችና አባላት በርትተን እንረባረባለን።

16) በመጨረሻ የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ት.ህ.ዴ.ን) ህዝባችንና አገራችንን ከዚህ አሁን ገብተውበት ካሉት ቀውስ ለማዳን እንዲቻል፣ ለዚህ ፀረ ሰላምና እድገት የሆነን ወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ስርዓት በማስወገድ ካለፈው በበረታ መልኩ የሚሰራ መሆኑን እያረጋገጠ ለጭቁን ህዝባችን 2009 ዓ.ም የሰላምና የብልፅግና አመት እንዲሆንላቸው መልካም ምኞቱን ይገልፃል።

ዘላለማዊ ክብርና ሞገስ ለጀግኖች ሰማዕቶቻችን
ድል ለጭቁኖች
ት.ህ.ዴ.ን ጳጉሜ 4 ቀን 2008 ዓ.ም

## ከታጋይ ይብራህ በርሄ ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቅ!!

ብስራት መፅሄት፦ የት.ህ.ዴ.ን ምክትል ሊቀ-መንበር ታጋይ ይብራህ በርሄ ለዚህ ቃለ-መጠይቅ ፈቃደኛ ሆነህ እዚህ በመገኘትህ በብስራት መፅሄት አንባቢዎች ስም ላመሰግንህ እወዳላሁ። በቀጥታ ወደ ጥያቄዎቼ ስገባ ደግሞ የት.ህ.ዴ.ን ድርጅት ከነሐሴ 28 ቀን እስከ ጳጉሜ 04 ቀን 2008 ዓ.ም ባካሄደው 2ኛው ድርጅታዊ ጉባኤ በርከት ያሉ ውሳኔዎችን አሳልፏል። ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ የትጥቅና ፖለቲካዊ ትግልን ማጠናከር፣ በሌላ በኩል ደግሞ በኢትዮጵያ አንድነት ከሚያምኑ ድርጅቶች ጋር አብሮ መስራት፣ አብሮ መታገል የሚል ይገኙበታል። ይህ ምን ማለት ነው?

*ታጋይ ይብራህ በርሄ፦ በመጀመሪያ እኔም የብስራት መፅሄት እንግዳ እንድሆን ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ። ወደ ጥያቄው ስገባ የትጥቅና ፖለቲካዊ ትግልን አጠናክሮ መቀጠል የሚለው በትክክል እስከአሁን ተጠናክሮ እየቀጠለ አልነበረም ማለት አይደለም። ይሁን እንጂ አሁን እየታየ ካለው የእድገት ደረጃ ጋር የህዝቡ የተቋቋሚነትና ታጋሽነት መንፈስ ያበቃበትና፡ የስርዓቱ ውስጣዊ አስተዳደር የተበላሸበት ሁኔታ ላይ ሆነን ያካሄድነው የድርጅታዊ ጉባኤ ቃል ስለሆነ፡ ይህ ደግሞ ከማንኛውም ጊዜ በላይ የለውጥ ሃይሎች ውህደት፣ የሁሉም ታጋይ ኢትዮጵያውያን ውህደት ወሳኝ መሆኑን ለመግለፅ ያለመ ነው።*



*ምክንያቱም በዚህ ሰዓት ህዝባችን የስርዓቱን በደሎች ሊታገስ በማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡ ስለዚህ በፖለቲካዊ መደረግ የሚገባው ህዝብን የማደራጀትና የማነቃቃት፤ በትጥቃዊ መደረግ የሚገባው ደግሞ ለፖለቲካው ድጋፍ በቀጣይነት የሚደረግ የግፊት አሰራር ከማንኛውም ጊዜ በላይ መጠናከር አለበት ማለት ነው። ሌላ ከሌሎች በኢትዮጵያ አንድነት ከሚያምኑ ሃይሎች ጋር ተባብሮ መስራት የሚለው ነገርም ምናልባት ባለፉት ጊዜያት እያየነው እንደመጣነው ጥቂት አይደለም። ፍላጎት አለ፣ ጉጉት አለ፣ ሙከራዎች አሉ። ይሁን እንጂ ተጨባጭ ውጤት መጧል ተብሎ የሚገለፅ ነገር አይደለም። እኛ ለአንዲት ኢትዮጵያ የምንታገል ኃይሎች ከሆነ የሚለያየን ነገር የለም። ምናልባት የሚለያዩን ጠባብ ነገሮች ሊኖሩ ይችሉ ይሆናል እነዚህን በማጥበብ በይበልጥ ልንጣመር የሚገባን ጊዜ አሁን ነው የሚል ነው መልእክቱ።*

***ብስራት መፅሄት፦ እስከአሁን የተካሄደው ሂደቶች ወይም ደግሞ እነዚህን የዚህ ድርጅት ውሳኔዎች ተግባራዊ ለማድረግ የተሄደው ርቀትስ የት ደርሷል ልንል እንችላለን?***

*ታጋይ ይብራህ በርሄ፦ ጉባኤ ከምናካሂድ ረጅም ርቀት አልሄድንም ጊዜው አጭር ነው። አጀማመሩ፣ እቅድ ተነድፏል፣ ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት ሊያሰራን የሚችል መስመር ተነድፏል። ሰፊ የሆነ እንቅስቃሴ ነው እያካሄድን ያለነው። የነበሩትን ደካማ ጎኖች አስወግደን ብልጫዎቻችንና ፀጋዎቻችንን ልንጠቀምባቸው በምንችልበት ጫፍ ላይ ደርሰናል። እነዚያ ውጤታማ ያልሆኑ ወይም እንቅፋቶቻችን የነበሩ የትኞች ናቸው የሚል ግምገማ በማድረግ ከተለያዩ የለውጥ ሃይሎች ከሚባሉት ኢትዮጵያውያን ታጋይ ድርጅቶች አመራሮች ጋር ብዙ ግምገማዎችንና የሃሳብ ልውውጥ በማድረግ ድክመቶቻችንና ጠባብ ልዩነቶቻችንን አስወግደን ወደ አንድ ልንመጣ የምንችልበት በይበልጥ ልንጣመር የምንችልበት ገፅታና ጥሩ መረዳዳት እየተደረገ ስላለ እንዳለፉት ፍላጎት ብቻ ሆኖ የሚተርፍ ሳይሆን ይበልጥ ተጣምረን ልንሰራበት የሚገባን ቦታ በማንጠፍ ላይ ነው ያለን።*



***ብስራት መፅሄት፦ ት.ህ.ዴ.ን በደማቅ ወታደራዊ ድሎች ነው የሚታወቅ በተለይ በትግራይ የተለያዩ ቦታዎች በስርዓቱ አረመኔ***

**ወታደሮች ላይ ብዙ ጥቃቶችን አድርሷል ት.ህ.ዴ.ን። በዚህ ቅርብ ግዝያት ግን ስለምንድን ነው ወታደራዊ ማጥቃቶች መቀዝቀዝ የቻለው የሚሉ ወገኖች አሉ ለእነዚህ ምን መልስ አለህ?**

*ታጋይ ይብራህ በርሄ፦* ይህ አባባል በጎን ሆነው ለሚመለከቱ ወገኖች ትክክል ነው ልትል ትችላለህ። ይሁን እንጂ ት.ህ.ዴ.ን በዚህ ጊዜ ስልቶቹን በመቀየር እያጠቃ እንዳለ ከማንም የተደበቀ አይደለም። ለምን ካልን ምናልባት ከ1996 ዓ.ም ጀምረህ ከህዝብ ጋር በመገናኘት ተፅዕኖ መጀመር ከጠላት የመከላከል ሃይል መነካካትና መጋጨት ከሚጀምር እስከ 2003 ዓ.ም ያለማቋረጥ እየተጋጨ ቆይቷል። በመጨረሻ እኛ የምንፈልገው እኮ ሁልጊዜ እሩምታ መተኮስ ሳይሆን ለውጥ ማምጣት ነው። ለውጡ ሊመጣ ከሆነ ደግሞ ጠላቶቻችን የሚደክሙበት እኛ ደግሞ ልንጠንክርበት በምንችልበት መንገድ ህዝባችንን ልናደራጀው ጠላቶቻችን ከህዝብ እንዲነጠሉ በሚችሉበት መንገድ መስራት ስላለብን ይህ ወታደራዊ ስራት ወይም ደግሞ ደማቅ ድሎች እያልከው ያለኸው መልኩን ቀይሮ ነው እየተሰራበት ያለው እንጂ ስራው አልቆመም።



ከ2003 ዓ.ም በኋላ ላለው ከመጣህ ደግሞ ት.ህ.ዴ.ን እንደ ድርጅት በትግራይ ህዝብ ውስጥ ሰፊ የሆነና ጥልቀት ያለው መሰረት አንጥፏል። እንደውጤቱ ደግሞ በሁሉም አካባቢዎች በስርዓቱ ላይ የሚደረጉ ተቃውሞዎች የት.ህ.ዴ.ን ውጤቶች ናቸው። ማጥቃቱ መልኩን ቀይሮ ርቀቱንም ቀይሮ እየሰራ ነው እንጂ የቆመ አይደለም። ስለዚህ ሁሉም የአሰራራችን ዘዴ ስንገመግም በሚያዋጣን መንገድ እንድንሄድ የግድ ስለሆነ። እንደ ድርጅቱ አመራርነት ይህንን ገምግሞና አይቶ ለቀጣይ በይበልጥ በህዝባችን ውስጥ ሊያስገባን የሚችል መስመር የስራ ለውጥ አድርጎ እየሰራ እንዳለ ነው ልገልጥላቸው የምፈልገው።

**ብስራት መፅሄት፦ የት.ህ.ዴ.ን ድርጅት ከህዝብ ወጥቶ ለህዝብ የሚታገል ህዝባዊ ድርጅት ነው ብለነዋል። ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ት.ህ.ዴ.ን እስከ ምንድረስ ነው በኢትዮጵያ ህዝብ ልብ የገባው ከጫፍ እስከ ጫፍ በኢትዮጵያ ህዝብ ገብቶ ታዋቂነትና ተቀባይነት የህዝብን ድጋፍ እስከምን ድረስ ያገኛል?**

*ታጋይ ይብራህ በርሄ፦* ት.ህ.ዴ.ን በዚህ ጊዜ ከባድ ፈተና ነው ያለው። በፈተና ላይ ያለ ድርጅት ነው። ስለምን ካልህ የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ለትግራይ ህዝብ ወክሎ የወጣ ድርጅት ነው። የትግራይ ህዝብ በዚህ ሰዓት በመላ አገራችን ያለውን ለዚህች እየወደቅንላት ያለነው የተፈጠረባት አገር እንዳልተፈጠረ፣ እንደ አንድ ልዩ ገዥ፣ እንደ አንድ ወራሪ እየታየ ያለው፣ እንደ አንድ ገዳይ እየታየ ያለበት ጊዜ ነው የምንገኘው። ስለዚህ ይህ የዚህ ድርጅት አመራር ወይም ድርጅቱ ምንድነው የሚጠብቀው በዚህ ጊዜ እኛ ስንታገል ለውጥ እናመጣለን ብለን ነው እየታገልን ያለነው፣ እየታገልንበት ያለነው አላማ ለውጥ ሊያመጣ ከሆነ ደግሞ መስራት አለበት። ሊሰራ ከሆነ ደግሞ ምናልባት ሊሰራቸው የሚገባቸውን ነገሮች ነው ማቀድ የሚገባው። ምን ልልህ ፈልጌ ነው ምን ያህል ነው በኢትዮጵያ ህዝብ ልብ የገባው ብለኸኝ ገብቷል ገና እንዲገባም ስራ የሚያስፈልገው ነው ጥቂት የማይባል ርቀትም ገብቷል።

ቢያንስ ቢያንስ የትግራይ ህዝብ ልክ እንደሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች የተበደለ ህዝብ እየተረገጠ ያለ ህዝብ፣ እንዲያውም ከማንም በላይ እየተገፋ ያለ ህዝብ መሆኑ የታፈነ፣

የተረገጠ ህዝብ መሆኑን ለማሳየት ፈትኗል። ከዚህ በፊት ለትግራዋይ እንደ አንድ ጠላት እንደ አንድ ፀረ ህዝብና ሃገር አድርገው መልዕክት ያስተላልፉ የነበሩት ፕሮፓጋንዳዊ ስራዎቻቸውን ያካሂዱ የነበሩት፣ ተገልብጠው በአሁኑ ጊዜ ያለፈውን ስህተት በማረም የትግራይ ህዝብ ልክ እንደ ሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚታገለው ለውጥ የሚፈልግ ህዝብ የጭቆና ቀንበር ተጭኖት ያለ ህዝብ ነው ለማለት ችለዋል። ይህ ማለት ይህ ድርጅት በተወሰነ ርቀት በኢትዮጵያ ህዝብ ልብ ገብተዋል። እንደዚህ ባይሆን ኖሮ የትግራይ ህዝብ እንደቀደሙ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ በተነጠለ፣ ቢያንስ ቢያንስ በዚህ ሰዓት ግን የትግራይ ህዝብ እየተበደለ ነው ያለው በማለት ቆም ብለህ የማሰብ መድረክም ደርሷል የኢትዮጵያ ህዝብ። ይህ ድርጅት በንቅናቄው ያመጣው ለውጥ ነው። ለኢትዮጵያ ህዝብ ሙሉ በሙሉ



የትግራይ ህዝብ የተበደለ መሆኑን አስረድቷል ወይ ካልከኝ ግን በፍፁም ገና አሁንም ያልተሰራ የቤት ስራ አለን ባይ ነኝ።

**ብስራት መፅሄት ፦ በዚህ በቅርብ ግዜያት በሰፊ መንገድ ህዝብና መንግስት በጣም ተነጣጥለው ህዝብ በስርዓቱ ላይ ሆ ብሎ ተነስቶ በጋራ ድምፁን የሚያሰማበትና የሚቃወምበት ዓመፅ ያስነሳበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ይህ ህዝባዊ አመፅ መነሻው ምንድን ነው?**

ታጋይ ይብራህ በርሄ፦ አዲስ እኮ አይደለም የቆየ ነው። የቆየ ስልህ በየደረጃው ከጊዜ ወደ ጊዜ መጀመሪያ ስህተት ሲፈጠር ችግር ሲታይ ይህ ስህተት ለምን ታየ ለምን እንደዚህ ተፈጠረ ይባላል። የማያድን መድሃኒት ይደረግለታል ዘግይቶም በተመሳሳይ ይቀጥላል በየጊዜው እየተደናገረ ግን ደግሞ ስሜቱን እየዋጠ የመጣ ህዝብ ነው። ማደናገር ሲበዛበት መቋቋም ሲከፋው ሊታገሰው በማይችል ደረጃ ሲደርስ ስሜቱን በደሉን ግፉን ህይወቱን ከፍሎ ሊያስተካክል የግድ ነው። በዚህ ህዝባዊ ማዕበል ብዙ ጭፍጨፋ ተካሂዷል። ብዙ ህዝብ ረግፏል። ህዝብ ሲረግፍ እኮ መኖር ስለጠላ የመሞት ፍላጎት ስላለው አይደለም ህይወቱን የከፈለ። የመጭ ህይወቱን ማስተካከል ስላለበት ነው። የተወሰነው ክፍል ህይወትህን ከፍለህ የተረፈው ህይወት እንድያስተካክል በሚል ነው የዚህ ብርቱ ተቃውሞ መነሻ።

ስለዚህ ከመጀመሪያ ይህ ስርዓት ሲመጣ ጀምሮ እስካሁን በላዩ ላይ እየተፈፀመ የመጣውን በደል እንደ መፍትሄ ተብሎ እየቀረበ ታሐድሶ ይባላል። ግምገማ ይባላል ብዙ ብዙ ነገር ነው። እነሱም የገዛ ራሳቸው በደል ፈፅመው እየሄዱ ልክ አዝማሪ በወንዝ አፋፍ ላይ ሆኖ እንደሚጫወት። ሰው ከኋላው መጥቶ "ምን እያደረግህ ነው አለው። ይሄ የውሃ



ሙላት ካሳለፈኝ ብየ እየዘመርኩለት ነው ብሎ አወደሰው፣ ታዲያ የሰማው ያልፋል ያልሰማው ይመጣል ሊያሳልፍህ አይችልም" አለው ይባላል። አዝማሪው ምንድን ነው ማድረግ ያለበት የሚችለው ከሆነ በጉልበቱ ጥሶት መሻገር አለበት ካልሆነ ደግሞ ማሲንቆውን አጥፎ ወደ ቤቱ መሄድ አለበት ማለት ነው። በሌላ አባባል ወደ ኋላ መመለስ አለበት።

ስለዚህ የትግራይ ህዝብም ይሁን የኢትዮጵያ ህዝብ በአጠቃላይ አንዱን ሲረግም አንዱ ይመጣል። አንዱን ይረግማል ሌላ

*ይመጣል። አንዱ በልቶ ይሄዳል ሌላው ይተካል። እሱ ሲጠግብ ሌላ ይመጣል። ጠቅልሎ ሊድን የማይፈወስ ችግር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተደራረበ ስለመጣበት ይህንን ለመፍታት ደግሞ አቤት ብሎ መፍትሄ ስላላገኘ በመጨረሻ ያለው አማራጭ አንድና አንድ ብቻ መሆኑን አውቆ ህይወቱን ከፍሎ የሌሎችን ትውልድ ህይወት ማዳን ነው። ስለዚህ የተጠራቀመ ትዕዝብትና የተጠራቀመ ምሬት የስርዓቱ የተዳበለ ክፋት በህዝቡ ላይ የፈጠረው ንዴት ነው የአመፁ መነሻ። ይህ ደግሞ ወደደም ጠላም ስርዓቱ ካልተቀየረ ሊገታ አይችልም።*

***ብስራት መፅሄት፦ ተነስቶ የነበረው ህዝባዊ ዓመፅ ለመቆጣጠር የተወሰዱ የተለያዩ እርምጃዎች አሉ። መጀመሪያ በጠመንጃ ሃይል በመጨፍጨፍ ለማስቆም ሞክረው አልሆነላቸውም። የተለያዩ ጉባኤዎችና ኮንፈረንሶች ተካሂደው የመጣ ለውጥ የለም። በመጨረሻ ደግሞ የስድስት ወር የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ነው ያወጁ። አስከትለውም የሚኒስትሮች ማቀያየር አካሂደዋል። ስለዚህ በዚህ ሂደት ምንያህል ለውጥ ይመጣል ብለህ ታስባለህ?***

*ታጋይ ይብራህ በርሄ፦ ምናልባት ይህ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እየተባለ ያለው*



*አስቀድሞ ማለቂያ የሌለው ጭፍጨፋ ነው የተካሄደው። በአንድ የአገር ዜጋ ነው እየተፈፀመ ያለው ብለህ ልትቀበለው በሚያስቸግር መልኩ ከባድ ግፎች ተፈፅሟል። ህዝቡ ግን በዚህ ሊንበረከክ አልቻለም ግርፋቱ፣ እስራቱ፣ ግድያውን ሁሉንም ገጥሟል። ሰደዱ ከጫፍ እስከ ጫፍ ተቀጣጥሏል። ስርዓቱ በመጨረሻ የመፍረስ ወይም የመሸነፍ ደረጃ ላይ ደርሶ መሆኑን አምኗል። ይህ ደግሞ አገርና ስርዓት፣ ህገ-መንግስትና ህገ-መንግስታዊ ደህንነት ልንጠብቅ በምንችልበት መንገድ መሄድ አለብን የሚል ነው መሰረታዊ የወሰደው ገምጋምና ያሳለፈው ውሳኔ፡ ከዚህ ተነስቶ ነው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የመጣ። በመሰረቱ ግን ስርዓቱ የህዝብ መሰረት የሌለው ህዝባዊ ስሜት የማይረዳው መሆኑ ለግል ጥቅሙና ለግል ኑሮው ብቻ የቆመ መሆኑን ያስረዳሃል። ህዝብ ይህ ስርዓት አያስፈልገንም ከጫፍ እስከ ጫፍ አገር ሙሉ ቆሞ እያለ እናስፈልግሃለን ብለህ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፍኖ መያዝ ማለት ምን ማለት ነው።*

*የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለአገር ሙሉ የተአወጀ አዋጅ ነው። ይህ አገራዊ አዋጅ ደግሞ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ ይህን እንደዚህን ማድረግ አይፈቀድም ከተባለ አገር ሙሉ ታስሯል ማለት ነው። ስለምን? አገር አስረው የት ላይ ሊኖሩ ይፈልጋሉ? እንዴትስ ሊፈፅሙ ይፈልጋሉ መሰረታዊ ፈፅሞ ሊፈታ የማይችል ደካማ ዘላቂ መፍትሄ የማይሆን እርምጃ ነው። ለህዝብ ነው ሊያስተዳድሩ የሚገባቸው ህዝብ ካልፈለጋቸው ደግሞ መልቀቅ ብቻ ነው ያለባቸው። ህዝብ እንዴት አድርጎ ነው አገሪቱ ከዚህ ገብታበት ካለችው መስመርና ግርግር እርስ በርስ መገዳደልና መጨፋጨፍ ጅማሬዎች ማውጣት ያለበት የሚል አጋዥ ድርሻቸውን ነው መጫወት ያለባቸው እንጂ አንለቅም በግድ እንቀጥላለን የሚባል ነገር ለሃገሪቱ ፈፅሞ እንደ*



*ባለስልጣኖች ግላዊ ጥቅሞች አለመመልከት ልቅ የሆነ ሞኝነት ነው። አገርና ህዝብን ልክ እንደግል ጥቅማቸው ቢመለከቱት ኖሮ የህዝቡን ስሜት የህዝቡን ፍላጎት የህዝቡን ምሬትና ስቃይ ባዩ ነበር። ችግር ባዩ ጊዜም ከህዝባቸው ጋር ነበር መወያየት የሚገባቸው።*

*ስለዚህ ለግል ዝናቸው ሲሉ ለግል ጥቅማቸው ሲሉ ህዝቡ እንደምርጫውና በነፃ ሊኖር እንደማይችል እንደማይፈቅዱለት ከእነሱ ውጭ ፈፅሞ አገር እንደ አገር ሊኖር እንደማይችል በማመን ፈላጭ ቆራጭ ሊሆኑ ብቻ ይሞክራሉ። እነሱ በሚፈልጉት እነሱ በሚጠቀሙበት ብቻ እንዲቀጥል ይፈልጋሉ። ስለዚህ ይህ ደግሞ የማይሆን ነገር ነው። ሊሆንም አይችልም። ምናልባት አሁን ተጭኖት ያለው አፈና ህዝቡን በአንድ ወጥመድ አስገብተው አፍነውት ያሉት እኔ እንደሰው ሁሉ ሆብሎ ሁሉ ከአገሪቱ ከጫፍ እስከ ጫፍ ተነሳስቶ ከባድ መሳሪያ የታጠቀ ምህረት የሌለው ከባዕድ ተለይቶ የማይታይ አምባገነን ሃይል ጋር ገጥሞ ማለቅ አለበት አልልም። እያንዳንዱ የትግሉን ዘዴ ህዝቡ መተሳሰር አለበት። በአንድ ጫፍም ይኑር በሌላ ጫፍ ከአንድ ብሄርም ይሁን ከሌላ ብሄር ከማንኛውም ጊዜ በላይ መተሳሰር የሚገባውን መረዳዳት የሚገባው መተጋገዝ የሚገባውን ተዋህዶ ህብረታዊ ንቅናቄ ማድረግ የሚችልበት ሁኔታ ነው መፈጠር ያለበት፡ ብቻ ነው ልትል የምትችል።*

*ወደ የሚኒስትሮች መቀያየር ከመጣን ድራማ ነው። ምናልባት እኔ በሁለት ጎን ልገልፀው እፈልጋለው፡ ለምን ካልከኝ እነዚህ አሁን መጥተው ያሉት ፕሮፌሰሮች በላቸው ዶክተሮች በ2009 ዓ.ም ነው ተምረው የተመረቁት? እነሱ እስከሚመረቁ እየጠበቁ ከነበረ አንድ ነገር ነው። ጥሩ ለውጥ ያመጡልናል ብለን ልንጠብቅ እንችላለን። እነዚህ ሰዎች አገራዊ ለውጥ የአስተዳደር ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ናቸው ተብሎ ይታመንባቸው ከነበረ ስለምን እስካሁን ተቀብረው የቆዩ? ህዝብ ማማረር ከጀመረ ለውጥ ከሚጠይቅ ስንት አመት ነው ያደረገ? ለምንድን ነው በጊዜው ለውጥ ማምጣት ካልቻሉ እዚያው የነበሩትን ባለስልጣናት ሊተኳቸው ያልቻሉ ምን ሆነው ነው?*



*መጨረሻ ላይ ሊወድቁ ሲሆን ሰው አምጥቶ አምጥተንላችኋል ማለትስ በመሰረቱ እውነታው እንደዚህ ነው ወይም ደግሞ እነዚህ ሰዎች እስካሁን ት/ት ቤት ውስጥ ነው የነበሩት ካልን ጨዋታ ነው። ሸቀጥ ነው። ከእነዚህ ሰዎች ሁለት ነገር ልጠብቅ እችላለሁ እኔ እንደ ይብራህ አንድ ለየት ያለ የጭፍጨፋ ስራዎች ሊያካሂዱ ይችሉ ይሆናል የት ለማን መቼ የሚለውን ለጊዜ እንተወው።*

*በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የሆነ ለውጥ ሊያመጡ የማይችሉ ተቃኝተው ማለትም ተሞልተው በስርዓቱ ሙሌት የተሞሉ ምንም አይነት ትርጉም የሌላቸው ደካማ ሰዎች ናቸው። ስም ብቻ የያዙ ናቸው ነው ልል የምችለው። ይህ ተሰጥቷቸው ያለው የሚኒስትርነት ማዕረግና የስራ ቦታ ሊቀበሉት የማይገባቸው ቦታ ነበር። ፈፅሞ ፀሃይ በጠለቀች በተበላሸና በተጨማለቀ ማዕድ ገብተው ታሪካቸውን ሊያበላሹ አይገባቸውም ነበር። ህዝብ እየፈለገ ያለው የስርዓት ለውጥ ነው። የሰዎች ለውጥ አይደለም። ስርዓት መለወጥ አለበት እየተባለ፡ ለውጥ የሚፈልጉ አካላት ቢሆኑ ኑሮ እነዚህ ከህዝባቸው ጋር ሆነው ስርዓቱን ለውጠው የአስተዳደር ለውጥ የስርዓት ለውጥ ነው ማምጣት የሚገባቸው እንጂ የሞተውን ስርዓት ለማስነሳት እየተቀጠሩ ከሆነ እነዚህ መጥፎዎች ናቸው።*

ብስራት መፅሄት፦ በዚህ ባለፈው ህዝባዊ አመፆች ትግራዋይ ከያሉበት እየታገቱ እየተቀጠቀጡ ንብረታቸውን እየተዘረፉ ወደ ቤተሰቦቻቸው ወደ ትውልድ አገራቸው ወደ ትግራይ የተመለሱበት ሁኔታ አለ ይህ ስለምን ሊሆን ቻለ? ምናልባት ትግሬን ታርጌት ያደረገ ትግልስ ሊያሸንፍ ይችላል? የምንመኘውን ሰላምና ልማት ዴሞክራሲ ሊያመጣልን ይችላል ለምድን ነው እንደዚህ የሆነው?

ታጋይ ይብራህ በርሄ፦ ይህች ለእኔ መሰረታዊ ጥያቄ ነች። ልክ አስቀድመን ስንለው እንደቆየነው በሁለተኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችን ውሳኔዎችና ደንቦች እንዳሳለፍነው በስርዓቱ ምክንያት የተፈጠረ ችግር ነው። የስርዓቱ አስተዳደር ቅንነት ስላልነበረው አገሪቱን እንዴት አድርጎ ከፋፍሎ በየቡድኑ አደራጅቶ እንዴት አድርጌ ልጠቀምባት እችላለሁ ነው እንጂ እንዴት አድርጎ እንደ አገር ወደ አንድ ይምጣ በሚል አይደለም እየሰራ ያለው። ወይም ደግሞ እየተጠቀመበት ያለው የአስተዳደር ስርዓት ከፋፋይ ነው። እንደዚህ አይነቱ ያመጣው ምክንያት ደግሞ ስርዓቱ በፈፀማቸው ግፎች በፈፀማቸው በደሎች ሁሉ ጊዜ ከትግራይ ህዝብ ጋር ይያያዛል። እኔ የሚያሳዝነኝ ነገር ካለ እንዳይገርመህ የትናንት ታሪክ እንዳለ እየተደገመ ስላለ ብቻ ነው። እኔ አስታውሳለሁ የደርግ ስርዓት እያለ አማርኛ ተናጋሪ ከሰማህ ደርግ ይባል ነበር። ወያኔ የገዛ ራሱ ምን እያለ ይቀሰቅስ ነበር ካልከኝ በአማራ ላይ ነው እየቀሰቀሱ የሚያነሳሱ የነበረው። በዛን ወቅት ግን ድሃ፣ ጭቁን፣ የተረገጠ፣ የተወረወረ የአማራ ህዝብ ነበር። ስለሆነም ወደ ትግል ወጥቶ ታግሎ በትግሉም የበኩሉን አበርክቷል። አሁን ግን ስርዓቱ የፈጠረው ነው።

ስርዓቱ ህዝብን ይጨፈጭፋል አማርኛ ይናገራል። የአማራ ህዝብ ደግሞ እንደ ገዳይ እንደጨፍጫፊ ሰው እንደሚበላ ተደርጎ ደግሞ ይወሰዳል። ነገር ግን በዛን ጊዜ በነበረው ስርዓት በስልጣንም ይሁን በውትድርና ደረጃ በሁሉም አይነት በአስተዳደሮችም ይሁን አማራዎች ነበሩ፣ ትግሬዎች ነበሩ፣ ሌሎች ብሄሮችም ነበሩ። በጊዜው ግን አማራ ይባል ነበር። በዚህ ሰዓት ደግሞ በሚንስትሮች ይሁን በከፍተኛ የመንግስት መዋቅሮች ያሉት አገልግሎት ሰጭ ተቋማት በጠቅላላ የስርዓቱ የአስተዳደር ቦታዎች ሌሎች ብሄሮች ናቸው በብዛት ያሉ ይሁን እንጂ ትግሬ ይባላል። ምናልባት ባለፈው ጊዜ ደርግን ለማጥፋት ሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች በአማራ ህዝብ ላይ



አልተነሱም የአማራን ህዝብ በየአገኙት አጋጣሚ አልገደሉትም፣ አልጨፈጨፉትም፣ አልገፉትም፣ ወይም ያላፈናቀሉት ሊሆኑ ይችላሉ። አሁን ግን የከፋ ነው። የነበረውን ታሪክ መድገሙ ደግሞ ከሱበላይ ማባባስ ነው። በአሁኑ ወቅት ስርዓቱ በፈጠረው ችግር ሌሎች ብሄሮች በትግራይ ህዝብ ላይ ሲነሳሱ ይታያሉ ብቻ ሳይሆን ሲገድሉት፣ ሲጎዱት፣ ሲያግቱት ስትመለከት ታሪክ ተደገመ ብቻ ሳይሆን ብሷል ልትለው ትደፍራለህ።

በመሰረቱ ግን የኢትዮጵያ ህዝብ የሚፈልገው ያለው ይህንን መለያየት ነው? ይህንን እርስ በርስ መጨፋጨፍ ነው? እራስ በራስ መገዳደልን ነው? የመጭው የኢትዮጵያ ህዝብ እድልስ ምንድን ነው እንዲሆን እየተፈለገ ያለው? መሰረታዊ የሆነ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ ሊያስብበት የሚገባው ጉዳይ ነው። ሄደን ሄደን መጨረሻ ላይ የኢትዮጵያ ህዝብ መጭው ትውልድ ምንድነው እንዲሆን የሚፈለገው። እሺ አሁንስ ሌሎች የኢትዮጵያ ብሄሮች ለትግሬ ይጨፍጭፈው ስርዓቱም ይወገድ። የትግራይ ህዝብ ነገ ምንድን ነው የሚያደርገው

የትግራይ ህዝብ ኢትዮጵያዊ አይደለም ነው? ምንድነው ሊደረግ የሚፈለገው ሊታገት፣ ሊታረድ፣ ሊገደል፣ ሊሸጥ ፈፅሞ የማይቻል ነው። በተራው ደግሞ ይነሳል ሌላ ነገር ይነሳል። እሱም የመጨረሻ እየገደለ እየተገደለ ሊኖር ነው ጉድ! ይህችን አገር ምንድነው ልናደርጋት የምንፈልገው ትውልዱ ምንድን ነው መሆን ያለበት የሚል ነገር ፈፅሞ እስካሁን ትኩረት ያልተደረገበት ነገር ነው።

ስለዚህ ትግራዋይን አግልሎ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚፈልገው ለውጥ ሊመጣ ይችላል ወይ? ከተባለ ሊመጣ አይችልም እንዴት ሆኖ የትግራይ ህዝብ ያልተቀላቀለበት ትግል ፍፁም! ፍፁም! ለድል አይበቃም። ለምን ካልከኝ የትግራይ ህዝብ የራሱ ህዝባዊ ክብር አለው ማንነታዊ ክብር አለው ክብሮች አሉት ይህንን ትልቅ የሆነ ታሪክ ያለውን ህዝብ ደምስሰህ ለማን ይዘህ ነው የምታሸንፈው? ስለዚህ የትግራይ ህዝብ፣ የአማራ ህዝብ፣ የኦሮሞ ህዝብ ወዘተ እያልክ ከመከፋፈል ይልቅ ኢትዮጵያዊ መሆኑን አምኖ በኢትዮጵያ ተፈጥሮ ያለውን ችግር ደግሞ አገሪቱን እየመራ ያለው ስርዓት የፈጠረው ችግር መሆኑን አምኖ ሊገጥመው ካልቻለ ቁስሉ ዘላለም እየደማ ይኖራል። ሊድንም አይችልም።

የኢትዮጵያ ህዝብ ማሰብ ያለበት ካለ፡ መላው የኢትዮጵያ ህዝቦች የለውጡ ትግል ተሳታፊ መሆን አለበት። የሚያፈገፍግ መስሎ የሚታይ ካለም ለምሳሌ የትግራይ ንቅናቄ የጎላ አይደለም በትክክል በትግራይ ያለው ችግር ግን ባለፈው አባይ ፀሃየ ከውራይና መፅሄት ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ በተጨባጭ ገልፆታል። "የትግራይ ህዝብ ተመችቶት አይደልም ህ.ወ.ሃ.ትን አቅፎት ያለው" በትክክልም አልተመቸውም። እያስፈራሩት ካሉ ሊጎዱት የሚፈልጉ ከሆነ የትግራይ ህዝብ ምን ማድረግ አለበት? መደራጀት አለበት መከላከል አለበት።

ህ.ወ.ሃ.ት የትግራይን ህዝብ እንደ አንድ መደበቂያ ምሽግ ነው ታጥቆ ይዞት ያለው የሚል አባባል እነሱም እኮ ያምኑበታል ይረዳቸዋል እኮ ያውቁታል እኮ፡ ታዲያ ምንድነው ሊያደርጉ የሚፈልጉት ህ.ወ.ሃ.ትንና የትግራይን ህዝብ ነው መለያየት ያለባቸው። በትግራዋይ ላይ የሚደረግ ቅስቀሳ ጠቅልሎ ካልቆመ በስተቀር በትግሬ ላይ የሚወሰዱት የተሳሳቱ እርምጃዎች የተሳሳቱ አመለካከቶች ሊስተካከሉና ሊታረሙ ካልቻሉ የትግራይ ህዝብ ተባብሮ ወደ ትግሉ ሊገባ የሚችልበት አግባብ ተፈጥሮ ሊቀላቀለው ካልቻለ በኢትዮጵያ የሚፈለገው ሰላም ዴሞክራሲያዊ ለውጥ ፍፁም ፍፁም ሊመጣ አይችልም። ይሄ አሁንም ይመለከተኛል የሚል አካል በዚህ ጉዳይ ላይ ለውጥ አመጣለሁ የሚል አካል ይህንን ቆም ብሎ ሳይመለከት ይህንን ቆም ብሎ ሳይገመግም ይህንን ሳያስተካክል ዝም ብሎ ወደፊት ብቻ ቢሄድ ኖሮ ምንም አይነት ለውጥ ሳያመጣ ድካም ብቻ ነው ሆኖ ሊተርፍ የሚችለው። ለምን ካልከኝ ከላይ እንዳልነው ነው።

የትግራይ ህዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች ለየት ያለ የራሱ ታሪክ አለው። እነዚህ የትግራይ ህዝብ ታሪኮችና ክብሮች የትግራይን ህዝብ ማንነትና ቀጣይነት ህላዌና የኢትዮጵያን ህዝብ ገፅታ ክደህ እንደፈለግከው ለመኖር ታስብ ከሆነ ሌላ ነገር ነው። እኛ እየታገልን ያለነው ትግሬዎች ነን። የትግራይ ህዝብ ሰላም ያላገኘ መሆኑ፡ የትግራይ ህዝብ ያላረፈ መሆኑ፡ የትግራይ ህዝብ ስርዓት እንዲለወጥ የሚፈልግ መሆኑ፡ እኛ በቂ ማረጋገጫ ነን እንደ እኛ የተሰዋ አካል እኮ የለም።

ከደርግ ስርዓት ውድቀት በኋላ የወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግን ስርዓት ለመታገል ከተደራጁ ድርጅቶች መካከል ከእኛ ጋር እኩል ይቅርና፡ የእኛን ያክል ሊጠጋ የሚችል መስዋዕት የከፈለ የለም። አሁንም ቢሆን ትግራዋይ ነው ከፍተኛውን ዋጋ እየከፈለ ያለው ይህንን አይነቱን የትግራይ ህዝብ ውሎ ወደ ጎን ትቶ ጀምሮት ባለው መልካም ተግባር እንዳይቀጥል እንቅፋት አይቶ እንዲቆም የሚወሰዱ እርምጃዎች ፍፁም የመጭውን ሁኔታ ያለማንበብ

የወለዳቸው ሊሆኑ እንደሚችሉ ግምት ውስጥ በማስገባት ከዚህ በኋላ ሊስተካከሉ ሊታረሙ የገባችዋል ብቻ ነው የምለው።

**ብስራት መፅሄት፦ እሺ ታጋይ ይብራህ በርሄ ምናልባት ስለትግራይ ተደጋጋሚ ጥያቄዎች ጠይቄሃለሁ በአሁኑ ጊዜ ያለው ተጨባጭ ፖለቲካዊ ሁኔታም እሱ ስለሆነ መልስ ስለሚያስፈልገው ልንታገለውም ስለሚገባን ነው በተደጋጋሚ እየጠየቅሁህ ያለሁት፣ ትግሬዎች ተጠቅመዋል ስለሆነም በትግራይ ተቃውሞ የሚባል ነገር የለም የሚባልበት ሁኔታ አለ ትግራዋይ ተጠቅሟል ወይ? የትግራይ ህዝብ ሐቀኛ አኗኗር እስኪ ግለፅልን? በመሰረቱ የትግራይ ህዝብ እየተቃወመ አይደለም የስርዓቱ ደጋፊ ነው የሚባልበት ሁኔታ ነው ያለው በትክክል የስርዓቱ ደጋፊ ነው? የትግራይ ህዝብ እየተቃወመ አይደለም ያለው?**

ታጋይ ይብራህ በርሄ፦ እንደ ሸረሪት ቤት በጨርቅ የተሸፈነ ነው እንጂ የትግራይ ህዝብ እንቅስቃሴ የለውጥ ሃዋርያ መሆን በቦታው አለ። ልክ ስልህ እንደቆየሁት ነው



ትግራዋይ አልተጠቀመም ብቻ ሳይሆን ተጎድቶ ከስሮ ህ.ወ.ሃ.ትን ለድል ለማብቃት የትግራይ ህዝብ በቤቱ አሉ የሚባሉ ወንድ ይሁን ሴት ልጁን ያልከፈለ የለም። አምራች የሚባለው ሃይል ስርዓቱን በማምጣት ወይም ድርጅቱን በመንከባከብ ከተከፈለ፣ የትግራይ ህዝብ ምርቱን ቀንሷል ማለት ነው። ይሄ ብቻ ሳይሆን የትግራይ ህዝብ ድርጅቱን በመንከባከብ ከከብቶቹ እስከ ንብረቱ ከፍሎ አሸሞንሙኖ ነው ወደ ስልጣን ያበቃው።

ከግንቦት 20 በኋላ አገር በተቆጣጠረ ጊዜ ደግሞ ምንም አይነት ያደረገለት ነገር የለም አደረገላቸው እንዳይባል እንዲያውም ቤታቸውን ትተው ነው፣ የትግራይ ህዝብ ከማንም በላይ በጦርነት ምክንያት የተጎሳቆለ የተጎዳና ያለቀ ህዝብ እያለ፣ የደኸየና የተጎሳቆለ ህዝብ እያለ፣ ለሌሎች የጦርነት ድምፅ ያልነበራቸው ክልሎች ነው ብዙ ነገር ሲሰጧቸውና ሲያደላድሏቸው የቆዩ፣ የትግራይ ህዝብ የት ነው የተጠቀመው? ት.እ.ም.ት የምትባል ተቋም (የትግራይ እግር መትከል) ለትግራይ ህዝብ ምን ታደርግለታለች እንዲያውም ከስሩ ትነቅለዋለች እኔ በደንብ አድርጌ አውቃታለሁ። ተበደሩ ይባላል ጥምድ በሬ ያለው ይበደራል መንቀሳቀሻ ያጣል ሰርቶ ሊበላበት የሚችል እድል የለም ገንዘቡን ያጠፉዋል ይታነቃል። በሬውን ሽጦ ይከፍላል ጥምድ በሬ የነበርውና ሊሰራ የሚገባው በአንድ በሬ ይተርፋል። ይህንን የቀረውን አንድ በሬ ሽጦ ደግሞ ወደ ስደት ይሄዳል። ማ.ረ.ት በተመሳሳይ ማህበራዊ ረድኤት ትግራይ ሁሉም በትግራይ አሉ የሚባሉት ፋብሪካዎች ትንሽ እንኳን ለትግራይ ህዝብ አይጠቅሙትም አልተጠቀመባቸውም፣ የትግራይ ህዝብ በእነዚህ የት.እ.ም.ት ተቋማት በርካሽ እየሸቀለ ለበይዎች ነው እየሰጠ ያለው።

ስለዚህ የትግራይ ህዝብ ፈፅሞ አልተጠቀመም፣ አልተጠቀመም ብቻ ሳይሆን ስሩ ተነቅሎ ፆሙን የሚያድር ሰው ነው የሚበዛው፣ ጨርቁን በእጁ ሰፍቶ የሚለብሰው ሰው ይበዛል ባዶ እግራቸውን የሚሄዱት እናቶቻችን ይበዛሉ የተጎሳቆሉ እናቶች አሉን። ሁሉን ነገር ማየት ይቻላል። የትግራይ ህዝብ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ እንደ ሌሎች ያልሆነበት ምክንያት ስለተጠቀመ ነው፣ ከዚህ በላይ ምን እንድናገኝ ፈልገን ነው ብሎ ነው የሚባል አባባል በራሱ ስህተት ነው። የትግራይ ህዝብ እንደ ሌላው ግልጥ የሆነ ንፋስ የሚመታው የሚቀጣጠል ነበልባል እንዳያነሳ፣ ስንለው እንደቆየነው የሸረሪት ጨርቅ የሸፈነው ይህ የሸረሪት ጨርቅ ምድነው ካልን በላዩ ላይ የሚነሳሳው ብትር እንዲቆም እንዳይቀጥል ሰቅጠጥ

እንዲል ያደረጋል። ይህንን ቢረዱ ጥሩ ነው እንደዚህ ያሉ ወገኖች ራሳቸውን ከማታለል ሁኔታውን በትክክለኛው መንገድ ገምግመው አይተው የትግራይ ህዝብ ለምንድን ነው ተሳታፊ ያልሆነ እየተጠቀመ ነው? ይህንን ቢያውቁ ጥሩ ነበር።

የአንድ የትግራይ ተወላጅ አመታዊ ገቢ ስንት ነው? የትግራይ ህዝብ ምን ያክል ፐርሰንት ነው ራሱን ችሎ በልቶና ጠጥቶ ሊያድር የሚችለው? የትግራይ ህዝብ ስንት ፐርሰንት ነው በስደትና በመከራተት የሚኖር? ያሙን እያደረ ባዶ እግሩን የሚሄድ ታሞ ሊታከም የማይችል ስንቱ ነው? አሁን ታዲያ ትግራዋይ ተጠቀመ የሚሉት እኛ ነን ያልበረታን እኛ ነን መሆን እንደሚገባን ያልሆነ እንጂ ህዝባችን እማ ለውጥ ይፈልጋል ከማንም ጊዜ በላይ ህዝባችን ከፍቶታል። ስለዚህ ይህ እንደዚህ አይነት መልእክት ትክክል ያልሆነ መልእክት ነውና ማረሙ ጥሩ ነው ባይ ነኝ።

**ብስራት መፅሄት፦ ህዝብ ያለውን ምሬት ያለውን ችግርና መከራ በጣም ወደ ከፍ ደረጃ ስለደረሰ ህዝባዊ አመፁ እየቀጠለ ይገኛል፡ ምናልባት በተቃዋሚ ድርጅቶች በኩል ግን ፖለቲካዊ ትግል የሚያደርጉ ሊሆኑ ይችላሉ ወይም የትጥቅ ትግል የሚያካሂዱ ድርጅቶች ህዝቡን ሊመሩት አልቻሉም ትግሉን ሊያስኬዱት አልቻሉም ህዝቡ ነው መርቷቸው እየሄደ ያለው የሚባልበት ሁኔታ አለ እዚህ ላይ ያለህ አስተያየት ምንድን ነው?**

ታጋይ ይብራህ በርሄ፦ ሃቁ እሱ ነው እየተባለ ያለው ጥሩ ነው፡ ለምን ካልከኝ እኛ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅቶች የትጥቅ ትግል ከምናካሂድ ከ10 ኣመታት በላይ አድርገናል። በውስጥ ያሉት ፖለቲካዊ ሃይሎች ተመሳሳይ። አንድ በመካከላችን ያለው መተሳሰር መሰረታዊ ህይወት ያለው ነገር አይደለም። ሁለተኛ ነገር ፖለቲካዊ ትግል የሚያካሂዱት ድርጅቶች የገዛ ራሳቸው ይደራጁ ይጠነክሩና በመካከላቸው ክፍተት ይፈጠራል። በጥቅም የሚባልጉ ስግብግቦች ይገኙባቸዋል። በውስጥ ሆነው የትግሉን እለታዊ እንቅስቃሴ ለጠላት በመመገብ ጠላት እንዲጠቀምበት ትግሉን እንዲያዳክመውና እንዲበታትነው በሚችል መንገድ እድል ይሰጡታል መጨረሻ ላይ ይበታተናል። ህዝቡም ተስፋ ይቆርጣል ተፈጥሮ የነበረው አደረጃጀትና መስመር ቀንቶ የነበረው ይጎለድፋል። ማዕበሉ ስላለ ግን ጎልድፎ እያለም ይሄዳል። በዚህ ልክ ህዝብ የሚከፍለውን መስዋዕት እየከፈለ ተቃዋሚዎች የሚባሉትን ሃይሎች ወይም ድርጅቶችን ይቀድማቸዋል። ይህ ነው እውነታው የትጥቅ ትግል እያካሄድን ያለን ተቃዋሚ ሃይሎች ለገዛ ራሳችን ሲባል እንደቆየው የተደራጀን አይደለንም። ያለመደራጀታችን ምክንያት ደግሞ አስቀድሜ ስልህ እንደቆየሁት አልጠነከርንም።

ለዚህ ነው በይበልጥ በ2ኛው ድርጅታዊ ጉባኤያችን ሊሰመርበት ይገባል። ከማንኛውም ጊዜ በላይ ሁኔታዎችን አንብበን ልንወሃሀድና ተጣምረን ደግሞ መስራት አለብን የምንለው ማለት ነው። ስለዚህ ህዝብ ቀድሞናል አዎ ህዝብ ከእኛ በላይ ከፍቶታል ስለዚህ ህዝቡ 24 ሰዓት በምሬት ስላለ ትዕግስቱ ሊያልቅ የግድ ነው፡ የመሰለውን እርምጃ ለመውሰድ የተገደደው። አሁን እኮ የሚያስተማምን ተቃውሞና ንቅናቄ አይደለም ያለው ዝምብሎ ስሜታዊ ግጭት ነው ያለው፡ ይህንን ስሜታዊ ጎነፅ ደግሞ መስመር የሚያስይዘውና የሚመራው ሰው ኣላገኘም፡ መስመር ቢይዝ ኖሮ ውጤታማ ሆኖ ወደ አንድ ደረጃ ይደርስ ነበር። ህዝብ ግን 24 ሰዓት በስርዓቱ ጫና ስር ሆኖ እስኪ ነገ ለውጥ ይመጣ ይሆናል የሚልበት እድል ስለሌለ የግድ በመሰለው መንገድ እየሄደ ነው።

**ብስራት መፅሄት ፦ ታጋይ ይብራህ በርሄ የነበሩኝን ጥያቄዎች እዚህ ላይ ጨርሻለሁ ምናልባት በመጨረሻ የምታስተላልፈው መልእክት ካለ እድሉ ልስጥህ።**

ታጋይ ይብራህ በርሄ፦ ምናልባት እኔ ምን ለማለት እፈልጋለሁ በዚህ ወቅት የኢትዮጵያ ህዝብ ይሁን የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች ስርአቱ በምን ደረጃ ላይ ደርሶ እንዳለ አይተናል። ምናልባት የኢትዮጵያ ህዝብ በዚህ ጊዜ ልቦና ያስፈልገዋል እላለሁ። አንዱ በአንዱ ላይ የሚነሳበት ጊዜ አይደለም። አንዱ በአንዱ ላይ የሚያሾፍበት ጊዜ አይደለም። ይህ ስርዓት በዚህም ይሁን በዚህ መያዣ የሌለው የደንደሮ እሾህ ማለት ነው። በትግራይ ህዝብ አልታቀፈም፡ ለትግራይ ህዝብም ይሁን ለሌሎች ኢትዮጵያውያን መከታ ያልሆነ ስርዓት ስለሆነ ሆላችንም ይህንን ኀመሮ እሾህ እንዴት አድርገን እንነቅለዋለን የሚለውን ማሰብ አለብን እንጂ፡ እርስ በርሳችን እየተሿሿፍን እርስ በርሳችን እየተጠቃቃን እየተጣላን እርስ በርሳችን እየተጎዳዳን የምንኖርበት ጊዜ ማብቃት አለበት።

ሌሎች ተቃዋሚ ኃይሎች ካለን ደግሞ በውስጥም ይሁን በውጭ ያለን ከማንኛውም ጊዜ በላይ መስራት የሚገባን በዚህ ጊዜ ነው። ጠላቶቻችን እየወደቅን ነው ብለው ውድቀታቸውን ባመኑበት ጊዜ እኛ ማድረግ የሚገባንን ነገር ካላደረግን ለውጥ ያለው ጉዳይ አይሆንም፡ ካለፈው ጊዜ የሚለይ አይደለም። የህዝባችን ስቃይ ስቃይ እየወለደ ይቀጥላል። ስለዚህ እኛም መንከራተታችን መታገላችን መስዋዕት መክፈላችን ካልቀረ እየተሰዋ ያለው ወጣት ህይወቱን ከፍሎ የትውልድን ህይወት ለማዳን የመጭውን ትውልድ ህይወት ለማስተካከል ለማደላደል የሚደረገው መስዋዕት መሆኑን አምነን፡ ነፍስ ወከፍ ይመለከተናል የምንል አካላት ተጋግዘን ልንሰራበት የሚገባን ተደራጅተን ልንሰራበት የሚገባን ጊዜ ነው ይህ ወቅት።

ጠላቶቻችን በህዝባችን ላይ እንደ እስስት ቀለማቸውን እየቀያየሩ ህዝባችንን ቀልቡን እያጠፉበት ስላሉ፡ እኛ ዝም ብለን ጊዜ ከምንሰጥ የህዝባችንን ስቃይ አሻግረን ከምንመለከት፡ ገብተን የስቃዩ ተካፋዮች እንድንሆን በይበልጥ ደግሞ መስራት ውጤት፣ ለውጥ ለማምጣት በለውጥ መስመር አንቀሳቃሾች እንድንሆን የሚቻል አቅማችንን አደራጅተን መስራት ይገባናል። ይህ ነፍስ ወከፍ ይመለከተኛል የሚል የለውጥ ሃይል ሊታጠቅለት የሚገባው ጉዳይ ነው።



ሌላ በጠቅላላ የኢትዮጵያ ህዝብ ለታቃዋሚዎች መደረግ የሚገባው መተጋገዝ፡ እንዲሁም ለትግል ኃይሎች የሚደረግ መተጋገዝ በሁሉም አይነት በፖለቲካዊ በዲፕሎማሲያዊ በማቴሪያላዊ መተጋገዝ አጠናክረው መቀጠል ይገባቸዋል። ከማንኛውም ነገር በላይ ደግሞ ለዚህ እየተነሳ ያለውን አመፅ ስሜታዊ ከሚሆን በልቦና አገራዊና ስትራቴጂካዊ የታቀደ፣ የተመራና የተደላደለ እንዲሆን መረዳዳትና መመካከር ያስፈልጋል። ምክንያቱም ሊቅ የወለደች አገር፣ ብዙ የተማረ የሰው ኃይል ያፈራች አገር አቅጣጫ ጠፍቶባት በእንደዚህ አይነት ውስብስብ ነገር እንዳትገባ፡ ነበረች እንድትሆን እጅና እግራችንን አጣምረን ማየት የለብንም። አገራችን ደግሞ ለህላዌያችን ለዘላለም እንድትኖር ሁላችንም ለዚህች አገር ለደህንነቷ መቆም መቻል አለብን።

**ብስራት መፅሄት፦- የት.ህ.ዴ.ን ምክትል ሊቀመንበር ታጋይ ይብራህ በርሄ የጠየቅንህን ጥያቄዎች ጊዜህን ሰውተህ ሰፊ ማብራሪያ ስለሰጠኸን በብስራት መፅሄት አንባቢዎች ስም ልናመሰግንህ እንወዳለን።**

# የኢህአዴግ በጥልቀት የመታደስ ሂደት ከየት ወዴት? ምንስ ይመስላል?

በመጀመርያ ህዳሴ ማለት ምን ማለት ነዉ? ህዳሴ አንድ የቆየ ነገር ካረጀ እንደ አዲስ ሊሰራ ከተፈለገ፣ የቆየዉን አስተሳሰብ ወደ ማያስረ ደረጃ ከወረደ፣ ሊያራምድ በማይችልበት ደረጃ ከወርደ፣ መቀየር አለበት ተብሎ ከታመነበት፣ ሲያገለግል የቆዬ ነገር እንደ አዲስ አሰርተህ ልትጠቀምበት የፈለከዉን ነገር እንድታሻሽለዉ መፈለግ (መገምባት) የሚል አንድ ወጥ መግለጫ ሊሰጠዉ ይችላል።

ህዳሴ ይህን የመሰለ መግለጫ ከተሰጠዉ ኢህአዴግ እንደ ስርአት ህንፃዎቹና መዋቅሩ ህገ- ደምቡና ፖሊሲዎቹ በወደመበት ደረጃ፣ አዎንታዊ ይዘት ያላቸዉ አዋጆቹና አሰራረቹ ቢሆንም ተግባራዊነት ሊላበሱ አልቻሉም። በተለይ ደግሞ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በራሱ ያወጣቸዉ ህጎች በራሱ እየጣሰ የህግ በላይነት በመጣስ ለህግ ተገዥና ተጠያቂ መሆን ወደ ጎን ቀርቶ ስርአት አልበኝነት በነገሰበት፣ ኢትዮጵያ ወደ እርስ በርስ ጦርነት እንዳትገባ አስጊ ነዉ እየተባለ እየተነገረ ባለበት ወቅት፣ የሃገራችን ፖለቲካዊ ሁኔታ ምስቅልቅል ባለበት ጊዜ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ እርምጃ ታስሮ ፈፅሞ ወደ ፊት መራመድ አቅቶት የኢትዮጵያ ህዝብ እየተቃወማቸዉ ለመጣ የስርአቱ የበሰበሱ አሰራሮች፣ በዚህ ወቅት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በርግጥ በሽታ አለኝ ግን በራሴ እፈወሳለሁ ወደሚል ድምዳሜ ደርሷል። እንደአገላለፁ ደግሞ "በጥልቀት መታደስ "ነዉ መድሃኒቴ ብሎ በመጣደፍ ላይ ተጠምዷል።

ገዥው ፓርቲ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በዚህ ቅርብ ጊዜ በሽታዬን በራሴ መርምሬ ለማግኜት ችያለሁ ያካሄድኩት ጥናትና ግምገማ መሰረት በማድረግ እታደሳለሁ በማለት፣ የስልጣን መቀያየር እንደሚያደርግ ከገለፀ በኋላ፣ ለዚህ ተከትሎም ባደረገዉ የስልጣን ሹም ሽር ተግባር ጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማርያም ደሳለኝ ወደስልጣን ያመጣቸዉ ካደራጃቸዉ 30 አባላትን ያቀፈ ካቢኔ በጥቅምት 22 ቀን 2009 ዓ/ም ዘጠኝ ብቻ በማስቀረት 13 አዲሶች ያላቸዉን በማምጣት ለይስሙላ የህዳሴ ጉዞ እርምጃዉ በዚህ ነዉ የጀመረዉ። ገና ሳይራመድም



የተንጠባጠበ ጅምር ሆኖ በርከት የለ ጥያቄም አስነስቷል።

ከ26 አመታት በላይ በስልጣን የቆየዉ ወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ከጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ጀምሮ ሌሎች አማካሪዎቹም አባይ ፅሃየ፣ ስብሓት ነጋ፣ በረከት ስምኦን፣ አርከበ ዕቁባይና ሌሎች የመንግስት የስራ አስፈፃሚ አካላት በአዲስ መልክ ወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ይደራጃል ሲሉ በአመቱ መጀመርያ ደግሞ ፕሬዚደንት ሙላቱ ተሾመ የኢህአዴግ መንግስት የገዞ አቅጣጫ የሚያሳይ መግለጫ ከሰጠ በኋላ፣ በጥልቀት መታደስ የሚለዉ እርምጃ እስከሚወሰድ ደግሞ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በእውነቱ ይታደሳል ወይም አይታደስም የሚለዉ ሲያወዛግብ ቆይቷል።

በትክክል ይታደሳል ወይም አይታደስም የሚለዉ ጥያቄ ግን ከቀድሞ የስርአቱ ተግባራት በመፈተሽ ማገናዘብ ይቻላል። ወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በ1993 ዓ/ም በስብሶ እንደ አዲስ ህዳሴ አድርጌያለሁ ብሎ እንደቀረበ የሚታወቅ ሆኖ፣ እንደገና በስልጣን ለመቀጠል ባደረገዉ ጥረት በጠመንጃ ሃይል ተጠቅሞ በስልጣን ሲቀጥል ቆይቶ፣ ከ15 አመት በኋላ

ደግሞ “በጥልቀት መታደስ” የሚል የስርአቱ ስልት፡ ለየዋሁ ወገናችን ገና በገናዉ አይኖቹ ሊሸፍነዉ በሚያስች ስልት ጥረቱን ሲቀጥል እየታዬ ነዉ።

የስርአቱ ባህሪና ፀባይ የገባዉ ወገን ግን የህዳሴዉ መነሻና መድረሻ በግዜዉ ስለ ገባዉ ትግሉ አጠናክሮ እየቀጠለ ነዉ የሚገኘዉ። በአንድ ሃገር ከአንድ ድርጅት ዉጪ አማራጭ ድርጅት በሃገሪቷ ካልተገኘ አንድ ጊዜ ሊታደስ ይችላል፡ ከዚያ ባሻገር ግን ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በህዝብ ላይ አለም ያወቀችዉ በወግ ጦርነት አዉጆ ሲያበቃ፡ በሙቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ፖለቲከኞች፣ ተቃዋሚ ድርጅቶች ከእነ አባሎቻቸዉ፣ ጋዜጠኞች በአሰቃቂ እስር ቤት ታጉረዉ ባሉበት ጊዜ፡ ባለፈዉ ምርጫ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ካለፉ ምርጫዎች ለየት ባለ መንገድ 100 በ100 አሸንፍኩ ብሎ ከእነብዙ ችግሮቹ በርግጥ በስልጣን ላይ እየቀጠለ ነዉ።



ይህ ሆኖ ሲያበቃ፡ ከምርጫ በኋላ ብአዴን፣ ኦህዴድ፣ ህወሃትና ደህዴን በላያቸዉ ላይ ካለፉ አመታት ለየት ባለና በበረታ መንገድ የተነሳባቸዉ ህዝባዊ ቁጣና ተቃዉሞ እስከ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ደርሷል። ሃገር በጊዜያዊ አዋጅ በወታደራዊ አገዛዝ እየተመራች ባለችበት ህዝቡና ስርአቱ በፍፁም ተነጣጥለዉ ባሉበት ወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ እታደሳለሁ ማለቱ ለማን የትኛውን ህዝብና ሃገር ሊያስተዳድር ነዉ? ህዝብና መንግስት የትና የት ሆነዉ እንደሚኖሩና እንደሚታገሉ ስርአቱ ግልፅ ያላደረገዉ ጉዳይ ነዉ።

አሁን እየተካሄደ የሚገኘዉ ግምገማ ዋና ትኩረቱ በታች አድርጎ በእሱ ላይ ተረግጦ እንዲካሄድ ማድረግ፡ ላየኛዉ አመራር ግን እንዳትነካኝ አልነካህም ተቻችለን እንሂድ ሚስጥራችን ይታቀብ መባባላቸዉ፡ “በጥልቀት መታደስ” የሚለዉ ዘመቻ ያልጠለቀ ለተጠያቂነት ዝግጁ ያለመሆን የሚያሳይ ሆኖ፡ ስርአቱ የፈፀማቸዉ ሁሉ ፀረ ህዝብ ተግባራት የስርአቱ ጥፋት ተብለዉ በግልፅ የተቀመጡ ስተቶችና ጉድለቶች፡ ያሻቸውን ብቻ የሚሸከማቸዉና የሚጠየቅላቸዉ ከሆነ፡ ጥልቀት የሌለዉ መሆኑን ነዉ የሚያሳየዉ፡ የበላይ አመራር በየተኛዉ መንገድ ነዉ ችግሩ ተፈትሾ እንደየችግሩም ተጠያቂ የሚሆንበት መንገድ እየተስተካከለ ያለዉ? ለሱ ተከታትሎ ወደ ህዝብ መረጃዉ የሚያቀርብ ለፓርቲዉና ለህዝቡ የሚያገናኝ ገለልተኛ አካል አለ ወይ? ያ በጥልቀት መታደስ ተብሎ የታወጀ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ዘመቻና አጋር ድርጅቶቹን ብቻ ሳይሆን ህዝቡም ጭምር መታደስ አለበት የሚል እምነት እንዳለዉ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ እየገለፀ እስካለ ድረስ፡ ግልፅነቱና ጥልቀቱ ሊታይ አልቻለም።

በመሰረቱም ተደጋግሞ ሲገለፅ እየተሰማ ያለዉ የታችኛዉ እና ወደ ማህበረሰቡ ወደ ወረዳና ቀበሌ ቅርበት ያለዉ አመራር ችግሩ በታችኛዉ አመራር ብቻ እንዳለ ነዉ የስርአቱ እምነት፡ የስርአቱ ፖሊሲዎች እንዴት እየሄዱ ነዉ? ምን በጊዜዉ ተግባራዊ ተደረገ ምን አልተደረገም ማን አጠፋ የመቆጣጠር ሃላፊነት የማን ነዉ? እርምጃ የመውሰድ ፈንታ የማን ነዉ? የሃገሪትዋ በጀት የትና በማን እንደተዋጠ የሚቆጣጠርና የሚጠይቅ ማነዉ ታድያ? ከሃገሪቷ ባንክና ካዝና መዞ መዞ የበጀተዉ ማነዉ? ለወታደራዊ፣ ለልማት፣ ለምርጫ ወዘተረፈ እያለ ማነዉ እንዴ ያከፋፈለዉ? የተመደበ በጀት ያጠፋፋ መንግስታዊ አካል አመራር፡ የሚጠይቅ የበላይ አመራሩ አይደለም እንዴ? ለዚ የማይቆጣጠር የበላይ አመራር

ለምን ተገምግሞ ተጠያቂ አይሆንም? መሰረታዊ ችግሩ በበላይ አምራር ላይ መሆኑ ግን መዘንጋት የለብንም።

የመልካም አስተዳደር ችግር እየተባለ እየተገለፀ የሚገኘዉ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ሃገሪቷ ገብታበት ያለችውን ፖለቲካዊ ቀውስ ተከትሎ፡ በተለይ በዚህ አመት የታዩ ችግሮች ሰከን ባለ



መንገድ ለመግታት ያልቻለዉ ስርአቱ በሃይል ለመፍታት፡ ወታደራዊ ትእዛዝ እያወረደው ሃይለማርያም ደሳለኝ ለፓርላማ አባላት ሰብስቦ ባወረደዉ ትእዛዝ መሰረት እኮነዉ በኦሮሚያና አማራ ክልሎች ተመልከት በማለት ከወታደር የተተኮሰ ጥይት በሽዎች የሚቆጠር ህይወት ተቀጥፎ ሲያበቃ፡ የዚህ ተጠያቂ ማነዉ? የተኛዉ ወታደር ነዉ በህይወት የተጠየቀዉ? ማን ተጠየቀ? ያ የተቃወመ ህዝብ ግን ሲገደልና ሲታሰር ነዉ የታዬዉ። ይህ ችግር ግን የበላይ አመራር ችግር እንጂ ለታችኛዉ ተሸከመዉ የሚባል አይደለም። በዚ ደግሞ እንማን ናቸዉ ተጠያቂዎቹ በግልፅ የበላይ አመራር ነዉ ባለቤቱ።

የታችኛዉ ጥፋትም የከፍተኛ አመራር ምስል የሚያሳይ የሱን ቅጥያ ሁኖ ሲያበቃ፡ በአጠቃላይ የበታች አመራሩ ብቻ ጥፋተኛ ከተባለ የሱ አለቃ ከፍተኛ አመራሩ እሱ አደለም እንዴ? ከፍተኛዉ እንዴት ብሎ ጤና ያለዉ ሊሆን ይችላል? እንደዚህ ከሆነማ ያ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ትልቅና ትንሽ አሳ እየተባለ ሲሰጠዉ የቆዩ ስም፡ ከፍተኛዉ የሱ የራሱ ችግሩ ሳይመረምር ከሱ በታች ላለዉ እንደጠላት እያደነ መዋጥ ብቻ ከሆነ ተግባሩ፡ በሽታዉ የት ላይ እንዳለ ህዝብ ልብ ብሎ ማስተዋል አለበት።

ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ህዳሴ እያስፈለገኝ ነዉ ብሎ በ15 አመታት ዉስጥ ያከናወናቸዉ ስራዎች በአራት ቀናት ዉስጥ ከገመገመ በኋላ፡ እስካሁን ሲያጋጥሙት ለቆዩ ፖለቲካዊ ችግሮች በግምገማ ለመፍታት እያደረገዉ ያለ ጥረት መሆኑ እየገለፀ ያለ ቢሆንም እንኳን፡ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የሚከተለዉ የዴሞክራሲ ማእከሉ ያልተቀደሰ ኪዳን በመሆኑ ግን ካለፉ አመታት የወሰድናቸዉ ትእዝብት በቂ ትምህርት ስለሆኑ፡ እዚህም ህዝብ የዚህ ሂደት በንቃት ሊከታተለዉ ይገባል።

ይህ የዴሞክራሲ ማእከላዊነት መርህ በአጋር ድርጅቶቹ መካከል ያለዉን በነዚህ ግንባሮች ያለዉ ግንኙነት ሚዛኑን አዛብቶት ነዉ የቆዬዉ። አራት ድርጅቶች ያቀፈው ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በስራ አስፈፃሚነት ያደረጋቸዉ የባለስልጣናት አቀማመጥ፡ ከታች ወደ ላይ ከላይ ወደ ታች የተወሰኑ ሰዎች በዚህ አቀማመጥ የስልጣን ድልድል እያደረገ ቢታይ እንኳን በተለይ ደግሞ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በተማረ የሰዉ ሃይል ፓርላማዉ ማጠናከሩ እየገለፀ ቢሆንም፡ ሆኖም ግን የሃገራችን ዩኒቨርስቲዎች ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የሱ ታማኝ አባሎቹ የሚመለምልላቸዉ ተቋማት እንደሆኑ የስርአቱ ፖሊሲና ስትራተጂ የሚያራምዱ አባላቱ የሚገነባለትና የሚያጠናክርለት መሆኑ በግልፅ ሲታይ የቆየ ጉዳይ ነዉ።

በዚህ መሰረትም በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የቆዩ የስርአቱ አባላት በጥቅምት 22 ቀን 2009 ዓ/ም በተደረገ የባለስልጣናት አቀማመጥ ተግባራዊ እንዲሆን አድርጎታል። ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ባሳለፋቸዉ አመታት በመልካም አስተዳደር ጉድለት የልማት ጥያቄ መልስ ባለማግኘታቸዉ፡ እንዲሁም በተለያዩ ምክንያት በተፈጠረ ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል ባለመኖሩ

ምክንያት በማድረግ ለተነሳዉ ህዝባዊ ተቃዉሞ፡ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ለሚነሱ ተቃዉሞዎች በዉጪ የሚገኙ ሃይሎች የሚመራና የሚተባበር ነዉ ብሎ ነዉ የሚገልፀዉ።

በሌላ በኩል የሚጋጭ የስርአቱ ሃሳብ ደግሞ በተለያዬ የሃላፊነት ደረጃ የተቀመጡ የመንግስት አመራሮች የመንግስት አካለት ህዝብ የማገልገል የመንፈስ መዳከም ከዚህ ዉጪም ስልጣን የኑሮ መሰረት በማድረግ በግል ጥቅማቸዉ መዋል፣ ከተጨባጭ የህዝባችን ሁኔታና የመልካም አስተዳደር ጉድለት፣ የልማት ስራዎች መጓተት፣ ከአመት ወደ አመት እየታዬ ያለዉን የተጋነነ የህዝብ ብዛት ከአለማዊ ብልፅግና የሚሄድ የማህበረሰቡ ሁኔታ ሊሟላ ባለመቻሉ የህዝብ ተቃዉሞ ከፍ እንዲል አድርጎታል ሲል የሚቀበለዉ ቢሆንም እንኳን፡

በህዳሴ ስም መነሻዉ ፌደራል አድርጎ ወደ አጋር ድርጅቶቹ ወደ ክልል እያለ እስከ ዞኖችና ወረዳዎች ለመገምገም የበቃ ቢሆንም፡ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ለዚህ ሂደት በሚፈለገዉ መንገድ እየሄደ እንዳለ የስርአቱ ችግሮች በሚወገድበት አገባብ ዉጤታማ በሆነ ሂደት እንዳለ ሲገልፅ እየተሰማም ቢሆንም፡ መሰረታዊ ግምገማዉ መካየድ የነበረበት ግን ከፍተኛ ባለስልጣናት ነበር መተየት የነበረባቸዉ። ካልሆነ ግን ታችኛዉን አገማግመህ ተጠያቂ ለማድረግ የሚደረግ ጥረት፡ ዘመቻዉ ስኬታማ እንዳይሆን የሚያሳይ ለማንም ደግሞ የሚዋጥለት ሊሆን አይችልም።



ጭንቅላት ካልተስተካከለ ምን ጤና ይኖራል? ይህ በእንዲህ እንዳለ ሌላ ችግር ደግሞ በባለስልጣናት መካከል በህ.ወ.ሓ.ት፣ ብ.አ.ዴ.ንና ኦ.ህ.ዴ.ድ ሃይለኛ የሆነ አለመግባባት ተፈጥሮ እንዳለ ከኢትዮጵያ ህዝብ እይታ የተሰወረ አደለም። በመሰረቱም በዚህ አመት ለተነሳዉ ህዝባዊ ቁጣ ተከትሎ ህ.ወ.ሓ.ት እንደ ህ.ወ.ሓ.ት ብ.አ.ዴ.ን እንደ ብ.አ.ዴ.ን ዴ.ህ.ዴ.ንም በተመሳሳይ የየራሳቸዉ አማራጭ ወደ ማፈላለግ አምርተዉ ቆይተዉ አሁንም አሉ።

በተለይ ግን ህ.ወ.ሓ.ት ሁልግዜ እንደሚለዉ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሰረት እኔ ነኝ በዚህ ወቅትም ከኢትዮጵያ ህዝብ ምን ያህል መነጠሉን እያወቀ፡ አሁንም ቢሆን ህ.ወ.ሓ.ት ከኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በላይ አልፎ በመሄድ፡ ለነዚህ አብሮት ፖለቲካዊ ጠበል ቀማሾቹንና የእድሩ አጋሮች ወደ መክሰስ ላይና ታች ሲል ነዉ የታዬዉ። በተለይ በተለይ በትግራይና አማራ መካከል ያለዉን የድንበር መጓተት ህ.ወ.ሓ.ትና ብ.አ.ዴ.ን መፍታት አልቻሉም፡ ይህ ደግሞ አሁን የተናሳ ሳይሆን ከረዥም አመታት የጀመረ ሲሆን፡ በየግዜዉ በሁለቱ ህዝብ መካከል ሲያጋጥም የቆዬ መሳሳብ በዚህም የህ.ወ.ሓ.ትና የብ.አ.ዴ.ን ባለስልጣናት እየተነጋገሩበት የቆዩ ቢሆንም እንኳን፡ ተግባብተዉ ሊፈቱት ባለመቻላቸዉ ግን የሁለቱም ክልል ህዝብ እስካሁን በችግር ዉስጥ ይገኛል።





ከሁሉም በፊት ህዳሴዉ ኦ.ህ.ዴ.ድ የጀመረዉ ሲሆን የድርጅቱ ሊቀመምበርና ምክትል ሊቀመምባር የተወገዱ ሆነዉ፡ ይህም ኦ.ህ.ዴ.ድ ራሱን ችሎ ለመፅዳት ስለ ፈለገ ሊታደስ ስለ

ፈለገ ብቻ ሳይሆን በኦሮሚያ ክልል የታየዉ ህዝባዊ ቁጣ ተከትሎ ኦ.ህ.ዴ.ድ ከኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ጋር የለም ለተቃዋሚ ድርጅቶች የተሸጠ ነዉ በማለት፡ በስርአቱ አገላለፅ በዉጭ ሃይሎች የተማረኩ ናቸዉ ሰለ ተባሉ፡ በልዩ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ እጁን አስገብቶ በመፈተሽ፡ ለነዚህ ባለስልጣናት ሲያስወግዳቸዉ ታይቷል። ይህን የመሰለ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሰነጣጠቅ ደግሞ ትልቅ የፖለቲካ መሻከር የፈጠረዉ በአጠቃላይም አጋር የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ድርጅቶች ኪዳናቸዉ ወደ ማፍረስ ወደ መፋታት አቅጣጫ እየሄዱ ያሉ የሚያስመስል ስእል ነዉ ለህዝቡ እያሳዩት ያሉ። በግልፅም ያለዉ ነገር እሱ ነዉ። ሆኖም ግን በድርጅቶቹ መካከል እንደዚህ አይነት መሰረታዊ ችግር እያለ ለሰፊዉ ህዝብ ግልፅ በሆነ መንገድ ስርአቱን ተገምግሞ ባልተፈታለት ስአት እየተካየደ ያለዉን በጥልቀት መታደስ የተባለዉ ተግባር፡ እንዴት ብሎ ተአማኝነት ይኖረዋል? በመሰረቱም የተራራቀ ልብ የያዙ ድርጅቶች ያቀፈ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ እንዴት ባለ መንገድ ሊራመድ እንደሚችል እንደ ሃሳብ አስነስተህ ሲታይም በመሰረቱ ችግር ያለበት ነዉ።



እንደዚህ ባለ መሰነጣጠቅ እያለ የዉስጥ ችግሮች ተባብሶ እየቀጠለ ባለበት ወቅት ስርአቱ በጥልቀትና በግልፅ እስካልተፈተሸ ድረስ፡ ከአራቱ ድርጅቶች ተዉጣጥተዉ በፌደራል የተሰባሰቡ ሰዎች፡ የየራሳቸዉ መስተዳደሮች ለማጠናከር በአንድ በኩል፡ በሌላ በኩል ደግሞ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መስመር ለማጠናከር የሚሉት እንቅስቃሴ ለማድረግ እያሰቡ እንደዚህ ባለ በተመሰቃቀለ ሃሳብ ዉስጥ እያሉ፡ የሚደረግ ህዳሴ ዉጤታማ ሊሆን ወይም ላይሆን እነዚህ እስካልተፈቱ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መንገድ የሚጠገን አይሆንም። ሆኖም ግን ስርአቱ በርግጥ እታደሳለሁ እመኑኝ እያለ ነዉ ቃል እየገባ እየተመፃደቀ ያለዉ። ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የሚለዉና የሚተገብረዉ ሁለት ጫፍ ይዞ ወደየአቅጣጫዉ እየተጓዘ ቆይተዋል። ምጥና የስርአቱ እቅድ በዙ ሳይቆይ የሚረሳ ጉዳይ ነዉ።

## <u>የስርአቱ ጉዞ የተንጠባጠበ ነዉ። ለምሳሌ</u>

ወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የአምስት አመት መርሃ ግብር (እቅድ) እድገትና ትራንስፎርመሽን የሚለዉ ባሳለፍነዉ አመት ከአንድ ደረጃ ወደ አንድ ደረጃ ከ1ኛ ወደ 2ኛ ተሸጋግረናል ማለቱ ትርጉም ያለዉ ሊሆን አይችልም። በ2ኛዉ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድም ግብርናው ኢኮኖሚዉን በመምራት ይቀጥላል በማለት ነዉ ስርአቱ አስምሮበት ያለፈ። ግብርናው በራሱ እቅዱ በቃል እንደሚባለዉ መዋቅራዊ ሽግግር ሊያመጣ ወደሚችል የእድገት መንገድ ሳይሆን፡ እንደ ድሮዉ በያንዳንዱ የቤተሰብ አባላት ያተኮሩና በጣም የተቆራረጡ አይነት ስራዎች ነዉ ትኩረት የተሰጠዉ።

እንደ ቲማቲም፣ ድንች፣ ሰላጣ፣ ጥቅል ጎመን ወዘተ በአጠቃላይ በብዛት ሊባል በሚችለዉ መንገድ፡ ዝርዝራቸዉ በመጥቀስ እስከዚህና ይሄን ያክል መቶ በመቶ እናሳድጋለን የሚሉ ቃላት ነዉ ለእቅዱ ሽፍኖት የምናገኘዉ ብቻ ሳይሆን፡ እቅድ ማዉጣት ለተግባራዊነቱ ግን ችላ በማለት ይተገበራል ወይ አይተገበርም ፈፅሞ የማያስተማምን አልተተገበረም ተብሎ ተጠያቂ አካል የሌለዉ ሂደት እያሳየን መጥቷል። በመጀመሪያው እቅድ የተያዙ እቅዶች ደግሞ ግማሻቸዉ ወደ 2ኛዉ እያሻገረ፡ እንደዚ ባለ እየጎተተ ጉዞ እንዴት ብሎ ነዉ እንድገት ሊያመጣ የሚችለዉ። ኢኮኖሚያዊ ልማት በማስመዝገብ የህዝባችን ኑሮ መካከለኛ ገቢ ካላቸዉ የሃገራት ዜጎች፡ ህዝባችንም ወደዚህ ተርታ እናሰልፈዋለን የሚል ፉከራ የስርአቱ የእድሜ ማስረዘምያ ተንኮል ነዉ። ሌላ ደግሞ ለጤናና ትምህርት ዘርፎች የዉሃና

አገልግሎት ዝርጋታ የሚመለከት፡ እቅዱ ለነዚ ርእሰ ጉዳዮች ያሉን ከፍና ዝቅ ያሉ ያልተሻገርናቸዉ ችግሮች ለመሻገር ጥረታችን በተጠናከረ መልኩ እንሰራለታለን ተብሎ ወደ 2ኛዉ እቅድ ለመሻገር ችሏል።

የትምህርት ጥራት ከ80% በላይ፡ እንዲሁም የጤና ሽፋንና የዉሃና የመሰረተ ልማት አገልግሎት ዝርጋታ ከ90% በላይ አድርሼ የሚል ድምዳሜ ያለዉ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ፡ በነዚህ ሴክተሮች ምን አዲስና ሰፊ እቅድ ልይዝ ይችላል? የመድሃኒት አቅርቦት 80% ከዉጪ በሚመጣ መድሃኒት የሚሸፈን ሆኖ እያለ፡ እዚህ ላይ ብዙ ሊሰራ የሚገባዉ ያልተሰራ እያለ በጤና 90% አስመዘገብን ማለታቸዉ ማንን ለማሳመን ብለዉ እየተናገሩ እንዳሉ አይገባቸዉም። በጣም የሚያሳስብ ግን እንደዚህ አይነት አገላለፅ ከሆነ፡ ከ5-10 አመታት ባለዉ ግዜ ዉስጥ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በነዚህ የተጠቀሱ አንዳንድ ሴክተሮች የሚኖረዉ አፈፃፀም 100% ይደርስና በቀጣዩ የሚያቅደዉና የሚሰራዉ ወደ ማጣት አቅጣጫ እያመራ እንዳለ በሚያስመስል መንገድ ነዉ የማታለያ መላዉ ግልፅ እያደረገዉ ያለ። ይህ ህዳሴ እየተባለ ያለዉ አሁንም ከዚ የሚያልፍ አይሆንም። እንዴት በስልጣን ላይ መቀጠል ይቻላል ተብሎ እንደ ፖሊሲ ተይዞ እየተደረገ ያለ መላ በሆኑ ግን መታወቅ አለበት።

በ 1ኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ 10 የስኳር ፋብሪካዎች ለመገንባት ተይዘዉ ከነበሩ ተላላቅ ፕሮጀክቶች ትልቁና ዋናዉ ሆኖ ሲያበቃ፡ ይህንን ለመገንባት አቅም ነበራቸዉ ወይ? እነዚህ ፕሮጀክቶች የሚገነቡበት ቦታዎችስ ምን አይነት ብቃት ነበራቸዉ ከተባለ፡ ስለ ግንባታዉ ካለ የኢትዮጵያ ዉሃና ሊለማ የሚችል መሬቱ ፀጋዉ ፈሶ የሚተርፍ ነዉ። ሆኖም ግን ታስቦበት፣ ዉይይት ተደርጎበት፣ በቂ የሆነ በባለሙያ ጥናት የተደረገባቸዉ፣ በቂ በጀት የተመደበላቸዉ ሳይሆን፡ በትግራይ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በአፈርና በደቡብ ወዘተ ይሰሩ ተብለዉ በደመነፍስ የተቀመጡ እንጂ፡ እንዴት ይፈፀሙ የሚለዉ ግንዛቤ ሳይጨበጥ የተወሰደ እርምጃ ነዉ የነበረ። ይህ ደግሞ በሃገሪትዋ ላጋጠመ የስኳር እጥረት ተከትሎ በዜጎቻችን ላይ ለተፈጠረ ቅሬታና ላጋጠመ የገበያ መዛባት፡ ለዚህ ችግር ለመፍታት ቆርጬ ተነስቻለሁ የህዝብን ድምፅ የሚሰማ ጆሮ ይኖረኛል ብሎ የህዝብ ልብ ለመስረቅ የተያዘ እቅድ እንደነበረ ግን የሚያጋልጡ መረጃዎች አሉ። በየጊዜው ችግሩ በተለያዩ ወገኖች እየተገለፀ ቆይቷል። ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ግን የተለያዩ ምክንያቶች እያቀረበ ቆይቷል አሁንም እያቀረበ ነዉ።

እነዚህ ፕሮጀክቶች እስከ አሁን ያልተከናወኑ በመሆናቸዉ ግን በጥር 4/2009 ዓ/ም ጠቅላይ ሚኒስተር ሃይለማርያም ደሳለኝ ጠቅላላ የ6 ወር የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የስራ አፈፃፀም ሂደት ለፓርላማ አባላት በሰጠዉ ማብራርያ፡ "በግዜዉ አይናችን ጨፍነን የወሰድነዉ እርምጃ እንጂ፡ ጥናት ሳናካይድ ግንዛቤ ሳይኖረን የወሰድነዉ እርምጃ ስለ ነበር እስካሁን ችግሩ ቆይቷል፡ በዚህ ሰአት ግን የተወሰኑ ስራቸዉን እየጀመሩ ነዉ" ብሎ ያምነ ሲሆን፡ ለዚህ ለማፍረስ ደግሞ፡ "ጥናት ሳናደርግ አስር ፕሮጀክቶቹ በአንድ ጊዜ የጀመርናቸው ብንሆንም፡ እስከ አሁን ሊከናወኑ ያለመቻላቸዉ፡ የጥናት ችግር ቢሆንም በድምር ስናየዉ ግን ዉጤታማ ነዉ ምክንያቱም ለጥናት ጊዜ መድበን ብንሰራ ኖሮ የፕሮጀክቶቹ ግንባታ ዘግይተን መጀመራችን አይቀርም ነበር። ስለዚ መጓተቱም መቀጠሉ አይቀርም ነበር ማለት ነዉ" የሚል መልስ ነበር የሰጠዉ። ይህ ደግሞ የስርአቱ ከሃዲነት የሚያረጋግጥ ተግባር መሆኑን የሚያሳይ ነዉ። ይህን የመሰለ መልስና ጉዞ ደግሞ የስርአቱ ባህሪ ነዉ።

መታደስ የሚባለው እንዳለ ተወስዶ በተለይ በጥልቀት የሚለዉ ነጥለን ስናየዉ፡ በጥልቀት ቢሆን ኑሮማ ከላይ ለተነሳ ሃሳብ ጭምር ነበር ማጠቃለል የነበረበት። ካልሆነ ግን ብቃትና አቅም፣ የኪራይ ሰብሳቢ፣ የስስትነት፣ ቆራጥ የህዝብ አገልጋይ አለመሆን ይህ ብቻ

ነዉ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ችግር ብለህ ላዩ ላይ ዳሰስ ዳሰስ አድርገህ መሄድ ከሆነ፡ በጥልቀት መታደስ የሚለዉ አሰራር ለማንም ተዉጠለት የሚሄድ አይደለም።

በግምገማዉ መሰረትም ከአማራ ክልል ከብ.አ.ዴ.ን ወደ 700 የሚሆኑ አመራሮች ከዞን ጀምሮ እስከ ወረዳዎች በግምገማዉ መሰረት ሰዎች ገለል በሉ እንደተባሉ ከሌሎችም በተመሳሳይ ገለል በሉ እንደተባሉ በስርአቱ እየተገለፀ እንዳለ እየተሰማ ነዉ። ይህ ብቻ ሳይሆን አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ እንደሚወስድባቸዉ መንግስት ለዚህ በሚመች መንገድ አሰራሩን አስተካክሎ እንደሚገኝ ሃይለማርያም ደሳለኝ በራሱ ገልፆታል። ቀደም ሲል በኦ.ህ.ዴ.ድ ብቻ የተወሰደ እርምጃ ካልሆነ በስተቀር፡ በከፍተኛ ባለስልጣናት በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ከጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማርያም ደሳለኝና ምክትሉ በህ.ወ.ሓ.ት.ም እንዲሁ በብ.አ.ዴ.ንና ደ.ህ.ዴ.ንም በተመሳሳይ የበላይ አመራሮቹ እንዳሉት በስልጣን እየቀጠሉ ነዉ።

ከነሱ በታች ባሉ ብቻ ትኩረት ማድረግ ግን በጥልቀት እየተባለ ያለዉ ጥልቀት የሌለዉ መሆኑን ነዉ የሚያሳየዉ። እየተካየዱ ካሉት ግምገማዎች ህብረተሰቡ እያሰማዉ ያለ ድምፅ ምንድነዉ ካልን ከስርአቱ ፈፅሞ ተስፋ እንደቆረጠ፡ ከሞተ ተስፋ ማግኘት አንችልም ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መጨረሻ ዉድቀቱ ላይ ስለ ደረሰ፡ ያለዉን አቅሙ አሟጦ እንዴት ብዬ ነዉ መዳን የምችለዉ ብሎ፡ በስርአቱ አንገት ላይ የገባችዉን ገመድ እንዴት መዉጣት አለብኝ የሚል መሆኑ፡ የህዳሴዉ ዋነኛ ስበት እሱ ነዉ ብሎ ጥምር ባለ ሃሳብ ህዝቡ ለስርአቱ እየነገረዉ ነዉ። ታድያ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ይዞት ባለ አካሄድ በጥልቀት ሊታደስ ይችላል ወይ? በዚህ ወደ ታችኛዉ ብቻ ያነጣጠረ ተሃድሶስ በህዝብና ሃገር እየወረደ የቆየና ያለ በደል ሊቆም ይችላል ወይ? በህዝቦችና ድርጅቶች መካከል ያለዉን አለመግባባትና መወነጃጀልስ እልባት ሊያገኝ ይችላል ወይ? ከተባለ ግን መልሱ ጊዜ ጋህድ ያደርገዋል ነው።

## የወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ስርዓት በስልጣን እየቀጠለ፡ ያለበት ምክንያት ምንድን ነው?

ጀርመን የተለያዩ ዘሮች (races)፣ ቋንቋዎች፣ ባህሎች፣ እምነትና ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ወዘተ የነበራቸው ህዝቦች አንድ ሆነው የሚኖሩባት አገር የነበረች ብትሆንም፡ ሂትለር ከ1933-1945 ዓ.ም የፋሺዝምና የናዚዝም ፖለቲካ ስነ ሃሳብ መስርቶ ጀርመንና አለምን ለመግዛት ሲሞክር፡ መጀመሪያ ያደረገው ህዝቦችን መበታተን ነው። በመሆኑም ዓለምን ልንገዛት እንችላለን ወዘተ በሚል ቅስቀሳና ፕሮፖጋንዳ በርከት ያለ ቁጥር ያላቸው ፖሊሽያውያን፣ ሩስያውያን፣ ዩክሬናዊያን፣ ስላቮውያን፣ ጥቁሮች፣ ጅፕሳውያን፣ ሮማውያንንና አካል ጉዳተኞችን ወዘተ ያለፍርድ በጅምላ እንደጨፈጨፈ ይታወቃል። የሂትለር ቀኝ እጅ በነበረው አዶልፍ ሃይክማን ትዕዛዝ መሰረት 6 ሚሊዮን አይሁዳውያን በመርዛም ጋዝ በማፈን የተፈፀመ ወንጀል ሸውአህ (shoah) በተባለ የአይሁዳውያን ቋንቋ ፍፃሜውን ሆሎኮስት ብለው ይጠሩታል።

ለመግቢያ ያህል ይህንን ካልን ከዚህ በማይለይ በገዛ ህዝቡ ላይ አረመኔያዊ ጭፍጨፋ እየፈፀመ ወዳለው የአገራችን ስርዓት እንሻገር፦ በ21ኛው ክ/ዘመን በ1983 ዓ.ም ወደ አገራችን ኢትዮጵያ የመጣው ቡድን ማለትም የወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ስርዓት በአገራችንና በህዝባችን ላይ የፈፀመው ግፎች ማለቂያ ስለሌላቸው የተወሰኑትን ለመጥቀስ እንሞክር። ይህ ከ1900 እስከ ሰኔ 28/1919 እ.ኤ.አ የተመሰረተው (League of Nations) እየተባለ የሚታወቀው የወቅቱ የአለም የተባበሩት መንግስታት ተቋም ከመመስረቱ በፊት፡ የሞቶ ዓመታት እድሜ ይዞ የቆየውንና ታላቅ እውቅና የነበረው ክቡር የአገራችንን ባንዴራ ጨርቅ ነው ብለው ወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ለሚገዛት ኢትዮጵያ አይወክልም በማለት አጣጥለው የራሳቸውን ምልክት እየተጠቀሙ ነው።

በአንድነት ተሳስረን የመጣን አንድ ልብ፣ አንድ አገራዊ ስነልቦና ያለን ለሺህ አመታት እንደ አንድ ህዝብ የነበርነ ኢትዮጵያውያንን በክልሎች ከፋፍሎ እርስ በርሳችን እንድንገዳደልና በጠላት አይን እንድንተያይ ፈርዶብናል። ፋሽስታውያኑና ናዚያውያኑ ለፖልሽያውያን፣ ለጅፕሳውያን፣ ለሰርባውያንና ለጥቁሮች እንደጨፈጨፉ፡ የወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ስርዓትም ኦሮሞን፣ ጋንቤላን፣ ለኮንሶ፣ ለአማራ፣ ለቤንሻንጉልና ለትግሬ በዚህ በቅርቡ ቀን ደግሞ የዲላ ነዋሪዎችንና ጉራጌን ወዘተ በጅምላ ጨፍጭፏል።

ፋሽስቱ ናዚ ጀርመን የጀርመን ህዝብ የሚናገረውን፣ የሚያደርገውን፣ የሚያስበውን፣ የሚበላውንና የሚጠጣውን ለመሰለል በፖለቲካና ሲቪክ ተቃዋሚ ድርጅቶች ውስጥ ሾልከው በመግባት በገሃድ በማዳከምና የጀርመን ፋሽስታዊ ስርዓት እድሜ ለማስረዘም ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። በአገራችን ደግሞ ሁላችን እንደምናውቀው አንድ ለአምስት በሚል አደረጃጀት የወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ካድሬዎች በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የጋስታፖውያን አይነት ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ። ማለት አጋዚና የፌደራል ፖሊስ እንደ ናዚ ፋሽስት ፓርቲ (Crops of Nazi Party) እንደ ማለት ነው። ህዝባዊ አመፅን ማፈን፣ ንፁሃን ዜጎችን ማሰር ወዘተ የመሳሰሉ ግፎችን በመፈፀም ላይ ይገኛሉ።

የናዚ ጀርመንን ፍርድ ቤትና ወንጀል የሚመሩ ከታችኛዎቹ ዳኞች ጀምሮ እስከ ላይኞቹ ፕሬዚደንት የፍትህ ተቋማት የሞትም ይሁን የእስራት ፍርድ እንዲፈርዱ የጀርመንን የዳኝነት ህገ መንግስት ተከትለው ሳይሆን፡ የናዚ ፓርቲ በሚያወርድላቸው መምሪያና ትዕዛዝ ነበር። በተመሳሳይ በዘመነ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ያለው የፍርድ አሰጣጥ ዳኞች በዜጎቻችን ላይ እየፈረዱት ያሉት የፍርድ ሂደት ወይም የፍርድ መመሪያ ተከትለው ሳይሆን የወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ሹመኞች በሚሰጧቸው ትዕዛዝ ነው የሚፈፀመው። በዚህ ደግሞ የቀልድ፣ የይምሰል፣ ኢ-ፍትሃዊ የሩጫ ፍርድ፣ የጭካኔ፣ የአድልዎ፣ እንደተመቻቸው ቅንነት የጎደለው ፍርድ እየሰጡ ይገኛሉ።

የወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ስርዓት የኢትዮጵያን ህዝብ ከእነ ሙሉ ሃብተ ገነቱ የዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ባለመኖሩ ምክንያት በረሃብና ድህነት እየተሰቃየ ይህንን ተከትሎም ህዝባችን በህመም እየረገፈ በሚገኝበት ወቅት ስርዓቱ ግን በኃያላን አገሮች ጫማ ስር ወድቆ ለጥቅማቸው የሚገለባበጥ በመሆኑ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ህዝብ እየተጨፈጨፈ እንኳ የሚያስጨንቃቸው ነገር አይደለም። “በቀንድ እየወጉ በጭራ እሽ ማለት” እንደሚባለው ይህ ስርዓት ከተመሰረተበት ጀምሮ እስካሁን ቃል ኪዳኖችን እየደረደረ ፖለቲካዊ ጥቅሙን ብቻ ይጠቀማል። ለምሳሌ በ1983 ዓ.ም የገባው ቃል “ህዝብ በቀን ሶስት ጊዜ በቀን ዳቦ ሊበላ ነው” የሚል ንግግር ነበር። በኋላ ግን እንኳንስ ሊበላ ይቅርና በረሃብ አለንጋ ተገርፏል። ለዚህ የቅርብ ምስክር ሊሆነን የሚችል በ2008 ዓ.ም በታየው አስገራሚ ድርቅ በርከት ያሉ ወገኖቻችን በምግብ እጥረት ምክንያት እንደቅጠል እረግፈዋል።

ይህ ስርዓት በየአመቱ እቅድ እያስመሰለ ህዝብን ማደናገር ራሱ የከፋ ማታለል ነው። በ1993 ዓ.ም የሣይንስ ተሃድሶ መልካም አስተዳደር የሚል እቅድ አውጥቶ የነበሩት የአመራር አካላት እንዲከፋፈሉ አድርጓል። ይህ ደግሞ ራሱን የቻለ የፖለቲካ ሸቀጥ ሆኖ ስለስልጣኑ እንጂ ስለሃገርና ስለህዝብ የማያስብ ስርዓት በመሠረታዊ ልማት ከፍተኛ ችግር እያለ ጥሩ አለን እንደሚል የሚያስረዳን ነው። በመሠረቱ በአገራችን ኢትዮጵያ እስካሁን ወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ስርዓት በመርሃ ግብር መዋቅር DOP (declaration of principle) ብቻ ይዞ ነው የሚንቀሳቀስ እንጂ፡ እስከዚህ አመት በየአምስት አመቱ መርሃ ግብር ነው ይዞ የሚንቀሳቀሰው። በየዓመቱ የማይገመገም መርሃ ግብር ከስራ አፈፃፀም ውጭ መሆኑን ማንም የሚስተው አይደለም። ኢሃዴጋውያን ይህንን ጉዳይ ልክ እንደ ሽፋን ነው የሚጠቀሙበት።

አንዳንድ ምሁራንን በገንዘብ እያታለሉ በመርሃ ግብሩ ላይ በየአመቱ አዲስ እቅድ አውጥቶ ይዘረጋል። የስራ አፈፃፀም አስመስሎ ምሁራንን ጣልቃ ማስገባት እየተገበራቸው ከሚገኙት የሙስና ተግባሮቹ አንዱ ነው። ለምሳሌ መምህራንን፣ ሐኪሞችን፣ የግብርና ሠራተኞችን ውጤት ተኮር የሚል አሰራር በ1996 ዓ.ም በማስገባት እነዚህ የሙያ ሰዎች እንዲሸማቀቁና ሙያቸውን እንዲጠሉ ትልቅ ሚና ተጫውቷል።

እንዲሁም በ1998 ዓ.ም ሁሉም የመንግስት ሰራተኛ የወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አባል መሆን አለበት በሚል ተግባር ምሁር ሃይል ለስደት፣ ለእስራትና ለመታገት ተጋልጧል። በአገራችን ኢትዮጵያ መርሃ ግብር (DOP) አፋኙ ስርዓት በሚጠቀምበት እንጂ ህዝብን በሚያገለግል መንገድ ተዋቅሮ አይወጣም። በአንድ አገር ለማንኛውም ስርዓት መንግስት ሊያሰኘው የሚችል ነገር ካለ አንዱ ህዝባዊ መዋቅርና ህዝባዊ ተቀባይነት ነው። መዋቅሩ ማሰሪያ የሌለው መንግስት ሁል ጊዜ እንዳጭበረበረ ነው። ለዚህ ምስክር ሊሆን የሚችል የወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ስርዓት አንደኛው ጉድለት ኤፒኤን ነው። ይህ ማለት አንዲት አገር አመታዊ በጀቷ ዓመት ሙሉ ተጠቅማ በአመቱ መጨረሻ የወጣው በጀት በሙሉ ዝርዝር ማስረጃ ሊያቀርብ የሚችል የኢኮኖሚ ዘዴ ነው። ስለዚህ በአገራችን በጀት ማስላት እንጂ የተጠቀመበት በጀት ለህዝብ ይፋ እንዲሆን አይፈልግም። ምክንያቱም ስርዓቱ በሚያጭበረብረው የገንዘብ ወንጀል ተጠያቂ ስለሚያደርገው።

ህዝባችንና አገራችንን ወደኋላ እየጎተተ ግን ደግሞ በጣም ሊያታልሉ በሚችሉ ተግባሮች እየተሽሎከሎከ የሚሄደው ስርዓት ከእንግዲህ የውድቀት ጊዜው እየደረሰ ነው። ምክንያቱም ህዝቡ አካሄዱን ተርድቶት ስላለ። ወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ እስከዚህ ሰዓት ማስተር ፕላን እንጂ ዝርዝር ፕላን የለውም። ይህ የሚይስረዳህ በእያንዳንዱ የኢትዮጵያ ከተሞች የሚያደርገው አገባብ የሌለው ተራ ምህንድስና ነው።

- በመጀመሪያ ነገር ጥሩ ከተማ በመሠረተ ልማት ስር ነው።
- ሁለተኛ አንድ ከተማ ካርታ ሊይዝ ከሆነ አስቀድሞ ማህበረሰቡ ምን ያስፈልገዋል የሚል ጥናት ማካሄድ ይገባል።

ይህንን ጉዳይ ሊይስኬደው የሚችል አካል ደግሞ ዝርዝር ፕላን እንጂ ማስተር ፕላን አይደለም። ይሁን እንጂ ይህ ጉድለት ስላለ ህዝብ በድንገት ከመሬቱ ይፈናቀላል። ይህ ማለት አንድ የግል ባለሃብት ከ300 ሰዎች መሬት በላይ ያካብታል። ደሃዎች መኖሪያ አጥተው ለስደት ይጋለጣሉ። የመሬት ሃላፊዎችና የመሬት ዳኞች ደግሞ በጉቦ እየተጨማለቁ በሙስና ወጥመድ ስርነው የሚገኙ። በህዝብና በሃገር ኋላቀርነት ትልቅ ሚና እየተጫወተ የሚገኘው የወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ስርዓት እቅድንና ቃልን እያደባለቀ ህዝባችንን ሲያደናግር ቆይቷል አሁንም እያደናገረ ይገኛል።

በሚሊንየም ውስጥ የገባው ትራንስፎርሜሽን የሚባል አሰራር ለህዝብ ብቻ ሳይሆን መዋቅሮቹንም አደናግሮበታል። ምክንያቱም የአምስት አመቱ መርሃ ግብር የእድገትና ሽግግር እቅድ ሊያገናኝ ባለመቻሉ ስርዓቱ ወደ አዘቅት ገብቷል። በከተማና በገጠር የነበረው መዋቅር አሰራሩ ለየብቻው ስለቆየ የአንድ ከተማ መዘጋጃ ቤት ስራዎች ከዞኖች ጋር ዝምድና ስላልነበረው በአጠቃላይ የአስተዳደር ሂደቱ ስላልጠበቀ ትራንስፎርሜሽኑ አብዛኛውን ህዝብ በድሏል። ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በኋላቀር አስተሳሰቡ ህዝብ ሊቀበለው ስላልቻለ በ2001 ዓ.ም ደግሞ BPR ማለት (መሰረታዊ ለውጥ የስራ ሂደት) የሚል አሰራር በአሜሪካ ከሚገኝ የሳሙና ፋብሪካ አምጥቶ በማስገባት በምሁር ሃይልና ማህበረሰብ የፖለቲካ ሽቀጥ ጀምሯል። የሚያስገርመው ይህ አሰራር **"እስፈላጊ ከሆነ ሰው መግደል ወንጀል አይደልም"**

የሚል መፈክር አለው። ይህንን ሁሉ በማየት ምሁር ሃይልና ወጣቱ ትውልድ ደግሞ ሙሉ በሙሉ እቅዱን ሳይቀበለው ቀርቷል። የዚህ እቅድ ዋና አላማ ደግሞ ባለሙያዎችን ማዳከም ነው።

ወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ማህበረሰቡ ውድቅ ስላደረገው ነው ልማታዊ መንግስት የሚል አዋጅ የጀመረ። ይህንን የታዘቡ የዩኒቨርሲቲ ምሁራን ወያኔያዊ አብዮታዊ የሚባለው መንግስት ወደየት ሄደ ብለው ባስነሱት ጥያቄ እናንተ አሸባሪዎች ናችሁ እያለ ብዙዎችን አጥፍቷል። በተለይ ደግሞ የዩኒቨርሲቲ መምህራንን፣ ዶክተሮችን የህግ ምሁራንን ትልቅ ጫናና ማስፈራራት አድርሶባቸዋል። ወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ስርዓት ኢንፍራስትራክቸር (መሠረታዊ ልማት) የሚባል በየአመቱ ተቀያያሪ መዋቅር ያደርጋል። በተለይ በሥርዓተ ትምህርት ዘርፍ ማለቂያ የሌለው ሙስና እየተፈፀመ ነው የሚገኘ። በጣም የከፋው ደግሞ በቴሌኮሚዩኒኬሽን ያለው ተፅዕኖ፣ አፈና፣ ጠለፋና መስመር መዝጋት እየፈፀመ ህብረተሰባችንን የቴሌፎን አጠቃቀሙ በቁጥጥሩ ስር አድርጎት ይገኛል። ይህ ሳይበቃ ከሚጠቀምበት በላይ የሚከፍለው ይበዛል፡ ስለዚህ ስርዓቱ አፋኝ መሆኑን የሚያስረዳ ትልቅ ምሳሌ ነው።

የወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ስርዓት በህዝቡ ላይ የሚያደርገውን በደል በደንብ ያውቀዋል። ስለሆነ ደግሞ በንፁሃን ደም ነው ቁማር እየተጫወተ ያለው በምርጫ ወቅት ምርጫው አንድ ሳምንት ሲተርፈው Psephology (ሰ-ፎሎጂ) የሰዎች አመራረጥ በመረጣ ወቅት የሚደረግ የጥናት አግባብ ይከተላል። ስለዚህ የፖለቲካ ተቃዋሚ ድርጅቶች የሚመስሉ በራሱ በጀት ያዳርሳል ያደራጃል በመጨረሻ ደግሞ ያደራጃቸው አባሎች የፓርቲው አላማ እንዲፈራርስ ያደርጋሉ። ለዚህ በምሳሌነት ስንወስድ ያለፉትን ለይምሰል የተደረጉትን ምርጫዎች ወደ ጎን ትተን፡ ባለፈው የአምስተኛ ዙር 2007 ዓ.ም ምርጫ የነበረው አብዛኞቹ ተቃዋሚ ድርጅቶች የሚመስሉ ግን ደግሞ ያልሆኑ የእነዚህ ፓርቲዎች ዋና አስተባባሪ የወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ካድሬዎች በመሆናቸው፡ በመጨረሻው ወቅት ምርጫው ይዘውት የነበሩትን የሐሰት አላማ በመተው ህዝብ እንዲደናገር አድርገዋል።

በዋናነት በፖለቲከኞችና (በፖለቲካ ምሁራን) በውጭ ሃይሎች ለወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ሊያስነቅፈው የሚችል ትልቅ ምክንያት የሚሉት መዋቅር ፓርላመንታዊ ስርዓት ነው። በአሁኑ ወቅት የፓርላማ ወንበሮች ሙሉ በሙሉ በወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ነው ተይዞ ያለው። አንዲት አገር ዴሞክራሲያዊ ስርዓት አላት ልትባል ከሆነ ግን የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን ካሳተፈና በፓርላማው ውስጥ የተማከለ ወንበር ሲኖር ብቻ ነው። ለዚህ ሊመሰክርልን የሚችል እውነታ በአገራችን ኢትዮጵያ ይህ ስርዓት ከሚመጣ ጀምሮ Praesidium (ቋሚ ማዕከላዊ ሸማግሌ) ስለሌለ የመንግስት መዋቅር ስርዓት ህላዌ በገዥው ስርዓት ብቻ ይማከላል ማለት ነው ይህ ማለት ደግሞ አምባገነንነት የሰፈነበት አገዛዝ ነው።

ወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ከውጭ አገሮች ጋር ያለው ዝምድና በተወሰነ መልኩ ብልጭ ብሎ ሊታይ የሚችል የጥቅም ዝምድና ይመስላል። ይሁን እንጂ ፖለቲካዊ ተግባር የተላበሰ ዝምድና ነው የሚተገብር በተለይ ከአሜሪካ ጋር ያለው ዝምድና Neo-Colonialisl በሌሎች አገሮች ተፅዕኖ ለማሳደር ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና መፍጠር የሚል አሰራር በመጠቀም ኢትዮጵያ ከአሜሪካ ጋር ዝምድና በመፍጠር በምስራቅ አፍሪካ በተለይ ደግሞ በአፍሪካ ቀንድ ለሚገኙ አገሮች ትልቅ ቀውስ ለመፍጠር የታቀደ የሁለቱም ተንኮል ተብሎ ነው የሚገለፅ። በተለይ ደግሞ ይህንን ሂደት በተለያየ መልኩ ወደ ትልቅ ጥቅም በማስገባት ልትጠቀምበት የቻለች አገር አሜሪካ ናት።

ምክንያቱም ኢትዮጵያ በመሠረተ ልማት ትኩረት አድርጋ ልትሰራና በፍትህና ዴሞክራሲ ትኩረት እንድታደርግ የሚገፋፋ የአሜሪካ መሰረታዊ ጉዳይ ስለላልሆነ ህዝብና

አገር እየታመሰ ገኘ[illegible]ው ስርዓት ወይም ወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የአሜሪካ አገልጋይ ሆኖ እንዲቀጥል ስለምትፈልገው ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የአገራችን ዜጎች በየአቅጣጫው እየተሰደዱ በተለያየ የአፍሪካ አገሮችም ሆነ የአውሮፓ አገሮች በተወሰነ መልኩ ስምምነት በመፍጠር ስርዓቱን ሊያሰጋው የሚችል ኢትዮጵያዊ ዜጋ ካለ በኤክስ ትራዴሽን (አሳልፎ መስጠት) መልክ ዜጎች እየተጠለፉ ለማጥፋት የሚያደርጉት ሙከራዎችም አሉ። ይህ በዚህ እንዳለ በአገር ውስጥ ደግሞ ብዙ ታላላቅ ምሁራን፣ ፖለቲከኞችና ጋዜጠኞች የመፃፍ መብታቸውን በማፈን ስርዓቱን የሚነቅፍ ፅሑፍ ከፃፉ ከህግ ውጭ ዶክሜንታቸውን



ከኮምፒውተራቸው በመውሰድ ከባድ የሰብዓዊ መብት ገፈፋና የዜጎች አፈና እያደረጉ ነው። በአንድ ጉዳይ በህዝብ ዘንድ ትልቅ ተሰሚነት ያላቸውን ዜጎች ደግሞ እያገተ አስሮ ያጠፋቸውል።

ክቡራን የብስራት መፅሄት አንባቢዎች ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ከሚፈጠር ጀምሮ እስካሁን ድረስ የራሱን አለም ለመገንባት ካለው የማይጨበጥ ህልም ተነስቶ፡ በህዝብና በአገር ላይ ከባድ ግፎች እየፈፀመ የመጣ ስርዓት ነው። ታዲያ እነዚህና ሌሎችም ማለቂያ የሌላቸው በደሎች በአገርና በህዝብ የሚያደርስ ስርዓት እስካሁን ድረስ በስልጣኑ እንዲቀጥል እያስቻለው ያለው ምክንያት ምንድነው ትላላችሁ? እስካሁን ወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በስልጣን እንዲቆይ ያስቻለው የሚጠቀምባቸው ተንኮሎች በጣም ብዙ ናቸው። ከጊዜ ወደ ጊዜ እንደ እስስት እየተገላበጠ የሚጠቀምባቸው የማደናገሪያ ዘዴዎች ማለቂያ የላቸውም ከእነዚህ ግን እስኪ የተወሰኑትን እንጥቀስ፦

1.በየአመቱ የማይተገበር የእቅድ ስም መቀያየርና የአንድ ለአምስት የኔትወርክ አደረጃጀት ማስፋፋት።

2. ሰነዱን ያላሟላ ለስርዓቱ በሚመች መንገድ የተለያዩ ሥልጠናዎችን መስጠት ለምሳሌ ካይዘን ከጃፓን የወረሰው የአስተዳደር ተግባር በህዝብ ላይ መጫንና ትርጉም የማያመጣ ኮንፈረንሶችን ያለወቅቱ ማብዛት።

3. የህገመንግስቱን አዋጅ ያላሟላ መዋቅር መከተል።

4. የብሄር ብሄረሰቦችን ሃብት የኢትዮጵያን አንድነት ምክንያት በመጠቀም ለፖለቲካዊ ጠቀሜታ በማዋልና መልካም አስተዳደርን ማንግስ በሚል ሃሳብ እያቀረበ ህዝብ እንዲደናገር ማድረግ።

5. በተግባር የማይሰራ አብዮታዊ ዴሞክራሲ፣ ልማታዊ ዴሞክራሲ፣ ሪፐብሊካዊ፣ ፌደራላዊ የሚሉና በየጊዜው የሚለዋወጡ የአስተዳደር ስሞች በመከተል ጊዜያዊ ትንፋሽ በመፍጠር።

6. እድሜ ስልጣኑን ለማስረዘም ከታላላቅ አገሮች ጋር ከአገራችን ክብር ጋር የማይስማማ ዝምድና በመፍጠር የተለያየ ስም ያላቸው የፀጥታ አካላት የሚላቸው እንደ ፌደራል ፖሊስ፣ ፈጥኖ ድራሽ፣ ደህንነት፣ ምሊሻ፣ ወታደርና አጋዚ ኮማንዶ እያለ መብቴን ብሎ በሚቃወም ህዝብ በማስፈራራት፣ በማሰር፣ በመግደልና በማገት ዜጎቻችን በጠመንጃ አፈሙዝ ደንግጠው እንዲገዙ ማድረግ።

7. ማህበረሰቡንና ወጣቱን ትውልድ በራሱ ሚዲያ ብቻ እንዲጠመድ በማድረግ ሁሉንም የብዙሃን መገናኛዎች በቁጥጥሩ ስር በማድረግ የህዝብን እውነተኛ መረጃ

የሚያስተላልፉትን ሚዲያዎች በማፈን ህዝባችን የሐገሩን ሀቀኛ ገፅታና አኗኗር እንዳያውቅ ማድረግ።

8. ታላላቅ የትምህርት ተቋማት ዩኒቨርስቲዎች የፖለቲካ ማዕከል በማድረግን ሌሎች ማለቂያ የሌላቸው ሴራዎችን በመጠቀም ሌሎች ያልተገለጡ ስውር መርዞችን በመጠቀም ነው በሥልጣን ኮረቻ ከ25 ዓመታት በላይ ያላንዳች ፍሬ ለመቆየት የበቃው ይህ ስርዓቱ የሚጠቀምበት አሰራር ነው።

በመሠረቱ ግን ወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ እነዚህ ተግባሮች ተግባራዊ ስላደረገ ብቻ ነው በስልጣን እየቀጠለ ያለው ከተባለ ግን መልሱ አይደለም ነው። ምክንያቱም በፖለቲካዊም ይሁን በትጥቅ ትግል ስርዓቱን እናስወግደዋለን በማለት የነፃነት ችቦ አብርተን እየታገልን ያለን ሃይሎችም ስርዓቱ በስልጣን እንዲቀጥል የየራሳችንን አስተዋፅኦ እያደረግን መጥተናል።

ለምሳሌ፦

✓ በአንድ ክልል ወይም አካባቢ በስርዓቱ ላይ የሚካሄድን ተቃውሞ የተወሰኑ ዜጎች ህይወታቸውን ሲከፍሉና አካላቸውን ሲያጎድሉ የተጀመረውን ትግል በቆራጥነት ከማስቀጠል ይልቅ አንተን አምኖ የተሰለፈውን ህዝብ ትተህ ህይወትህን ልታድን ከተቃውሞ ማዕበል መሸሽ።

✓ ሁሉም ተቃዋሚ ድርጅቶች በሚያሰኝ ፕሮግራማቸው አላማቸውና ራዕያቸው አንድ እያለ በአንድ ላይ ተጣምረው አንድ የተዋሀደ ሃይል ከመፍጠር ይልቅ ተበታትኖ መታገል የህዝቡን ድምፅ ወደ ብዙ እንዲከፋፈል ማድረግ።

✓ በስርዓቱ የሚካሄዱ የፖለቲካ ቅስቀሳዎች ተደናግረው በሌሎች ብሄረሰቦች ላይ ጥላቻ ማሳደርና እርምጃ መውሰድ፡ ህዝብ ለህዝብ ተቃቅፎ በለውጥ ማዕድ እንዲያርፍ ከማድረግ ይልቅ እርስ በርሱ የሚያጣሉ ተግባሮችን መፈፀም፡ ለምሳሌ ይሄ ብሄር ተጠቃሚ ነው፣ ሌላው ደግሞ ተጎጂ ነው የሚል ያልበሰለ ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ወደ ህዝብ እንዲሰርፅ ማድረግ።

✓ ተቃዋሚ ድርጅቶች በሚያካሂዱት ቅስቀሳ በቆራጥነት እራሳቸውና ቤተሰቦቻቸው መስዋዕት ለመክፈል ዝግጁ ያለመሆንና በስርዓቱ ቅስቀሳና ማስፈራሪያ ፈርቶ የገንዘብ ተገዥ መሆንና ወደ ስደት ማምራት።

✓ የትጥቅ ትግል የሚያካሂዱ ድርጅቶችንና በውጭ የሚገኙ ዜጎችን በአንድ ላይ ፀንተው አንዲት ጥምርትና የበለፀገች ኢትዮጵያን ለመገንባት ኔትወርክ ሊዘረጉ ያለመቻልና፣ የሚመካከሩበት መድረክ ያለማዘጋጀትና ያለመተሳሰር (ለየብቻ መታገል) ወዘተ ስርዓቱ በስልጣን ላይ እንዲቀጥል የምናደርጋቸው አስተዋፅኦዎች ናቸው።

✓ የአገራችን ብሄር ብሄረሰቦች እርስ በርሳቸው በጥላቻ አይን መተያየት ይህ የወለደው ደግሞ ከማናውቀው መላክ ያወቅነው ሰይጣን ይሻላል በማለት እየተበደሉ ራስን ደፍቶ ዝም ብሎ በማየት የኢትዮጵያን የጀግንነት ባህል ያለመከተል ወዘተ ስርዓቱ በስልጣን እንዲቀጥል የምናደርጋቸው አስተዋፅኦች ናቸው።

ይሁን እንጂ "Necessity is the mother of invention" ማለት **"ችግር ብልሃት ያስተምራል"** እንደሚባለው ይህ ሁሉ ግፍና ተንኮል በህዝባችን ላይ ለሩብ ክ/ዘመን ያህል እየፈፀመው ያለው ዛሬ መፍትሄው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል እየታዘብን ነው። በአሁኑ ወቅት በመላው አገራችን ተቀጣጥሎ ያለው ተቃውሞ ከስርዓቱ ቁጥጥር ውጭ ሲሆን በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የታሰረው አመፅ የዚህ መግለጫ ነው።

**"የታፈነ ሐቅ ሰገባ ውስጥ እንዳለ ጎራዴ ነው"** እንደሚባለው የኢትዮጵያ ህዝብ በስርኣቱ እየወረደበት ላለው በደል ረጅም ጊዜ ጠብቆ ተስፋ ሲያጣ የተለያዩ አማራጮችን

በውጭና በውስጥ ለመወሰን በቅቷል። ከዚህ አንድ ምሳሌ ስናነሳ መተኪያ የሌለው አማራጭ የትጥቅ ትግል ነው ብለው ፊት ለፊት በተደራጀና ባልተደራጀ መንገድ እየታገሉ ያሉት ዜጎች እየበረከቱ እየሄዱ ነው። ለምሳሌ ት.ህ.ዴ.ን ድርጅትና ሌሎች በርከት ያሉ ኃይሎችን ልንጠቅስ እንችላለን።



ስለዚህ የወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ስርዓት በስልጣን እያስቀጠሉት ያሉ ነጥቦች ከዚህ በላይ የጠቀስናቸውና ሌሎችም በመሆናቸው መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ እነዚህን የለውጥ እንቅፋት የሆኑ አስተሳሰቦችና አመለካከቶች በሚገባ አርቆ በማስተዋል፣ ቀጠሮ ሳይሰጥ ይህንን አፋኝና ፀረ ዴሞክራሲ የሆነ ስርዓት ለማስወገድ ህዝቡ ሁለንተናዊ የሆነ ትግል እንዲከተልና፣ በቆራጥነት በበረሃ ፊት ለፊት ከስርዓቱ ጋር እየተናነቁ ያሉ የህዝብ ልጆች በተቻለው መጠን ሊያበራታታቸውና ከጎናቸው ሊሰለፍ ይገባል።

## <u>የትግራይ ህዝብ ሊሄደው የፈለገው መንገድና ተግዳሮቶቹ</u>

*ባለፉት 25 ዓመታት የትግራይ ህዝብ ተጨባጭ ማስረጃዎች በሌላቸው የጥቅም ሐሜት ሲታማ መቆየቱ የሚታወቅ ሆኖ የዚህ ማሳያም ከሃሜት የዘለለ፣ በዚህ ክልል ተወላጆች ላይ ያተከረ በአሁኑ ወቅት ጎልተው እየተፈፀሙ ያሉት ተግባራትና የአደባባይ ንግግሮች በቂ ማሣያዎች ናቸው። የትግራይ ህዝብ ሊሆን የፈለገውና ይዞት ያለው መንገድስ ምን ይመስላል? የሚለውን ሃሳብ በጥያቄ መልክ ማንሳቱ አስፈላጊነት ያለው ነው። የትግራይ ህዝብ ጥቅም ከዚህ ስርዓት ነው የሚለውስ ሐቅ ነው? እነዚህና ሌሎችን ሁሉንም መሬት ላይ ካለው የትግራይ ህዝብ ነባራዊ ሁኔታ ጋር አነጣጥሮ ከስሜት ውጭ ሆኖ በትክክለኛ ዓይነ ህሊና ሲታይ ወይም ደግሞ ሲነበብ ግን ቅንጣት ታህል የዚህ ሃሳብ ሐቀኝነት ማግኘት አይቻልም።*

*ምክንያቱም ያልሆን ስለሆነ። ሌላው ይቅርና ይህ የቅርብ ሩቅ ከ25 ዓመታት በፊት ባካሄደው የትጥቅ ትግል የገበረው ንብረትና የከፈለው የህይወት መስዋዕት ለምን መሆኑ የተረዳቸው አይደሉም እነዚህ እንደዚህ ነህ የሚሉት። ለጭቆናና ለብሄራዊ የበላይነት ቦታ ያሳጣ ህዝብ መከታነቱ ሊጋራ ጥቅም የበላይነት አይደለም ወይ ትግሉ? በጠቅላላስ ህሊና ከመግዛት አይደለም ወይ ይህን መራራ የትጥቅ ትግል ያካሄደው? ተመልሶ ይህንን የሚያመቻችለት መንገድ እንዴት አድርጎ ይመርጠዋል ይባላል?*

*በርግጥ ነው ማለት ሳይሆን እዚህ ላይ መምጣት የነበረበት ሌላ ቢሆን በተሻለ። ይህ ማለት ከግንቦት 20 ድል በኋላ ባሉት ዓመታት ስርዓት የመለወጥ ትግሉ የተዳከመ ይመስላል በሚለው ሃሳብ ትንሽ ሊመስል ይችላል ብለህ ልትጠብቅ ትችላለህ። ማለትም ከዚህ ስርዓት የኋላ ጀርባ አመጣጥ ጋር ተያይዞ ሊመጣ የሚችል ስለሆነ። ትክክል ነው ማለት ግን አይደለም። ለአንዳንድ የዋህ ወገኖች መስሎ እየታያቸው ስለነበር ነው። እንደዚህ ብሎ ነው የሚቀጥል? ሌላ ነገር ሆኖ።*

*በማንኛውም አይነት መለኪያ ግን የትግራይ ህዝብ በዚህ ስርዓት ላይ ያለው ጥላቻ ካለፉት ጨቋኝ ስርዓቶች ተለይቶ የሚታይ አይደለም። ይህ ከሆነ ታዲያ ፍላጎቱን የመፈፀም አቅሙን አግቶ የያዘው ምንድነው ሲባል ደግሞ ይህ አመለካከት የትግሉ አንድ አካል*

*በማድረግ በተፈጠሩት የትግል መድረኮች ተካፋፍሎ እየታገለ መሆኑን እንድትገነዘብ ያደርጋል። እዚህ ላይ ግን ይህ አይነት አመለካከት ለምን ለትግራይ ህዝብ ተሰጠው ወይም ለምን ተነሳ ሳይሆን መምጣት ያለበት ምን ስለተፈለገ ነው በእንደዚህ አይነት ሊገልፁት የሚሞክሩ ችላ ተብሎ የማይታለፍ መመራመር የሚያስፈልገው ጉዳይ ሆኖ ይገኛል።*

*ሁል ጊዜ የትግራይ ህዝብ ሁለንተናዊ አስተሳሰብ፡ አድሎና ብዝበዛ፣ የአንድ ብሄርም ሆነ ቡድን ወይም ግለሰብ የበላይነት ፈፅሞ የማይፈቅድ፣ በጋራ ጥቅምና እድገት የሚያምን አገራዊ እምነት የታጠቀ አስተሳሰብ ነው ብለናል። ስለሆነም ይህንን አስተሳሰብ እንዳለ መግቻ አድርገው የሚቃኙትና የሚያዩት አልታጡም እንደየራሱ አመለካከት ስለሆነ። እንደዚህ ስለሆነም ነው ባዳ ሊያዛምዱ እየፈለጉ ያሉት። ካልሆነ ጥቅሙ በየትኛው መንገድ ነው፣ ይህ ህዝብ ከዚህ ስርዓት ተጠቅሟል የሚባለው? የትግራይ ህዝብ እንደህዝብ መልስ ያስፈልገው ነበር መላሽ አካል ግን የለም። ከየት ይመጣል? ሊመጣም አይጠበቅም። የሚያናጋ ንግግር በህዝብ መካከል ወርውሮ ዝምታ ነው በቃ።*

*ተፈልጎ ያለው ግን በትክክል የትግራይ ህዝብ ከዚህ ስርዓት ስለተጠቀመ ሳይሆን ያለህበትን ሁኔታ ማለትም ካንተ ይልቅ የጭቆናና የአፈና የጥፋት መንገድ ያዘነበለ መጥፎ ፖሊሲ በሚያሰላስል ስርዓት ተነጥቆ ዝም ብለህ ልታይ ካለመቻል የመነጨ ቅናት ነው።*

*ሌላ ብቸኛ መግለጫ አይገኝለትም የለውምም። ግን እንደዚህ አይደለም። ይህ ዘመን ያለፈው አስተሳሰብ ነው። ልክ ዘርን በአለት ላይ እንደማፍሰስ በቃ ከንቱ ድካም ውጤት የሌለው የሚፈልገውን ተከፍሎት የታለፈ የተዘጋ ምእራፍ ስለሆነ መካን ቅሬት ይዞ የሚደረግ ለስልጣን ፍለጋ ነው። ካልሆነ ግን ይህንን ጭቁን ህዝብ ተጠቃሚ መስሎ ሊቀርብ የተፈለገበት መንገድ ግን ይህ ስርዓት ውሎ አድሮ በሚፈፅማቸው መጥፎ ተግባሮች ከስልጣኑ መወገድ ስለማይቀረው ከስርዓቱ ቀብር በኋላ እንዲመጣ የሚፈለግ የስርዓት ለውጡ በአይነቱ ከዚህ በማይለይ መንገድ እንዲተካ ስለታሰበ ብቻ ነው።*

*ህልማቸውን ለመተግበር ደግሞ የግድ ሊቀበላቸው የማይችል ህዝብ፣ ሊታገላቸው የሚችል ህዝብና ሊያስቀጥላቸው የማይችል ህዝብ አስቀድመው ማን መሆኑን ስላወቁ ብቻ ነው አስቀድመው የስም ማጥፋት መርጠው ትኩረታቸውን ወደዚህ ህዝብ ሊያደርጉ የቻሉት። ለትምክህት ተብሎ የትግራይ ህዝብ በቃ ያለውን እንዳሻው የማድረግ ችሎታ በራሱ ብቻ የተመረኮዘ ነው ለማለት ነው ግን ይህ አባባል አይደለም። ታዲያ ባለችው አቅሙ በምትፈቅድለት ይህችን አገር ለጥሩ ነገር ያለምንም ሽፋን እሱን ከመሰሉ ጭቁን ወገኖቹ ጋር ሆኖ ጭቆናንና ብዝበዛን ላለመቀበል ለሚደረግ እንቅስቃሴ ቅድሚያ ሰጥቶ የሚሰራ የታጠቀ ህዝብ ስለሆነና ስለሚያምኑ ነው።*

*ካለማወቅ ነው እንጂ የዚህን ስርዓት የስልጣን እድሜ ጊዜ ከመንተት አልፎ ይህ ማለት በየቦታው የተቀመጡ ጠላቶች እንዳሉ የሚታይበት መንገድ የለም እንደማለት ነው የሚሆን። እዚህ ላይ ግን የማይካድ ጥቂት ህዝብ የሚደናገርበት እንዳለ ነው እያየንም ስለሆነ። የትግራይ ህዝብ እንደሚባለው ያልሆንና የዚህ ሃሜት ባዳ መሆኑን ግን ተግባራዊ ምስክሩ የመስዋዕት አድማሱ ነው። በትግራይ የታጠረ ከሆነ እነዚህ በዚህ ቃል ሊደለሉ ተፈልገው ያሉት ባሉበት ቦታ ያሉ አፈረ አዳም ያልለበሱ የትግራይ ስውዓት ለሃገራቸውና ለህዝባቸው ካላቸው ክብር የመነጨ አይደለም ወይ እራሳቸውን የገበሩት።*

*እንደመልካም ተግባር አምኖ አይደለም ወይ ማንኛውንም ነገር ለዚህች አገር የከፈለው። ይህ ከሆነ እውነታው ለምንድን ነው ለዚህ ህዝብ የማይገልፀውን ሊሰጡት የተፈለገው? መሰረታዊ ሊመለስ የሚገባው መልስ የሚያስፈልገው ሃሳብ ነው። እዚህ ላይ ነው*

*እንግዲህ ምንና እንዴት አይነት የህዝብ እንከኖች ገጥሞ እየታገላቸው የሚገኝ መግለጫ የሚያስፈልጋቸው። ምናልባት በተሞክሮ የበሰለ በመሆኑ ካልሆነ በስተቀር እነዚህ አሁን መሬት ላይ ያሉት ተግዳሮቶች ከማንኛውም ጊዜ በላይ በአይነትና በብዛት ካለፉቸው ወቅቶች ጋር ሲነፃፀር የጠነከሩና የተለያዩ መልኮችን የያዙ ሆነው እናገኛቸዋለን። ይህ አሁን እየተፈፀመ ያለው ፍፃሜ በፈለገው አይነትም ይሁን መልክ ትኩረትን የሚመለከት የነዚህ ነፀብራቅ የጠቅላላውን የኢትዮጵያ ህዝብ ምስል ያረፈበት የሚያንፀባርቅ ሆኖ አታገኘውም። ታድያ የጥቂት ግለሰቦችና ቡድኖች አሻራ ያረፈበት ወደ ትግራይ ህዝብ ያነጣጠረ፡ ያልሆነ ስህተት አቋም ታገኛለህ።*

*ይህ ግን የትግራይ ህዝብ በጥቅም አይን ስለታየ አይደለም። ከላይ እንደተጠቀሰው ዋናው ጉዳይ በዚህች አገር አመጣጥ ያለው ቦታ እንደ አቋም በማንኛውም ጊዜ የማይቀየር ደልዳላ ህዝባዊነት ያለው መሰረት ያነጠፈ ህዝብ ስለሆነ ብቻ ነው። የትግራይ ህዝብ ትግል ከስልጣን ሽሚያ ርቆ በአንድ ወጥ አስተሳሰብና አገራዊ ጥቅም ቅድሚያ የሚሰጥ ትውልድ በመገንባት አስተማሪ ሆኖ ስለተገኘና ይህ ትውልድ ይሁን ብሎት በተግባር ሊከተለው ስለቻለ ነው። ጥቅም ተብሎ ሊገለፅ የሚችል ካለ ግን በሺዎች መስዋዕትነት ዋጋ ሊያገኘው የቻለ ብቸኛ ጥቅም ቅኑ አገራዊ አስተሳሰብ መገንባት ነው። ይህ ነው እንግዲህ ሊዋጥላቸው ያልቻለ። ውስጣቸውን የሚቆረቁራቸውና መታወቅ ያለበትም። ካልሆነ ግን ይህ ስርዓት በሚፈፅማቸው መጥፎ ተግባሮች ከስልጣኑ ለማስወገድ የትግራይ ህዝብ ድርሻ የበለጠ ሆኖ አሁኑም በመጨረሻው የለውጥ መንገድ እየተጓዘ ነው ያለው። የሚደራደርበት ወይም የሚማፀንበት መንገድ የለም። የሚደጋገም ምክንያታዊ ያልሆነ ሃሳብ ግን አለ። እሱም፦*

*በተጨባጭ መስረጃ የተደገፈ ባይሆንም እንኳን የትግራይ ህዝብ እንደተጠቃሚ ተደርጎ የሚቀርብበት ምክንያት፣ የማእከላዊ መንግስት የስልጣን አያያዝ በክልሏ ተወላጆች ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚሄድ ጥቅማጥቅምና የአንድ ብሄር የበላይነት የሚሉ ሌሎች ተዛማጅ ተዳብለው የሚቀርቡ ምክንያቶች አሉ። የትግራይ ህዝብ በልዩ የተጠቀመበት መንገድ የለም። እያየናት ያለችው ትግራይ አይደለችም ወይ ትግራይ እየተባለች ያለችው? በቂ ምክንያት የያዘ ወይም ያለው እስኪ እንደምሳሌ ያቅርብ? ሊያመጣ ግን አይችልም ስለሌለ። የትግራይ ህዝብ እልፍ ጭቁንነት ግን ከዚህ አመለካከት ነው የሚጀምር። እነዚህ ህወሃትንና የትግራይን ህዝብ ምንነታቸውን ለይቶ ማየት ያልቻለ የህሊና መነፀር የታደሉ ናቸው።*

*የትግራይ ህዝብ ህልሙንና ፍላጎቱን በህዝቦች እኩልነት ያመነ ትውልድ እንዲፈጠር የተጠየቀውን ንዋይ የከፈለ ብቻ ሳይሆን ለዚህ ታሪካዊና ስር የሰደደ ትምክህትም ቢሆን አፍሽሎ የቀበረና ለዚህ ብልጭታ ቅሬት ዳግማዊ ህይወት እንዳይዘራ መከላከል፣ ኢትዮጵያዊ አስተሳሰብ እንዲሆን የድርሻውን የተጫወተና እየተጫወተ ያለ ህዝብ እንደሆነ የሚዘነጋ አይደለም።*

*በስም ብሄራት የሚሸቀጡ ግን ደግሞ የህዝብ ተልዕኮ የሌላቸው ግለ ሰቦች የትግራይን ህዝብና ይህ ስርዓት አንድ ናቸው የሚል የሚያቀርቡት ትችት በእነሱ እምነት የትግራይ ህዝብ ከሌሎች ወንድሞቹ ህዝቦች ጥላቻ እንዲያድርበት አድርጎ በመነጠል፡ ይህችን አገር እንደፍላጎታቸው ሊያሽከረክሩ የሚችሉበት ቦታ የሚፈጥር ነው የሚመስላቸው። ግን ደግሞ ከንቱ አስተሳሰብ ነው። ፍፁም ከኢትዮጵያ ህዝብ ፍላጎት የማይስማማ አስተሳሰብ። ሌላው ይቅርና ከወረቀት የማያልፈው የስርዓቱ ህገ መንግስትም ለዚህ የሚፈቅድ ሆኖ አልተቀረፀም።*

*ምክንያት ግን አለው። ለጥሩ ስላሰበ ሳይሆን ጥሩ ላልሆነ ነገር የሚራመድበት ፊት ለፊት በዚህ ገጥሞ ሊሆንለት የማይችል መሆኑን ስላመነ ብቻ ነው። ይህም ከዚህ የሚለይ*

*አይደለም። በዚህም አለ በዚህ በፈለገው መንገድ ይምጣ የትግራይ ህዝብ አገራችን ኢትዮጵያ እንደ አገር አገራዊ ክብር እንድትጎናፀፍ የሚያደርገው ትግል የማያቋርጥ የህዝባዊነቱ መስመር ነው። አሁንም ይህ እንዳለ ነው ያለው እየቀጠለም ነው። በጥቂት የዚህ ቋንቋ ተናጋሪዎች በሚፈፀም መጥፎ ተግባር የሚበረዝ አይደለም። እውነታው ይህ እያለ ለዚህ የሚፃረር ደግሞ መልካም ተግባር ለመፈፀም የሚመለስ ግላዊ የቤት ስራ ስላለው ሳይሆን ከማዛጋት የማያልፍ በተረት ያለቀ ድብቅ አጀንዳ ይዞ ኢ-ፍትሃዊ መንገድ የመረጠ ነው።*

*ካልሆን ግን ትምኒቱ ጥሩ የሆነ ኢትዮጵያዊ ለትግራይ ህዝብ በዚህች አገር አመጣጥ ያደረገው አስተዋፅኦ ሌላ አይነት መልክ የሚወጣለት አይደለም። ባለፈው ያስነሳው የለውጥ ትግል እንዳሰበው ያለመሄዱ ግን ተጠቃሚ ሳይሆን እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ተጠቂ ከመሆኑ ባለፈ እልፍ ሹመቱ በዚህ አመለካከት ለመታማት መብቃቱ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ ለትግራይ ህዝብ ተጨማሪ ሊታለፍ የሚገባው ትግል ነው። በጥቅም ደረጃ ከሚገለፅ ይልቅ በጭቆና ደረጃ ቢገለፅ ደግሞ በተሻለ ነበር ሐቀኝነቱ ተቀባይነት ባገኝ።*

*በዚህም ይበል በዚህ "በሬ ወደ ፈለገው ያዘንብል እርፉን ግን አጥብቅ" ነው መፍትሄው። እኛ ኢትዮጵያውያን አይደለም ውሻ ጮኾ አንበሳ ቢያገሳም የሚይስፈራን አይደለም። አልወረስነውም የእኛም አይደለም። የህዝብ ውክልና የሌላቸው አንዳንድ አጎብዳጊዎች በትግራይ ህዝብ ላይ ጀነሳይድ ለመፈፀም ቢፍጨረጨሩም የሚያስደነግጥ የለንም። ምክንያቱም እኛ ትግሬዎች አይደለም መብታችን የወገኖቻችን መብትም እንዲከበር እናደርጋለን። በክንዳችንና ፅኑ ኢትዮጵያዊ አስተሳሰባችን አምነን የምንኖር በጮኽ ውሻ የማንንከስ አንበሳዎች ነንና። ከመላው የአገራችን ህዝቦች ጋር ያለን ፍቅርና አንድነት ደግሞ ፅኑ ኪዳን ነው።*

## <u>የህዝባችን የማንነት ጥያቄ ህገ-መንግስታዊ ምላሽ ሲያገኝ እንጂ በኃይል አይቀለበስም!!</u>

ምናልባት ይህንን አርዕስት ስናነሳ ያለአንዳች ምክንያት አይደለም። ምክንያቱም ይህ ለአመታት መፍትሄ አጥቶ ተዳብሎ የቆየ የኢትዮጵያ ህዝብ መሰረታዊ ጥያቄና ፍላጎት የመጨረሻውን ደረጃ ደርሶ ዛሬ በላዩ ላይ ሆኖ ቸ ፈረሴ ሲለው የቆየና ያለውን ስርዓት ከስረ መሰረቱ ነቅሎ ለመጣል የፈነዳው ትግል በአንድ በኩል፤ በሌላ በኩል ደግሞ አታስፈልገንም የተባለ ስርዓት ከህዝብ ሲቀርቡ የቆዩና ያሉ መሰረታዊ የስርዓት ለውጥ ለዚህ ሊጠፋ የማይችል የተቀጣጠለው እሳት ጊዜያዊ መከላከያ የሚሆነው ከመስራትና ከመፈፀም በዘለለ ሌላ በህዝብና በሃገር ላይ አንጃቦ ያለውን አደጋ ሊያድን የሚችል ዘላቂ የሆነ መፍትሄ ሊያስቀምጥ ወይም ደግሞ ስልጣኑን ለባለቤቱ የኢትዮጵያ ህዝብ ሊያስረክብ ባልቻለበት።

በተጨማሪም ስለሃገርና ስለህዝብ ያገባናል የሚሉ አካላት በአንድ መድረክ ተሰባስበው ልዩነታቸውን አጥብበው ህዝብ እንደህዝብ መጠን ክብሩ፣ ዋስትናው፣ አንድነቱ፣ ፍቅሩ፣ ዝምድናው ሊጠናከር የሚችልበት ህገ መንግስታዊ መብቱ ተጠብቆለት የዴሞክራሲ አቋሞች ያለመሸራረፍ እንዲተገበሩና ወደፊት ሊያራምድ የሚችል ቦታ እንዲመቻች ኣላደረገም። እንዲያውም የሰላማዊ ትግሉን መንገድ ይዘው ይንቀሳቀሱ የነበሩ ተቃዋሚዎችን መልሶ ሲያስጨንቃቸውና ብሎም የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን አባላትና አመራሮች ወደ እስርቤት ነው ሲያጉራቸው የታየው። በመሰረቱ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ሰላምና መረጋጋት ሊፈጥር የሚችል መፍትሄ

መሬት ላይ ሊተገብር የሚችል አቅምና ቅንነት ስለሌለው ልክ በዚህ ፅሁፍ አርእስት እንደተገለፀው ህዝብ ያስነሳውን ደማቅ ትግል ወደ ጎን ትቶ ተሃድሶ በሚል ዘመቻ ከላይ የፌደራል አካላት ጀምሮ እስከ ክልላት፣ ዞኖች፣ ወረዳዎች፣ ብሎም እስከ ቀበሌዎች ተሳስተን ነበር፣ በሙስና ተጨማልቀን ቆይተናል፣ ህዝባዊ ወገንተኝነት የምናረጋግጥበት የህዝባችን ጫማ ሆነን የምናገለግልበት ወቅት አሁን ነው። እኛ የላይኞቹ አካላት በጥልቀት ታድሰናል መላው ብዙሃን ደግሞ በጥልቀት ተሃድሶ የነበሩትን ስህተቶች አርሞ በአዲስ መንፈስ መራመድ አለበት በማለት ተጠምዶ ይገኛል።

ምናልባት ይህ ተሃድሶ የሚል ዘመቻ ወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴግ የተቀጣጠለውን ህዝባዊ ትግል መፍትሄ ሊሆነው ይችል ይሆን? በመሰረቱስ ወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ እራስ በራሱ ታድሶ በስልጣን ሊያስቀጥል የሚችል የህዝብ ድጋፍ ይኖረዋል? መሰረታዊ የህዝብ ጥያቄና ፍላጎትስ ምንድን ነው? ብለን ጥያቄ ስናነሳ ወያኔ ተሃድሶ ከማወጁ በፊትና በኋላ ያለው ሁኔታ ምን መሆኑን በወሳኝ መልኩ እናየዋለን። ወያኔ ይህንን የሚመልስበትንና አከታትሎ የተነሳውንና አሁንም ገና ታፍኖ ያለው ጉዳይ ምን እንደሚመስል እንይ።

ስለማንነት ካነሳን አንድ ህዝብ ማንነቴ አልተጠበቀልኝም ብሎ ጥያቄ ሊያቀርብ የሚችል የት ሆኖ ነው? ጥያቄ ሊያቀርብ የሚችልስ ለማን ነው? ፍትህ ባጣበት ጊዜ ምንድን ነው ማድረግ ያለበት? ለዚህ በህገ መንግስቱ ማንነቴ አልተከበረልኝም ወይም አልተጠበቀልኝም ብሎ ጥያቄ ያስነሳ ህዝብ ራሱ የህዝቡ ባለቤት ሆኖ በህጋዊ መንገድ በተወካዮቹ ወደ ክልል ም/ቤት ይሁን ህዝብ ቀጥተኛ በሆነ ተሳትፎ ጥያቄ የማቅረብ መብት እንዳለው ይገልፃል። በዚህ ልክ ደግሞ በርከት ያሉ የአገራችን ብሄረሰቦች የማንነት ጥያቄ እያነሱ ለአመታት መልስ ሳያገኙ እንደመጡና እንዳሉ የሚታወቅ ነው።

ይህ በመሆኑ ደግሞ በርከት ያሉ የአገራችን ብሄረሰቦች ለጥያቄያቸው ተገደው በሰላማዊ ሰለፍ በኩል ወደ አደባባይ ወጥተው ቁጣቸውን ለመግለፅ በሞከሩበት ወቅት ደግሞ በላያቸው ላይ በፀጥታ ሃይሎች የማያባራ ግርፋትና ስቃይ ሲደርስባቸውና ከዚህ በዘለለም ወደ አላስፈላጊ ግጭትና ግርግር እየገቡ እንደመጡና እንዳሉ የሚታወቅ ነው። ለዚህ እንደምሳሌ ማንሳት ይቻላል።

1, በአማራ ክልል በቅማንት ህዝብ የተነሳውን የማንነት ጥያቄ የሚመለከት ነው። የቅማንት ብሄረሰብ ባነሱት የማንነት ጥያቄ ለተወሰኑት እውቅና ሰጥተናችኋል ተብለው መልስ ሲያገኙ፡ አብዛኛዎቹ ደግሞ መልስ ሊያገኙ ባለመቻላቸው ወደባሰ ግጭትና የሰው ህይወት ወደጠፋበት ሲገባ ታይቷል። የቅማንት የማንነት ጥያቄ በወከሏቸው አካላት በኩል ወደ ክልል ም/ቤት እና የፌደሬሽን ም/ቤት ህገ መንግስታዊ መብታችን ሊከበርልን ይገባል በማለት ላቀረቡት ጥያቄ ፈጣን ምላሽ ባለማግኘታቸው በአማራና በቅማንት ብሄረሰብ መካከል ወደ አልተፈለገ ግጭት በማምራቱ ከሁለቱም ወገኖች የብዙ ሠዎች ህይወት እንደጠፋና በርካቶች እንደታሰሩ በተለያዩ ጊዜያት እየገለፅነው እንደመጣን የሚታወስ ነው።

ይህ በአማራ ብሄርና በቅማንት ብሄረሰብ መካከል የተነሳው ግጭት በአገሪቱ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ሰኔ 19 ቀን 2008 ዓ.ም ባወጣው ሪፖርት 22 ሠዎች ተገድለው፣ 10 ሠዎች ደግሞ ቆስለዋል ሲል ቁጥራቸው በትክክል ያልታወቁ ወገኖች ደግሞ እንደታሰሩ ገልጿል።

2, በትግራይ በወልቃይት የማንነት ጥያቄ በተነሳው ሰበብ በወቅቱ ጥያቄውን በህገ መንግስታዊ አይን ተፈትሾ መልስ ማግኘትና መልስ ሊሰጠው እየተገባው ይህንን ጥያቄ ያስነሱትን ወገኖች ፀረ ህገ-መንግስታችንና ሰላማችን፣ እንዲሁም ልማታችን ያነቃቸው ናቸው

እየተባሉ በየጊዜው ሲታሰሩ፣ ሊገደሉና በድብቅ እንዲታፈኑ እየተደረጉ እንደመጡና እንዳሉ የሚታወቅ ነው።

3, በተለይ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች በየጊዜው ስለማንነት ጥያቄ በሚመለከት በሰኔ ወር 2008 ዓ.ም ባወጣው መረጃ እኛ ማንነታችን አማራ ነው በሚል የማንነት ጥያቄ ያነሱ ወገኖችን 34 ሠዎች እንደሞቱ፣ 93 የሚሆኑ ደግሞ በተለያየ ጊዜና ቦታ ታፍነው እንደተወሰዱ እስካሁን ድረስ የት እንዳሉ አድራሻቸው እንደማይታወቅ ባወጣው መረጃ አስታውቆ ነበር። ይህ እንዳለ ሆኖ ብዙ ወገኖች ደግሞ እንደታሰሩ፣ 12 የሚሆኑ ወገኖች የማንነት ጥያቄ በማንሳታቸው ብቻ መኖሪያ ቤታቸውንና የእርሻ መሬታቸውን እንደተቀሙ 173 ሰዎች ደግሞ ከመኖሪያ ቤታቸው እንደተባረሩ በወቅቱ የወጣው መረጃ አመልክቷል።

ይህ መፍትሄ ሊሆን ስላልቻለ ደግሞ ጥያቄው ወደ ሌላ አቅጣጫ አምርቶ ህዝባዊ ጥያቄ ያነሱ አካላትን ለመያዝና ለማሰር በተደረገው እንቅስቃሴ ተከትሎ በሰሜን ጎንደር ሐምሌ 5 ቀን 2008 ዓ.ም የተነሳው አመፅ የዚህ ውጤት ነው። ይህ ጥያቄ ትክክለኛም ይሁን አይሁን በህገ መንግስቱ በሰፈረው መሠረት በወቅቱ መልስ ማግኘት እየተገባው ስርዓቱ የፀጥታ ሃይሎችን በማሰማራት የህዝብን ጥያቄ ያስነሱትን ወገኖች በሃይል ለመጨፍለቅ ተሰማርተዋል።

ጉዳቱ ደግሞ ይህንን ተከትሎ የተነሳው ሠፊ ህዝባዊ ተቃውሞ በጎንደርና በባህርዳር በአጠቃላይ በሁሉም የአማራ አካባቢዎች ህዝቡ በንቅናቄ ተነስቶ ወደ አልተፈለገ ግጭትና ህይወት መጥፋት ከባድ ውድመት አስከትሏል። እዚህ ላይ መነሳት የሚገባው ነጥብ ካለ የማንነት ጥያቄ የማቅረብ መብት ያለው ራሱ በአካባቢው ሠፍሮ የሚገኝ ነዋሪ ህዝብ እንደሆነና ይህም በአካባቢው ባለው አስተዳደር ብሎም እስከ ክልል ም/ቤት በማቅረብ መፍትሄ ካጣ ደግሞ ወደ ፌደሬሽን ም/ቤት ጥያቄውን እንደሚያቀርብ ይታወቃል።

እነዚህን ሂደቶች የሚጥስ እንቅስቃሴ ካጋጠመ ደግሞ ጊዜ ሳይወስዱ መንገዳቸውን ጠብቀው እንዲሄዱ አቅጣጫ በማስያዝ ህገ መንግስቱ በሚለው አይን ታይቶ ዘላቂ መፍትሄ ሊደረግበት ይገባ ነበር። ይሁን እንጂ ወያኔ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ዱላንና እስራትን እንደመፍትሄ እያደረጉ ህገ መንግስቱን እንደፍላጎታቸው እየጣሱ ለመኖር በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የተነሳ የተለያየ አመለካከት "በኑግ የተገኘ ሰሊጥ አብሮ ይወቀጣል" እንደሚባለው ጠላትና ወዳጅ በማይለይበት አኳኋን ንፁህ ህዝብ አብሮ እየተጨፈለቀ ህይወቱን ሲያጣ፣ ንብረትን ሲወድም፣ በአገሩ ላይ እንደሁለተኛ ዜጋ ተቆጥሮ ወደ ትውልድ አገሩ ሲፈናቀል ታይቷል።

ይህ ደግሞ የተነሳውን ህዝባዊ ትግል ወደ ኋላ የሚጎትት፣ ህዝቦች አብረው በስርዓቱ ላይ እንዳይነሱ የሚያደርግ፤ ለስርዓቱ ደግሞ ጊዜያዊ መደበቂያ እንዲጠቀምበት የሚያጠናክር ከመሆን አልፎ ወደፊት የሚያራምድ ተግባር አይደለም። ምክንያቱም የስርዓት ለውጥ እየተፈለገ የህዝቦችን አንድነት እየተበታተነ የሚያሸንፍ የህዝብ ትግል ስለሌለ። ሁሉም ጭቁን ህዝቦች ተስማምተው በላያቸው ላይ ሆኖ ማለቂያ የሌለው ኪሳራዎች እያወረደ ያለው ጨቋኝ ስርዓት ለማስወገድ የበኩላቸውን እንዲሳተፉና በጋራ ጠላት የጋራ ክንድ እንዲያርፍበት ካላደረግን ለስርዓቱ እድሜ ማራዘሚያነት ከመሆን አልፎ በልፍለፋና በፉከራ ብቻ የሚለወጥ ስርዓት አልታየም አይኖርምም።

እንዲያው ይህ በደም፣ በባህል፣ በታሪክና ጋብቻ የተሳሰርን ህዝብ እንዲህ እያደረጉ ጥቅሙ ለማን ነው? ነገ ይህንን ስርዓት አስወግደን አንዲት የበለፀገችና ዴሞክራሲያዊት አገር ለመገንባት የምናካሂደው ህዝባዊ ትግል በማንኛውም አይነት መለኪያ ህዝብ ለህዝብ የሚያጋጭ፣ አንድነቱን የሚያደፈርስ፣ ጥላቻ የሚፈጥር እንቅስቃሴና ተግባር ሊኮነን ይገባል። ምክንያቱም አገር እራሷ ሰላም፣ አንድነት፣ ፍቅርና መረጋጋት አትፈጥርም።

ታዲያ በቀዳሚነት ህዝባችን ወደ አንድ አይነት አመለካከት፣ አንድነትና ሰላምን ፈጥሮ ሰላምና መረጋጋትን አግኝቶ በሚፈልገው አካባቢ እየተዘዋወረ ከሃገሩ ፀጋ በእኩልና በፍትሃዊነት የእኔ ያንተ ሳይባባል የሚኖርበት ቦታ ሊኖር ይገባል።

4, ሌላ ደግሞ በደቡብ ክልል ዋና ከተማ ሰላምበር በምትባል ወረዳ ቁጫ ብሄረሰብ እኛ ጋሞ አይደለንም እኛ ወላይታ አይደለንም ቁጫ ነው ማንነታችን ህጋዊ እውቅና ሊሰጠን ይገባል የሚል ጥያቄ እያነሳ ያለ መፍትሄ ታፍኖ እንዳለ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን እያጋለጡት እንደመጡ ይታወሳል።

ከዚህ ባለፈ ለዚህ የቁጫ ብሄረሰብ ጥያቄ ያነሱ አካላት በፀጥታ ሃይሎች እየተፈለጉ ወደ እስርቤት እንዲታጎሩ በማድረግ ጥያቄያቸውን በትኩረት ተመልክቶ መፍትሄ የሚሰጣቸው አካል በማጣታቸው ወደ ግጭትና ጥላቻ የሚያመሩበት ሁኔታ ነው ያለው።

5, በሶማሌ ክልልም መቋጫ ያጣ የማንነት ጥያቄ እንዳለ የተለያዩ መረጃዎች ያስረዳሉ። ማለትም በምስራቅና በምዕራብ አሚ ሡፍሮ የሚገኝ የዱቤ ህዝብ እኛ ሶማሌ አይደለንም ማንነታችን ዱቤ ነው በሚል ላነሳው ጥያቄ እስካሁን መፍትሄ ሊያገኝ አልቻለም።

እነዚህ ከዚህ በላይ ህገ መንግስቱን መሰረት አድርገው የማንነት ጥያቄ ያነሱ የአገራችን ብሄረሰቦች እንደምሳሌ ለማየት ያህል እንጂ እነዚህ ብቻ እንዳልሆኑ አልዘነጋንም። ለዚህ ግን ስርዓቱ በወቅቱ መፍትሄ ሊያበጅላቸው ባለመቻሉ የአገራችን ህዝቦች እርስ በርሳቸው እንዳይዋደዱ በማድረግ በላያቸው ላይ ከፍተኛ የሆነ ኪሳራ ሲደርስባቸውና በዚህም የተነሳ ደግሞ ለዚህ አሁን ተፈጥሮ ላለው አደጋ ምክንያቱ መሆኑን ለመግለፅ ነው።

## በወሰኖች ጉዳይ የሚታየውን ግጭት በሚመለከት፡

በአገራችን በወሰኖች ምክንያት የሚነሱት ግጭቶች በጣም ብዙ መሆናቸው የሚታወቅ ነው። በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን ከፍተኛ የወሰን ግጭት ትተን፤ በሁለቱ ክልሎች መካከልና በአንዲት ክልል ባሉት ቀበሌዎች፣ መንደሮች ያለው አዋሳኝ ሊሆን ይችላል። ይህ ደግሞ በአገሪቱ ከሚኖረው ከፍተኛ ቁጥር የያዘ መሬት የሌለው ዜጋ ተፈጥሮ ካለው የስራ አጥነትና ተጠቃሚነት ማጣት ጋር ተደማምሮ በዚህ ልክ እየተስፋፉ ያለው የሙስና አስተዳደር፣ የፍትህና የዴሞክራሲ እጦት ችግሩን ምን ያህል የከፋ እንደሚያደርገው ለመገመት የሚያስቸግር አይደለም። በዚህ ላይ በየቀኑ በሁሉም የአገራችን ክፍሎች የሚነሱ ግጭቶች የወሰን መከለል የሚመለከት በዚህ አጭር ፅሁፍ ሁሉንም ለመዘርዘር የሚቻል አይደለም። ምናልባት ግን አንድ ምሳሌ እናንሳ። በዚህ መሰረት ደግሞ በአማራና በትግራይ ክልሎች መካከል የሚያዋስን በጠገዴ ወረዳ የሚገኙ ቀበሌዎች ለ25 ዓመታት ያህል በሁለቱ ህዝቦች መፍትሄ እንዲገኝለት በየወቅቱ እያቀረቡት የመጡት ጥያቄም ይሁን አቤቱታ ያለመፍትሄ እስካሁን ተዳፍኖ እየቀጠለ ነው።

ይህ ችግር ወደ ባሰ ሁኔታ ሳያመራ መቋጫ እንዲያገኝ ህዝብ በቀጣይነት እየጠየቀ የመጣ ቢሆንም ለዚህ ትኩረት ሰጥቶ መፍትሄ የሚያደርግ የሁለቱ ክልሎች አስተዳደራዊ አካል አልተገኘም። አንድ ህዝብና አገርን ወክሎ አስተዳድራለሁ የሚል ስርዓት እንኳንስ ለ25 ዓመታት ያህል እየተቋሰለ የሚኖር የህዝብ ጥያቄና ችግር አፍኖ ሊኖር ይቅርና ለአንድ አመት የሚሆን መፍትሄ ሳያደርግለት ከቀረ በስልጣንም ይሁን በህዝባዊ አስተዳደር የሚያቆየው ሁኔታ የለም። ይሁን እንጂ ኢህአዴጋውያን በመላ ህዝቦች ትግል የተገኘውን

ስልጣን ለግላቸው አድርገው ህዝብ ያሸከማቸውን አደራና ቃል ኪዳን ረስተው በሙስናና ስርቆት ተግባሮች ተሰማርተው ወደዚህ አሁን ተፈጥሮ ወዳለው ሁኔታ ይዘውት ተጉዘዋል። ስለሆነም በሁለቱ ክልሎች መካከል የሚኖር ህዝባችን ስር በሰደደው የሁለቱ ክልሎች አመራሮች እርስ በርሳቸው ባለመስማማት የተፈጠረ ክፍተት " ሁለት ዝሆኖች እየተጣሉ ሳር ይጎዳል" እንደሚባለው ሆኖ ጭቁን ህዝብ ከሃዲ መሪዎቹ በፈጠሩት ጥላቻና ውስጣዊ ነውጥ በተለያዩ ችግሮች ተቀርቅሮ እንዲኖር ፈርደውበታል።

ጭቁኑ ህዝብ ግን ዛሬም ይሁን ነገ አንድነትና መዋደድ ፈላጊ ነው። ይሁን እንጂ በሁለቱ ክልሎች አመራሮች በወሰን ግጭቱ አመካኝተው የስልጣን እድሜያቸውን ለማስረዘም በሚጠቅማቸው መንገድ እየተከተሉ ያቀጣጠሉት ተንኮል ህዝባችን እርስ በራሱ እንዳይስማማ፣ እንዲጋጭ፣ ብሎም ወደ አልተፈለገ ደምነት እንዲገባ እያደረጉት ነው። በዚህ ጉዳይ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ በጥር ወር 2009 ዓ.ም መጀመሪያ አካባቢ በይምሰል ፓርላማው ቀርቦ በምክር ቤቱ አባላት ፊት "እስካሁን ይህ የወሰን ግጭት የአማራና የትግራይ ክልል ለምን መፍትሄ ያልተደረገለት" ብለው በጠየቁበት ጊዜ የሰጠው መልስ "ዋናው ችግራችን የሁለቱ ክልሎች አመራሮች ያለመስማማት በቆራጥነት በተግባር ሊፈቱት አለመቻላቸው ነው ብሎ ነበር። በዚህ በቅርቡ ቀን ደግሞ ይፈታል" የሚል እምነት አለኝ ሲል ተሰምቷል።

የሚገርም ነው ከ25 ዓመታት በላይ ያስቆጠረ ችግር በህዝብ ወንበር ተቀምጠው እንደዚህ አይነት የተለመደ መልስ መደጋገም ከዚህ ገብቶበት ካለው አደጋ ሊያወጣ የሚችል ዘላቂ መፍትሄ ታጥቶለት እንዳለ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ከመሆን አልፎ ሌላ ትርጉም የለውም። ስርዓቱ ህገ መንግስቱን እየጣሰ በየጊዜው በህዝብ ላይ ከ25 ዐመታት በላይ ሲፈፅመው የቆየ ፀረ ህዝብ ተግባራቱ ከእነዚህ ካለፉት ቅርብ ዓመታት ጀምሮ በላዩ ላይ ያነጣጠረ ህዝባዊ አመፅ በአንድ በኩል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች በፀጥታ ሃይሎቹ እያሰማራ ወገኑን ሲያስርና ሲገድል በአጠቃላይ ቀላልና ከባድ ጉዳት እያወረደ ሲመጣ በሌላ በኩል ደግሞ የተነሳውን ነበልባላማ ህዝባዊ አመፅ ለመቀልበስ ሲል የማይፈነቅለው ድንጋይና ምክንያት የለም። የህዝብ ቁጣ ያስነሳው የተቃውሞ ማዕበል፣ የማንነት ጥያቄ ትክክለኛ የሆነ መልስ በመስጠት እንጂ እንደዚህ ወያኔ እንደሚከተለው ያለ አካሄድ ተከትሎ ዘላቂ መፍትሄ ለማስቀመጥ የሚቻል አይደለም።

## ሕዝብ ነው ኃያሉ!!

ህያው ለዘላለም አይታጠፍ ቃሉ
ጋሻና መከታ አለኝታ ለሁሉ
የለም ከሱ በላይ ህዝብ ነው ኃያሉ።
አሻግሮ ተመልካች ታጋሽና አስተዋይ፣
አብዮት ፈጣሪ ፍቱን የለውጥ ሃይል፤

ተሟግቶ ሚረታ ክንዱ የበረታ
ለወፍ ዘራሽ ወሬ ፍፁም ማይረታ
አጥፊውን ለይቶ ድባቅ የሚመታ፣
ሊጨበጥ የማይችል ውስጡ ከተቆጣ
ማዕበሉ ገንፍሎ በአመፅ የሚቀጣ።

እውነት ተናጋሪ መካሪ አስተማሪ፡

በሃዘን በደስታ በአንድ ተባባሪ፣
እንደሸረሪት ድር ጠላቱን አሣሪ፣
በአርበኝነት ወኔው ፋሽስት አሣፋሪ።



በአንድ ድምፅ ሆ ብሎ ጠላቱን ያናጋ
የአምባገነኖቹን የወያኔን መንጋ
ወደፊት ተራማጅ በነበልባል ኃይሉ
የለም ከሱ በላይ ህዝብ ነው ኃያሉ።

በጠመንጃ ብዛት ፈርኦንን ቢመስሉ
ህፃን አዋቂውን ቢሰቅሉ ቢገድሉ
አጃቢ ቢናኙ ሞግዚት ቢያስከትሉ።

እውነትን ረግጠው ውሸትን ቢሰብኩ
ዘረ-ፊጅ መሣሪያ እሳት ቢታጠቁ
ማታለያ ዘዴ ቢቀይሩ መላ
ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ብላሽ ነው ይስሙላ።

በበሬ ወለደ በአፋቸው ወለምታ
በህዝቡ ጫንቃ ላይ ከበሮ ሊመታ
ሴራውን ሲቀምር የወያኔው ተርታ
ሐበሻን ለማጥፋት ሲመክር ሲዶልት
ካንተ አይሰወርም ወገኔ ተመልከት።

ተመልከት እውነቱን ላንተ ስንት ተባለ
እየተራብክ በልቷል
ሳትጠጣ ረክቷል
ሃብቱ ጣራ ነክቷል ቤት ጎተራው ሞልቷል
ይላሉ ሴረኞች እኒህ ጠላቶችህ
በስምህ ለመኖር ሚርት ቀማሪዎችህ።



እውነቱን ታውቃለህ አትኩረህ ተመልከት
ሚባለውን ተንኮል ሚዘራውን ውሸት
ሚሰራውን ሴራ ሚሰራውን ስህተት።

ፍትህ ነግሷል አሉህ የማታውቅ መስሏቸው፣
ስንት ወጣት አስረው
ስንት ወጣት ገድለው
ስንቱን ሽባ አድርገው ስንቱን ረሽነው
ዴሞክራሲ አለ አሉህ የማታይ መስሏቸው
ፍርድ እያጎደሉ ከአንድ ለአንዱ እያዳሉ
ህዝብ እየዘረፉ ሙስና እየበሉ።

ሃብታም ሆኗል አሉህ ግዑዝ ነው መስሏቸው
በድህነት ቀንበር እየተሰቃየህ
በረሃብ በቸነፈር ስንቱን እየገበርህ
በስደት በእንግልት ቂመኛ እያረደህ
ባዕዳ እያነደደህ፤ ባህር እየዋጠህ
ቤቱ ሞልቷል አሉህ እነዚህ ግፈኞች
የኢትዮጵያ ጠላት የዘርህ ቀበኞች።



በእድሜ ስልጣናቸው ረግጠው ለመኖር
በስመ ህዳሴ ሲተካኩ ወንበር
የህዝብ ደም ሲጠጡ ጠብቀው እንደመኸርገር
ቸ! ፈረሴ ሊሉህ በላይህ ላይ ወጥተው
ታድሰናል አሉ ጥርስ የሳለ አምጥተው።

ስለዚህ ወገኔ!
ወጨፎህን ታጠቅ ጦር ጋሻህን አንሳ
ለወገንህ ድረስ በአንድ አዋጅ ተነሳ
አንገት እንዳትደፋ ቀናበል ተመልከት
መጣሉ ይበጃል ታግለህ በሞት ሽረት!!

ድል ለብዙሃን ነው ታምር ለሚሰራ
አንድነቱ ብርቱ ሞራለ ጠንካራ
ህያው ለዘወትር አይታጠፍ ቃሉ
ዘላለማዊ ነው ህዝብ ነው ኃያሉ!!